መሸጥ ክልክል ነ
በነፃ የሚታደል

# ኢስላም

## መሠረቶቹና መሪህዎቹ


ዝግጅት

ዶክተር / ሙሐመድ ቢን አብደላህ
ቢን ሰልህ አልሱሀይም

ትርጉም/ሐሰን ታጁ

# ኢስላም

## መሠረቶቹና መርሆዎቹ

ዝግጅት፡- ዶክተር ሙሐመድ ቢን አብደላህ ቢን ሷሊህ አልሱሐይም

ትርጉም፡- ሐሰን ታጁ

የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::
All rights are reserved

አንደኛ እትም ጥቅምት 2002

በነጻ ይታደላል እንጅ አይሸጥም:
يوزع مجانا ولا يباع

# ማውጫ



| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| መቅድም | 5 |
| መግቢያ | 10 |
| መንገዱ የት ነው? | 14 |
| የአምላክ ሕልውናና አንድነት | 15 |
| የፍጡራን መፈጠር ጥበብ | 30 |
| የሰው ልጅ መፈጠርና ልቅና | 38 |
| የሴት ልጅ ደረጃ | 43 |
| የሰው ልጅ የመፈጠር ጥበብ | 48 |
| የሐይማኖት አስፈላጊነት | 51 |
| የእውነተኛ ሐይማኖት መስፈርቶች | 55 |
| የሐይማኖት አይነቶች | 64 |
| ሌሎች ሐይማኖቶች አሁን ያሉበት ተጨባጭ ሁኔታ | 67 |
| የነብይነት ምንነት | 74 |
| የነብይነት ምልክቶች | 80 |
| የነብያት ትምህርት አስፈላጊነት | 83 |
| መጭው አለም | 88 |
| የነብያት ትምህርት መሠረቶች | 94 |
| ዘልዓለማዊ መልእክት | 98 |
| የነብይነት መቋጨት | 106 |
| የኢስላም ትርጉም | 109 |
| የእስልምና መሰረቶችና ምንጮች | 116 |
| የእምነትና የተግባር ደረጃዎች | 127 |
| የመጀመሪያው ደረጃ ኢስላም | 127 |
| አምልኮ በኢስላም | 131 |
| ሁለተኛው እርከን ኢማን | 133 |
| እርከን ሦስት ኢህሳን | 150 |
| የእስልምና ውበትና ልዩ ባህሪያት | 153 |
| 1) የአላህ ሐይማኖት ነው | 154 |
| 2) ሁለንተናዊነት | 154 |

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| 3) ፈጣሪን ከፍጡር ያገናኛል | 155 |
| 4) የዚህችን ዓለም ጉዳዮች ያደረጃል | 156 |
| 5) ገርነት | 157 |
| 6) ፍትህ | 158 |
| 7) በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል | 158 |
| ተውባ | 160 |
| በእስልምና ያልተመራ ሰው ፍጻሜ | 164 |
| 1) በፍርሃት መሞላትና ሰላም ማጣት | 164 |
| 2) የጭንቅ ሕይወት | 165 |
| 3) ከራሱና በዙሪያው ካለው አለም ጋር በግጭት ይኖራል | 166 |
| 4) መሐይም ሆኖ ይኖራል | 167 |
| 5) ራሱንም በዙሪያው ያሉ ሰዎችንም በዳይ ሆኖ ይኖራል | 167 |
| 6) ለአላህ እርግማንና ቁጣ ተጋልጧል | 168 |
| 7) ስኬት አልባንትና ኪሣራ | 169 |
| 8) በአላህ የካደና ሕልውናውን ያስተባበለ ሆኖ ይኖራል | 170 |
| 9) እውነተኛ ሕይወትን ተነፍጓል | 170 |
| 10) ዝንተ አለም በቅጣት ውስጥ ይኖራል | 172 |
| ማጠቃለያ | 175 |




# መቅድም

መልእክተኛውን ቅን መንገድና እውነተኛ ሐይማኖት አስይዞ ለላካቸው አላህ ምስጋና ይድረሰው። የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዮች ላደረገን አላህ ምስጋና ይድረሰው። የርሳቸውን ቅን ጎዳና አጥብቀው ከሚይዙትና ወደርሱም ጥሪ ከሚያደርጉት እንድንሆን ለቸረን አላህ ምስጋና ይድረሰው።

ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ። አንድ ነው። አጋር የለውም። የጥንቶቹም የአሁኖችም አምላክ ነው። የሰማያትና የምድር አስተናባሪ ነው። ደጎችም ክፉዎችም ለርሱ አጎብድደዋል። ለተፈጥሯዊ ፍቃዱ ተገዥ ሆነዋል። አይኖችና ሕሊናዎች ፍትሁንና ቸርነቱን መስክረዋል። ያሻውን በችሮታው ወደ ቀጥተኛው ጎዳና የመራ፣ ዘልዓለማዊ ቅጣት የሚገባውን ደግሞ በፍትሁ መቀናትን የከለከለ አምላክ።

ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህ አገልጋይ መልእክተኛ መሆናቸውንም እመሰክራለሁ። እድሜያቸውን በሙሉ ጽናት ለሚጠይቅ ትግል ያዋሉ፣ በሂደቱም መከራን ሁሉ በጸጋ የተቀበሉ፣ በትእግስት ያስተናገዱ መሆናቸውንም እናዘዛለሁ። በሁሉም ሁኔታዎችና አጋጣሚዎች ወደ አምላካቸው መንገድ ጥሪ አድርገዋል። «ወደ መቀናት ኑ። ወደ ትግል (ጅሃድ) ኑ» ሲሉ አውጀዋል። አላህ በርካታ ድንቅና ከሌሎች የተለዩ ባህሪያትን ለግሷቸዋል። ሸሪዓቸውንም እስከ እለተ ቂያማ ቋሚ አድርጎታል።

ከርሳቸው ሕልፈት በኋላም ተከታዮቻቸው እስከ እለተ ቂያማ አርማቸውን ያነግባሉ። ከነርሱ ውስጥ በሐቅ ላይ የጸኑ ወገኖች ምንጊዜም ይኖራሉ። የአላህን እገዛም ያገኛሉ። እነርሱን ያልረዳ ወይም የተቃረናቸው አይጎዳቸውም። ምክንያቱም የነብያቸውን ፈለግ የሚከተሉ በሐቅ ጎዳና ላይ ናቸውና።

﴿ قُلْ هَٰذِهِۦ سَبِيلِىٓ أَدْعُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ ۚ عَلَىٰ بَصِيرَةٍ أَنَا۠ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِى ﴿١٠٨﴾ ﴾ يوسف: ١٠٨

*"ይህ ጉዳናዬ ነው። ወደ አላህ ጥሪ አደርጋለሁ። እኔም፣ እኔን የተከተሉ ሁሉም ግልጽ መረጃዎችን ይዘናል።" በል(ዩሱፍ 108)*

እነዚህ ወገኖች ከአላህ ዘንድ ያለውን ምንዳ በመሻት መንገድ የሳተውን ወደ መቀናት ይጠራሉ። የሰውን ልጅ ከጥፋት ያስጠንቅቃሉ። ሐላፊነታቸውን ወደ ኋላ አሽቀንጥረው በመጣል ጥፋት ውስጥ እንደገቡት የመጽሐፉ ባለቤቶች አይሆኑም። አላህ እንዲህ አለ፡-

﴿وَإِذْ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ لَتُبَيِّنُنَّهُۥ لِلنَّاسِ وَلَا تَكْتُمُونَهُۥ فَنَبَذُوهُ وَرَآءَ ظُهُورِهِمْ وَٱشْتَرَوْا۟ بِهِۦ ثَمَنًا قَلِيلًا ۖ فَبِئْسَ مَا يَشْتَرُونَ ﴿١٨٧﴾﴾ ال عمران: ١٨٧

*«አላህ ከነዚያ መጽሐፉ ከተሰጣቸው ወገኖች፡- "ለሰዎች ልታብራሩትና ልታስተምሩት፣ ላትደብቁትም ብሎ ቃል ኪዳንን በያዘ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። (ይህን ቃልኪዳን) ወደኋላቸው አሽቀንጥረው ጣሉት። በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሸመቱበት። የሸመቱት ነገር ምን ያህል አስከፊ ነው!»* (አሊዒምራን 187)

በመጽሐፍት ትርጉም ዝግጅትና ስርጭት መስክ የሰራ ሁሉ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ወደ እስልምና የሚጠራ መጽሐፍ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ጠንቅቆ ይረዳል። በእርግጥ በእስልምና ዙሪያ የተጻፉ መጽሐፍት ብዙ ቢሆኑም ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ወደ እስልምና ለመጋበዝ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን አያሟሉም። ምክንያቱም ከፊሎቹ ሙስሊም ላልሆኑ ወገኖች ሳይሆን ለሙስሊሞች የተጻፉ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ሙስሊም ላልሆኑ ወገኖች በማያስፈልጉ ዝርዝር የአምልኮ (ኢባዳ) ሕግጋት የተሞሉ ወይም ደግሞ በነርሱ ለመጠቀም የማያስችሉ ግድፈቶችን የያዙ ናቸው።

በኢስላማዊ ጉዳዮች፣ በአውቃፍና የዳእዋ ሚኒስቴር ውስጥ የመጽሐፍት ስርጭት ክፍል በዚህ ረገድ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ተገቢውን ጥረት ያደረገ ቢሆንም ክፍተቱን የሚሞላ መጽሐፍ ሊያገኝ አልቻለም። እኛ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሰዎች በአንድ መጽሐፍ ወይም ደራሲ ላይ ልንስማማ አልቻልንም። በሐይማኖት ትምህርት መስክ ለተጠበቡ (ስፔሻሊስት) ሰዎችም ይህንኑ ጉዳይ አዋይተን የነበረ ቢሆንም ሙሉ ስምምነት አልተገኘም። ምን አልባትም የዚህ ዋና ምክንያቱ የሐጢአት መብዛትና የአላህን መብት በአግባቡ ያለ መወጣት ችግር ሊሆን ይችላል።



ከኢስላማዊ ማእከላት ወይም አዲስ ከሰለሙ ሰዎች መሐል ለወገኖቻቸው ተርጉመው የሚያቀርቡትና ሙስሊም ላልሆኑ ወገኖች ይበልጥ ተስማሚ የሆነ ኢስላማዊ መጽሐፍ እንጠቁማቸው ዘንድ የሚጠይቁ መልእክቶች በየጊዜው ይደርሱናል። ይሁንና ወደቀኝም ወደግራም ብናማትር ይህን አይነት መጽሐፍ ልናገኝ አልቻልንም። የአላህን ሐይማኖት በአጭሩ የሚያብራራ መጽሐፍ ማግኘት አለመቻላችን ሐፍረትና ጭንቀት አላበሰን።

ከዚያም ይህን ጉዳይ በይደር ማቆየት የማያልቅ በሽታ፣ የሌለን ነገር መመኘት ሞኝነትና መሆኑን ተረዳሁ። ለዚህ ክፍተት ምንም አይነት ምክንያት ልናቀርብ እንደማንችልም ተገነዘብኩ። ለጊዜውም ቢሆን ክፍተቱን የሚሞላ፣ ቀዳዳውን የሚደፍን፣ የምንመኘውን አይነት አቀራረብና ይዘት ያለው አንድ መጽሐፍ ለማዘጋጀት አላህን አማረጥኩ። እገዛውንም ጠየቅኩ። በእርግጥ ክፍተቱን ሙሉ በሙሉ ሞልቻለሁ ብዬ አላምንም። ግና ሌሎች ይቀጥሉበት ዘንድ መንገዱን እንዳመላከትኩ፣ ያሳድጉት ዘንድ ችግኙን እንደተከልኩ ይሰማኛል።

በዚህች መጽሐፍ ውስጥ የእስልምናን መሠረቶች እና አንኳር መርሆዎች በማብራራት፣ እንዲሁም ስለ እስልምና ስናስተምርና ወደርሱ ስንጠራ ሊብራሩ የሚገቡ ነጥቦችን በማብራራት እስልምናን ባጭሩ ለማስተዋወቅ የምችለውን ሁሉ አድርጌያለሁ።

በዚህ ረገድ ሁለንተናዊ የሆኑ የነቢዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) ንግግሮችን በዋነኛነት ተጠቅሜያለሁ። ለምሳሌ ሙዓዝን ወደ የመን ሲልኩ እንዲህ ብለውታል፡-

«ከመጽሐፍ ባለቤቶች የሆኑ ሰዎችን ታገኛለህ። የአላህን አንድነትና እኔም መልእክተኛ መሆኔን እንዲመሰክሩ ጋብዛቸው። ይህን ከተቀበሉህ አላህ በነርሱ ላይ በየቀኑ አምስት ወቅት ሶላቶችን ግዴታ እንዳደረገባቸው አስተምራቸው። ይህንንም ከተቀበሉህ ከሐብታሞቻቸው ተወስዶ ለድሆቻቸው የምትሰጥ ምጽዋት ግዴታ እንዳደረገባቸው ንገራቸው. . .»[1]

ዑመር ኢብኑል ኸጧብ ያስተላለፉት ሐዲስም ይጠቀሳል፡-

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም

አንድ ቀን ከአላህ መልእክተኛ ዘንድ ተቀምጠን እያለ አንድ ሰው መጣ። ልብሱ በጣም ነጭ፣ ጸጉሩ ደግሞ በጣም ጥቁር ነው። የጉዞ ምልክት አይታይበትም። ከመሐከላችንም የሚያውቀው የለም። ከነቢዩ አጠገብ ተቀመጠ። ጉልበቱንም ወደ ጉልበታቸው አስጠጋ። እጆቹን ከጭኖቹ ላይ አሳረፈ። «ሙሐመድ ሆይ፣ ስለ እስልምና ንገረኝ» ሲልም ጠየቃቸው። የአላህ መልእክተኛም «ኢስልምና ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከርህ፣ ሶላት መስገድህ፣ ዘካ መስጠትህ፣ የረመዷንን ወር መጾምህና ወደ አላህ ቤት መንገዝ ከቻልክ ሐጅ ማድረግህ ናቸው።» አሉት። «እውነት ብለሃል» አላቸው። በድርጊቱ ተገረምን። ይጠይቃቸዋል። ሲመልሱለትም፡ «እውነት ብለሐል» ይላቸዋል። «ስለ ኢማን ንገረኝ» አላቸው። «በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍት፣ በመልእክተኞችና በመጭው ዓለም ማመንህ፣ እንዲሁም በቀደር-ደግም ሆነ ክፉ- ማመንህ ነው» አሉት። «እውነት ብለሀል» አላቸው። «ስለ ኢህሳን ንገረኝ» ሲልም ጠየቃቸው። «አላህን እንደምታየው አድርገህ ማምለክህ ነው። አንተ ባታየው እርሱ ያይሐል።» አሉት። (ሰውየው ጥያቄውን አጠናቆ ሄደ)። ነቢዩም «ዑመር ሆይ፣ ጠያቂው ማን እንደሆነ ታውቃለህ?» አሉ። «አላህና መልእክተኛው ያውቃሉ» አልኳቸው። «ጅብሪል ነው። ሐይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ነው የመጣው» አሉ።

ነቢዩ (ሰዐወ) በነዚህ ሁለት ሐዲሶች የኢስላምን፣ የኢማንንና የኢህሳንን መሠረቶች አስተምረዋል። ዝርዝርና ቅርንጫፍ ጉዳዮችን አላከሉም። እንዲያውም በመጀመሪያው ሐዲስ ለሙዓዝ ጾምንና ሐጅን አላወሱለትም። ይህን ያደረጉበትን ምክንያት ዑለሞች አብራርተዋል። እዚህ ላይ አስፈላጊ ባለመሆኑ አላወሳሁትም።

በተጨማሪም እምነታዊ ለሆኑ ሁሉም ጉዳዮች ከቁርአን አንዳንድ ወይም ከዚያም በላይ መረጃዎችን ዘርዝሬያለሁ። ይህን ያደረግኩት ተከታዩን የአላህ ትእዛዝ ለመተግበር ነው፡

﴿وَإِنْ أَحَدٌ مِّنَ الْمُشْرِكِينَ اسْتَجَارَكَ فَأَجِرْهُ حَتَّىٰ يَسْمَعَ كَلَامَ اللَّهِ﴾ التوبة: ٦



*«ከአጋሪዎች አንዱ ታስጠጋው ዘንድ ከጠየቀህ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው።»* (አል ተውባህ 6)

ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች የአላህን ቃል ሊሰሙ ይገባል። ምክንያቱም አእምሮን የሚቆጣጠር፣ ልብን የሚገዛ ውበትና ጉልበት አለውና። ብዙ ሰለምቴዎች ለመስለማቸው ምክንያት ከቁርአን ያነበቧቸው አናቅጽ መሆናቸውን ሲናገሩ በብዛት ይሰማሉ።

በአንባቢያን አእምሮ ውስጥ ብዥታን ሊፈጥሩ የሚችሉ አጀንዳዎችን ላለማንሳት ጥንቃቄ አድርጌያለሁ። ለአንዳንድ ብዥታዎች በቀጥታ መልስ ከመስጠት ይልቅ ብዥታዎችን ሊገፉ የሚችሉ የሐይማኖቱን መርሆዎች በማስፈር ብቻ ተወስኛለሁ።

መጽሐፉ ልክ እንደ «ኢትላስ» ቀላልና ቀልጣፋ ይሆን ዘንድም ዝርዝር ውስጥ ከመግባት ተቆጥብያለሁ። ይህ ስራ የሰው ልጅ ጥረት እንደመሆኑ ከስህተት የራቀ፣ ከግድፈት የተጠበቀ ሊሆን አይችልም። ስህተቱ ከኔ ሲሆን፣ ትክክለኛው ከአላህ ነው።

የርሱን ውዴታ በመሻት የተከናወነ ተግባር ያደርገው ዘንድ አላህን እለምናለሁ። ጥረቴን እንዲቀበለኝም እማጸነዋለሁ። ሰፊ ተቀባይነት ያለው ስራ እንዲያደርግልኝም እጠይቀዋለሁ። ከውስጡ ግድፈት ከተገኘ ከኔና ከሸይጧን የመነጨ ነው። አላህ ከስህተትና ከጉድለት የጠራ አምላክ ነውና። የዚህን መጽሐፍ ስህተት ወደ መቀናት ይመልስልኝ ዘንድም እለምነዋለሁ።

በመጨረሻም በዚህ መጽሐፍ ሕትመት፣ የትርጉም ስራና ስርጭት ላይ የተሳተፉ ወገኖችን ሁሉ ከልብ እያመሰገንኩ የበረከተ ምንዳ ይሰጣቸው ዘንድ አላህን እጠይቃለሁ። ጠቃሚ የእውቀትና የተግባር ምንጭ እንዲያደርገውም እማጸነዋለሁ። ይህን ለማድረግ ባለቤቱ እርሱ ብቻ ነውና። ችሎታውም ያለው ከርሱ ብቻ ነው።

የአለማት ጌታ የሆነው አላህ የተመሰገነ ይሁን። በነቢዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልንጀሮቻቸው ሁሉ ላይም የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን።

ደራሲው፡ ዶክተር ሙሐመድ ቢን አብደላህ ቢን ሷሊህ አልሱሐይም

የሙ.ሳ.ቁ. 1032 ሪያድ 11342

# መግቢያ

ምስጋና ለአላህ ይድረሰው። እናመሰግነዋለን። እገዛውን እንጠይቃለን። ምህረቱን እንለምናለን። ከነፍሶቻችን ክፋትና ከመጥፎ ስራዎቻችን በርሱ እንጠበቃለን። አላህ ያቀናውን የሚያጠመው የለም። አላህ ያጠመመውንም የሚያቀናው የለም። ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ። አንድ ነው። አጋር የለውም። ሙሐመድም ባሪያውና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ። የበረከተ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈንባቸው።

አላህ ለሰው ልጆች መልእክተኞችን በየዘመናቱ ልኳል። እዝነት፣ ብርሃንና ፈውስ የሆኑ መጽሐፍትንም አውርዷል። ባለፉት ዘመናት መልእክተኞች የሚላኩት ለየወገኖቻቸው ብቻ ነበር። መጽሐፍቶቻቸውን የመጠበቁ ሐላፊነትም የነርሱ ነበር። እናም መጽሐፍቶቻቸው ከነርሱ ሕልፈት በኋላ ጠፍተዋል። ትምህርቶቻቸው ተበርዘዋል። ተከልሰዋል። ምክንያቱም ለተወሰነ ሕዝብና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የተላኩ ነበሩና።

በአንጻሩ ነቢዩ ሙሐመድን የነብያትና የመልእክተኞች መቋጫ በማድረግ የተለየ ማእረግ ችራቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿ مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ﴾

الأحزاب: ٤٠

*«ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ መካከል የአንዱም አባት አይደለም። ግና (እርሱ) የአላህ መልዕክተኛና የነቢያት መቋጫ ነው።»* (አል አህዛብ 40)

ከመለኮታዊ መጽሐፍት ሁሉ በላጩን ለርሳቸው ሰጠ። እርሱም የተከበረው ቁርአን ነው። ይህን ቅዱስ መጽሐፍ የመጠበቁን ሐላፊነትም ለሰዎች ሳይተው እርሱ ራሱ ወሰደ። አላህ እንዲህ አለ፡

﴿ إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا ٱلذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ۝٩ ﴾ الحجر: ٩



*«መልዕክቱን ያወረድነው እኛ ነን። (ከመበከልም) በእርግጥ እንጠብቀዋለን።»* (አል ሂጅር 9)

ሐይማኖታቸውንም እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ዘላቂ አደረገው። ለዚህ ሸሪዓ ሕልውና ሰበቦች በርሱ ማመንና ወደርሱ መጥራት፣ በሂደቱ የሚያጋጥሙ እንቅፋቶችን መታገስ መሆኑንም ገለጸ። አላህ የነቢዩንና የተከታዮቻቸውን የጥሪ ስልት አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡

﴿ قُلْ هَٰذِهِۦ سَبِيلِىٓ أَدْعُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ ۚ عَلَىٰ بَصِيرَةٍ أَنَا۠ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِى ۖ وَسُبْحَٰنَ ٱللَّهِ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ۝١٠٨ ﴾ يوسف: ١٠٨

*"ይህ ጉዳናዬ ነው። ወደ አላህ ጥሪ አደርጋለሁ። እኔም፣ እኔን የተከተሉ ሁሉም ግልጽ መረጃዎችን ይዘናል። ክብር ለአላህ ይሁን። እኔ ከአጋሪዎች አይደለሁም።" በል* (ዩሱፍ 108)

በአላህ መንገድ በሚደረግ ትግል ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች በትእግስት እንዲያስተናግዱም እንዲህ በማለት አዘዘ።

﴿ فَٱصْبِرْ كَمَا صَبَرَ أُو۟لُوا۟ ٱلْعَزْمِ مِنَ ٱلرُّسُلِ ﴾ الأحقاف: ٣٥

*«(ሙሐመድ ሆይ!) ከመልዕክተኞች የጽናት ባለቤቶች እንደታገሱት ሁሉ ታገስ። »* (አል አህቃፍ 35)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱصْبِرُوا۟ وَصَابِرُوا۟ وَرَابِطُوا۟ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ۝٢٠٠ ﴾ آل عمران: ٢٠٠

*«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ታገሱ። ትእግስታችሁም (ከጠላቶቻችሁ ጽናት) የላቀ ይሁን። (ሕልውናችሁን) በንቃት ጠብቁም። ትድኑ ዘንድም አላህን ፍሩ ...።»* (አል ዒምራን 200)

ይህን ስልት በመጠቀም የአላህን መጽሐፍና የነቢዩን ፈለግ መሠረት አድርጌ ወደ አላህ ሐይማኖት ጥሪ ለማድረግ ይህችን መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ። የፍጡራንን መፈጠር፣ የሰው ልጆችን ልቅና፣ የመልእክተኞችን ለሰው ልጆች መላክና የጥንት ሐይማኖቶችን እጣ ፈንታ ባጭሩ አብራርቻለሁ። በመቀጠልም የእስልምናን ትርጉምና መሠረቶች አብራራሁ። እናም መቅናትን የፈለገ እነሆ መረጃዎቹ በእጆቹ ገብተዋል። መዳን የሚሻ መንገዱን ገልጬለታለሁ።

የነብያትንና የደጋጎችን ፈለግ መከተል የሚሻም እነሆ የተጓዙበትን ጎዳና አሳይቸዋለሁ። ከነርሱ የሸሸ ራሱን አቁለ። የጥመትን መንገድም ተከተለ።

የሌሎች ሐይማኖቶች ተከታዮች ብቸኛ እውነት ነው ብለው ወደ ሚያምኑበት ሐይማኖት ሌሎችን ይጋብዛሉ። የየሐይማኖቶቻቸውን ባለቤቶችና መሪዎች እንዲያልቁና እንዲከተሉም ጥረት ያደርጋሉ።

ሙስሊሞች በበኩላቸው የግለሰብን እምነትና አመለካከት ወደመከተልና ግለሰብን ወደማላቅ ጥሪ አያደርጉም። ምክንያቱም ሐይማኖታቸው በአላህ የተመረጠ ነውና። አላህ እንዲህ አለ፡

﴿ إِنَّ ٱلدِّينَ عِندَ ٱللَّهِ ٱلْإِسْلَٰمُ ﴾ ال عمران: ١٩

*«ከአላህ ዘንድ (ተቀባይነትና ተወዳጅነት ያለው) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው። »* (ዓሊ-ዒምራን 19)

በአላህ ሐይማኖት ውስጥ ሁሉም ሰዎች እኩል ናቸው። አላህን በመፍራት ካልሆነ በቀር አይበላለጡም። እናም የሰው ልጅ የአምላኩን ጎዳና እንዲከተል፣ በመልእክተኞች እንዲያምን፣ የነብያት መቋጫ በሆኑት በነቢዩ ሙሐመድ ላይ ያወረደውንና እርሳቸውንም ለሰው ልጆች እንዲያደርሱት ያዘዛቸውን ሐይማኖት ይከተሉ ዘንድ ሙስሊሞች ሌሎችን እንዲጋብዙ ታዞዋል።

ይህ መጽሐፍ የተጻፈበት አላማም አላህ ለራሱ ወደመረጠውና የመጨረሻውን መልእክተኛ ወደላከበት ሐይማኖት ሰዎችን ለመጋበዝ፣ መቀናትን ለፈለገ መመሪያ፣ ሐሴትን ለፈለገ አመላካች ይሆን ዘንድ ነው። በአላህ እምላለሁ፣ የሰው ልጅ በዚህ ሐይማኖት ካልሆነ በቀር እውነተኛ ደስታን አያገኝም። የአላህን አምላክነት፣ የነቢዩ ሙሐመድን (ሰዐወ) መልእክተኛነት እና እስልምናን እንደ ሐይማኖት ያልተቀበለ ሰው ውስጠ ሰላምን አያውቅም። ጥንትም ሆነ ዛሬ ወደ እስልምና የመጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እውነተኛ ሕይወትን ያወቁት ከሰለሙ በኋላ መሆኑንና እውነተኛ ደስታን የተጎናጸፉት በእስልምና ጥላ ስር መሆኑን መስክረዋል።



ሁሉም ሰዎች ደስታን ለማግኘት፣ ውስጠ ሰላምን ለመጎናጸፍና እውነትን ለማወቅ ጉጉትና ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ ለዚህ ይረዳቸው ዘንድ ይህችን መጽሐፍ አዘጋጅቻለሁ።

ይህን ስራዬን ከርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና ወደርሱ ጎዳና የሚጠራ፣ እንዲሁም በአንባቢያን ዘንድ ተወዳጅና በዚህችም ሆነ በመጭው አለም የሚፈይደኝ በጎ ስራ ያደርግልኝ ዘንድ አላህን እለምነዋለሁ። በየትኛውም ቋንቋ መተርጎምና ማሳተም ለሚሹ ሁሉ መልእክቱን በትክክል የማስተላለፉን አደራ እስከተወጡ ድረስ ሙሉ ፈቃድ ሰጥቻቸዋለሁ።

በመጽሐፉ ላይ አስተያየት ያለው ማንኛውም ወገን ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻዬ አስተያየቱን እንዲልክልኝ አጥብቄ እጠይቃለሁ።

ለአላህ ምንጊዜም የተሟላ ምስጋና ይድረሰው። በይፋም በሚስጥርም ምስጋና ለርሱ ነው። በጅማሬም በፍጻሜም ላይ ምስጋና ለርሱ ነው። ሰማያትን፣ ምድርንና ከአምላካችን ፍጡራን የሚሻውን ሁሉ የሞላ ምስጋና ለርሱ ነው። በነብያችን በሙሐመድ፣ በባልደረቦቻቸውና ፈለጋቸውን በተከተሉ ሁሉ ላይ የበረከተ የአላህ እዝነትና ሰላም እስከ እለተ ቂያማ ድረስ ይስፈንባቸው።

ደራሲው፡ ዶክተር ሙሐመድ ቢን አብደላህ ቢን ሷሊህ አልሱሐይም

ሪያድ 13/10/1420 ሂጅሪያ

የመ.ሳ.ቁ. 1032 ሪያድ 11342

# መንገዱ የት ነው?

የሰው ልጅ በአካልም በአእምሮም እየጎለበተ ሲመጣ በርካታ መሠረታዊ ጥያቄዎች ከአእምሮው ውስጥ ማቃጨላቸው አይቀሬ ነው። ለምሳሌ ከየት መጣሁ? ለምን መጣሁ? ወደየት እሄዳለሁ? እኔንም ሆነ በዙሪያየ የሚገኘውን ዓለም የፈጠረ ማን ነው? የዚህ ዓለም ባለቤትና አስተዳዳሪ ማን ነው? የሚሉና መሰል መሠረታዊ ጥያቄዎችን ይጠይቃል።

የሰው ልጅ ብቻውን ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት አይችልም። ዘመናዊ ሳይንስም ለእነዚህ ጥያቄዎች ምንጊዜም ምላሽ የመስጠት አቅም የለውም። ምክንያቱም እነዚህ ጥያቄዎች ሐይማኖት በሚባለው መስክ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸውና። ይህም በመሆኑ ለነዚህ ጥያቄዎች የሚሰጡ ምላሾች የተለያዩና ብዙ፣ እንዲሁም ከአፈ ታሪክና እንቶ ፈንቶ እምነቶች ጋር የተቀላቀሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህም ሁኔታ የሰውን ልጅ ግራ መጋባት ይበልጥ ጨመረው።

የሰው ልጅ ለነዚህና ለሌሎችም የሕይወት እንቆቅልሾች ትክክለኛና ቁርጥ ያለ ምላሽ ሊያገኝ ወደሚችልበት እውነተኛ ሐይማኖት አላህ እስካልመራው ድረስ ግራ መጋባቱ ምንጊዜም ይቀጥላል። ምክንያቱም እነዚህ ጥያቄዎች ከሩቅ ሚስጥር ውስጥ የሚመደቡ ሲሆኑ ትክክለኛ ምላሻቸው የሚገኘውም ከእውነተኛ ሐይማኖት ውስጥ ብቻ ነው። ለነብያት በወሕይ የገለጸላቸው ብቸኛ እውነት እርሱ ነውና።

እናም የሰው ልጅ እውነተኛውን ሐይማኖት አፈላልጎ ሊያገኝ፣ አግኝቶም ሊማረውና ሊያምንበት ይገባል። ይህ ሲሆን ግራ መጋባቱ ይወገዳል። ብዥታው ይገፈፋል። ቀጥተኛውን ጎዳናም ይከተላል።

በቀጣዮቹ ገጾች ወደ ቀጥተኛ ጎዳና እጠራሐለሁ። ጠንካራ ማስረጃዎችንም አቀርብልሐለሁ። በጥሞና እንድታስተውላቸውም እጋብዝሐለሁ።



# የአምላክ ሕልውናና አንድነት

ከሐድያን ፍጡራንን፣ ማለትም እንጨት፣ ድንጋይ፣ ዛፍና ሰው ወዘተ ያመልካሉ። ይህም በመሆኑ አይሁዶችና ጣኦት አምላኪዎች ነቢዩ ሙሐመድን ስለ እውነተኛው አምላክ ባህሪያት እንዲያብራሩላቸው በጠየቁ ጊዜ ከአላህ (ሱወ) እንዲህ የሚል ምላሽ ተሰጥቷቸዋል፡

﴿ قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ۝١ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ۝٢ لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ۝٣ وَلَمْ
يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ﴾ الإخلاص: ١ - ٤

*«እርሱ አላህ አንድ ነው። አላህ (የፍጡራን) የበላይ ገዥና መጠጊያ ነው። አልወለደም፣ አልተወለደምም። አንድም ቢጤ የለውምም በል።» (አል ኢኽላስ)*

አላህ ለባሮቹ ራሱን እንዲህ ሲል አስተዋውቋል።

﴿ إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ
يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ يَطْلُبُهُۥ حَثِيثًا وَٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتٍۭ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ أَلَا لَهُ ٱلْخَلْقُ
وَٱلْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ۝٥٤ ﴾ الأعراف: ٥٤

*«ጌታችሁ አላህ ያ ሰማያትን በስድስት ቀናት የፈጠረ ነው። ከዚያም ከዙፋኑ ላይ ተሰየመ። ቀኑንም በሌሊቱ ያሸፍነዋል። በፍጥነት ይፈላለጋሉ። ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት በትእዛዙ የተገሩ ናቸው። አዋጅ፣ መፍጠርም ማዘዝም የርሱ (ሥልጣንና መብት) ነው። የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ ላቀ።»* (አል አዕራፍ 54)

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِى رَفَعَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ بِغَيْرِ عَمَدٍ تَرَوْنَهَا ۖ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ ۖ وَسَخَّرَ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ ۖ كُلٌّ
يَجْرِى لِأَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ يُدَبِّرُ ٱلْأَمْرَ يُفَصِّلُ ٱلْءَايَٰتِ لَعَلَّكُم بِلِقَآءِ رَبِّكُمْ تُوقِنُونَ ۝٢ وَهُوَ ٱلَّذِى
مَدَّ ٱلْأَرْضَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَٰسِىَ وَأَنْهَٰرًا ۖ وَمِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ جَعَلَ فِيهَا زَوْجَيْنِ ٱثْنَيْنِ ۖ يُغْشِى ٱلَّيْلَ
ٱلنَّهَارَ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ۝٣ وَفِى ٱلْأَرْضِ قِطَعٌ مُّتَجَٰوِرَٰتٌ وَجَنَّٰتٌ مِّنْ
أَعْنَٰبٍ وَزَرْعٌ وَنَخِيلٌ صِنْوَانٌ وَغَيْرُ صِنْوَانٍ يُسْقَىٰ بِمَآءٍ وَٰحِدٍ وَنُفَضِّلُ بَعْضَهَا عَلَىٰ بَعْضٍ فِى
ٱلْأُكُلِ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ۝٤ ۞ وَإِن تَعْجَبْ فَعَجَبٌ قَوْلُهُمْ
أَءِذَا كُنَّا تُرَٰبًا أَءِنَّا لَفِى خَلْقٍ جَدِيدٍ ۗ أُو۟لَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِرَبِّهِمْ ۖ وَأُو۟لَٰٓئِكَ ٱلْأَغْلَٰلُ فِىٓ

أَعْنَاقِهِمْ وَأُولَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٥﴾ وَيَسْتَعْجِلُونَكَ بِٱلسَّيِّئَةِ قَبْلَ
ٱلْحَسَنَةِ وَقَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِمُ ٱلْمَثُلَٰتُ وَإِنَّ رَبَّكَ لَذُو مَغْفِرَةٍ لِّلنَّاسِ عَلَىٰ ظُلْمِهِمْ وَإِنَّ
رَبَّكَ لَشَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ﴿٦﴾ وَيَقُولُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا لَوْلَآ أُنزِلَ عَلَيْهِ ءَايَةٌ مِّن رَّبِّهِۦٓ إِنَّمَآ أَنتَ
مُنذِرٌ وَلِكُلِّ قَوْمٍ هَادٍ ﴿٧﴾ ٱللَّهُ يَعْلَمُ مَا تَحْمِلُ كُلُّ أُنثَىٰ وَمَا تَغِيضُ ٱلْأَرْحَامُ وَمَا
تَزْدَادُ وَكُلُّ شَىْءٍ عِندَهُۥ بِمِقْدَارٍ ﴿٨﴾ ﴾ الرعد: ٢ - ٨

«አላህ ያ ሰማያትን -የምታዩት ምሰሶ ሳይኖር -ከፍ ያደረገ፣ ከዚያም ከዙፋኑ ላይ የተሰየመ (አምላክ) ነው። ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ ነው። ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ (በየምህዋራቸው) ይጓዛሉ። ነገሮችን ሁሉ ያስተናብራል (ይመራል)። አንቀጾቹንንም ያብራራል። ጌታችሁን መገናኘታችሁ የማይቀር መሆኑን በእርግጥ ታምኑ ዘንድ (ይህን ያደርጋል)። እርሱ ያ ምድርን የዘረጋ፣ ከበላይዋም ጋራዎችንና ወንዞችን ያደረገ፣ ጥንድ ጥንድ የሆኑ ፍራፍሬዎችንም ያደረገባት (አምላክ) ነው። ቀኑንም በሌሊት ይሸፍናል። እነዚህ ለሚያስተነትኑ ሰዎች (ድንቅ) ተአምራት ናቸው። በምድር ላይ ጉረቤታሞች የሆኑ (ግና እየቅል የሆነ ባሕሪ ያላቸው) ቁርጥራጭ መሬቶች አሉ። ከወይን የሆኑ የአትክልት ሥፍራዎችም፣ አዝርዕቶችም፣ መንታዎች የሆኑም መንታዎች ያልሆኑም የዘንባባ ተክሎች አሉ። (ሁሉም) አንድ ዓይነት ውሃ እንዲጠጡ ይደረጋል። ግና የከፊሎችን ጣእም ከከፊሎቹ (የተለየ እና) የተሻለ እናደርጋለን። እነኝህ ለአስተዋዮች (ድንቅ) ተአምራት ናቸው። መገረም ካለብህ ከምንም ነገር በላይ እጅግ የሚያስገርመው (ከሓዲያን) "አፈር ከሆንን በኋላ እንደ አዲስ እንፈጠራለንን?" ማለታቸው ነው። እነዚህ (ይህን ያሉት) ከጌታቸው የካዱት ናቸው። እነርሱ በእርግጥም ከአንገቶቻቸው ላይ ካቴናዎች ያሉባቸው ናቸው። እነርሱ በእርግጥም የእሳት ሰዎች ናቸው። ከውስጧም ዝንተ ዓለም ይኖራሉ። ከነርሱ በፊት ቅጣቶች (የወረዱባቸው በርካታ ሕዝቦች) ማለፋቸው እየታወቀ ከበጎው ይልቅ በክፋው ያቻኩሉሃል። ግና ጌታህ ሰዎችን በደላቸውን ይምራል። ጌታህ ቅጣተ ብርቱም ነው። እነዚያ የካዱት፡- "ከጌታው ዘንድ ለምን ተአምር አልወረደለትም?" ይሉሃል። አንተ አስጠንቃቂ ብቻ ነህ። ሁሉም ሕዝቦች መሪ (መልዕክተኛ) አላቸው። አላህ እያንዳንዷ ሴት ያረገዘችውን፣ ማኅፀኖች የሚያጉድሉትን፣ የሚጨምሩትንም ጠንቅቆ ያውቃል። ከርሱ ዘንድ ሁሉም ነገር በልክ (መጠኑ የተወሰነ) ነው።» (አል ረእድ 2-8)

﴿ قُلْ مَن رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ قُلِ ٱللَّهُ قُلْ أَفَٱتَّخَذْتُم مِّن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءَ لَا يَمْلِكُونَ لِأَنفُسِهِمْ نَفْعًا وَلَا
ضَرًّا قُلْ هَلْ يَسْتَوِى ٱلْأَعْمَىٰ وَٱلْبَصِيرُ أَمْ هَلْ تَسْتَوِى ٱلظُّلُمَٰتُ وَٱلنُّورُ أَمْ جَعَلُوا لِلَّهِ شُرَكَآءَ



خَلَقُوا كَخَلْقِهِۦ فَتَشَٰبَهَ ٱلْخَلْقُ عَلَيْهِمْ قُلِ ٱللَّهُ خَٰلِقُ كُلِّ شَىْءٍ وَهُوَ ٱلْوَٰحِدُ ٱلْقَهَّٰرُ ﴿١٦﴾ ﴾ الرعد:
١٦

«የሰማያትና የምድር ጌታ ማን ነው? በላቸው። አላህ ነው፣ በላቸውም። ከርሱ ሌላ፣ ራሳቸውን መጥቀምም ሆነ መጉዳት የማይችሉ (የሐሰት አማልክትን) ረዳት አድርጋችሁ ያዛችሁን? በላቸው። እውርና ዓይናማ እኩል ናቸውን? ጨለማዎችስ ከብርሃን ጋር እኩል ናቸውን? በላቸውም። ወይስ የርሱን (የአላህን) ፍጡራን የሚመስሉ (ነገሮች) የፈጠሩ (አማልክትን) ለአላህ ተጋሪ አደረጉለትን? እናም ፍጡራኑ ተመሳሰለባቸውን? የሁሉም ፈጣሪ አላህ ብቻ ነው። እርሱ አንድና ኃያል የሆነ አምላክ ነውና።" በላቸው።» (አል ረእድ 16)

ስለርሱ ሕልውናና አንድነት የሚመሰክሩ ተአምራቱን ሲገልጽ፡-

﴿ وَمِنْ ءَايَٰتِهِ ٱلَّيْلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمْسُ وَٱلْقَمَرُ لَا تَسْجُدُوا لِلشَّمْسِ وَلَا لِلْقَمَرِ
وَٱسْجُدُوا لِلَّهِ ٱلَّذِى خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمْ إِيَّاهُ تَعْبُدُونَ ﴿٣٧﴾ فَإِنِ ٱسْتَكْبَرُوا
فَٱلَّذِينَ عِندَ رَبِّكَ يُسَبِّحُونَ لَهُۥ بِٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ وَهُمْ لَا يَسْـَٔمُونَ ۩ ﴿٣٨﴾ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنَّكَ
تَرَى ٱلْأَرْضَ خَٰشِعَةً فَإِذَآ أَنزَلْنَا عَلَيْهَا ٱلْمَآءَ ٱهْتَزَّتْ وَرَبَتْ إِنَّ ٱلَّذِىٓ أَحْيَاهَا لَمُحْىِ ٱلْمَوْتَىٰٓ إِنَّهُۥ
عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٣٩﴾ ﴾ فصلت: ٣٧ - ٣٩

«ሌሊትና ቀን፣ ፀሐይና ጨረቃ ከተአምራቱ ናቸው። ለፀሐይም ሆነ ለጨረቃ አትስገዱ። ለዚያ ለፈጠራቸው (አምላክ) -ለአላህ (ብቻ) ስገዱ- እርሱን ብቻ የምታመልኩ ከሆናችሁ። (ከሓድያን አላህን ከማምለክ) ቢኮሩ (ከልዕልናው የሚቀንሱት ነገር የለም)። እነዚያ ከጌታህ ዘንድ ያሉት (ፍጡራን) እርሱን በቀንም በሌሊትም ያወድሱታል። እነርሱ ፈጽሞ አይሰለቹም። ምድርን ደረቅ ሆና ማየትህም ከተአምራቱ (አንዱ) ነው። በርሷ ላይ ውሃ ባወረድን ጊዜ (በቡቃያዎችዋ) ነፍስ ትዘራለች። ትለመልማለችም። ያ እርሷን ሕያው ያደረጋት አምላክ በእርግጥም ሙታንን ሕያው ያደርጋል። እርሱ ሁሉንም ነገር መፈፀም ይችላል።» (ፉሲለት 37-39)

﴿ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ خَلْقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفُ أَلْسِنَتِكُمْ وَأَلْوَٰنِكُمْ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ
لَءَايَٰتٍ لِّلْعَٰلِمِينَ ﴿٢٢﴾ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ مَنَامُكُم بِٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱبْتِغَآؤُكُم مِّن فَضْلِهِۦٓ إِنَّ فِى
ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَسْمَعُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾ الروم: ٢٢ - ٢٣

*«የሰማያትና የምድር መፈጠር፣ ቋንቋችሁና ቀለማችሁ መለያየቱም ከተአምራቱ ነው። በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ተአምራት አለ። በሌሊትም በቀንም መተኛታችሁ፣ ከችሮታው መፈለጋችሁ ከተአምራቱ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሰዎች ተአምራት አለ።» (አል ሩም 22-23)*

ራሱንም ሙሉ በሆኑ ባህሪያት ገልጿል፡-

﴿ اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْحَيُّ الْقَيُّومُ ۚ لَا تَأْخُذُهُ سِنَةٌ وَلَا نَوْمٌ ۚ لَهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ ۗ مَن ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِندَهُ إِلَّا بِإِذْنِهِ ۚ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ ۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَيْءٍ مِّنْ عِلْمِهِ إِلَّا بِمَا شَاءَ ۚ وَسِعَ كُرْسِيُّهُ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ ۖ وَلَا يَئُودُهُ حِفْظُهُمَا ۚ وَهُوَ الْعَلِيُّ الْعَظِيمُ (٢٥٥) ﴾ البقرة: ٢٥٥

*«አላህ (ብቸኛ አምላክ ነው፤) ከርሱ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። ሕያውና ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅ ልፍም አይዘውም። በሰማይም በምድርም ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉ የርሱ ናቸው። ከርሱ ዘንድ ያለርሱ ፈቃድ የሚያማልድ ማን ነው? (ፍጡራን) በዚህችም ሆነ በቀጣዩ ዓለም የሚገጥሟቸውን ነገሮች ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል። እርሱ የፈቀደውን ያህል ቢሆን እንጅ ከእውቀቱ ቅንጣት ያህሉን አይደርሱበትም። ዙፋኑ ከሰማያትና ከምድር ሰፋ። እነርሱን (ሰማያትንና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው ያሉ ፍጡራንን) መጠበቅ አይሳነውም። ከፍ ያለና ልዑል (አምላክ) ነው።»* (አል በቀራህ 255)

﴿ غَافِرِ الذَّنبِ وَقَابِلِ التَّوْبِ شَدِيدِ الْعِقَابِ ذِي الطَّوْلِ ۖ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ۖ إِلَيْهِ الْمَصِيرُ (٣) ﴾

غافر: ٣

*«ኃጢአትን መሐሪ፣ ንስሐን ተቀባይ፣ ቅጣተ ብርቱ፣ የልግስናም ባለቤት። ከርሱ ውጭ ሌላ አምላክ የለም። መመለሻም ወደርሱ ብቻ ነው።» (ጋፊር 3)*

እንዲሁም ብሏል፡-

﴿ هُوَ اللَّهُ الَّذِي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْمَلِكُ الْقُدُّوسُ السَّلَامُ الْمُؤْمِنُ الْمُهَيْمِنُ الْعَزِيزُ الْجَبَّارُ الْمُتَكَبِّرُ ۚ سُبْحَانَ اللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ (٢٣) ﴾ الحشر: ٢٣



*«አላህ ከርሱ ውጭ ሌላ አምላክ የሌለ የሆነ፣ ንጉሥ፣ ከጉድለት ሁሉ የጠራ፣ የሰላም ምንጭ፣ የእምነት የበላይ ጠባቂ፣ ባሮቹን ተቆጣጣሪ፣ አሸናፊ፣ ኃያልና ኩሩ (አምላክ) ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።»* (አልሐሽር 23)

ይህ ጥበበኛና ሐያል አምላክ ራሱን ለሰው ልጆች በሚገባ አስተዋውቋል። ማንነቱን የሚመሰክሩ ተአምራትን ገልጿል። ምሉእ የሆኑ ባህሪያቱንም ዘርዝሯል። ስለ ሕልውናውና አምላክነቱ የነብያት ሁሉ ትምህርቶች፣ የአእምሮ ምርምሮች፣ ንጹህ የሰው ልጅ ተፈጥሮ፣ ተፈጥሯዊ ስሜቶች ሁሉ መስክረዋል። ሁሉም ሕዝቦች በዚህ እውነታ ላይ ተስማምተዋል። ከዚህ ውስጥ ጥቂቱን ቀጥሎ አብራራለሁ። ሕልውናውንና አምላክነቱን ከሚያሳዩ መረጃዎች መካከል ተከታዮቹ ይገኙበታል።

## 1) የፍጥረተ ዓለሙ ድንቅ አፈጣጠር

በዚህ ድንቅ ፍጥረተ አለም ተከባሐል። ሰማያቱ፣ ከዋክብቱ፣ ምህዋራቱ፣ የተዘረጋች ምድር፣ ልዩ ልዩ እጽዋት፣ በጥንድ የተዋቀሩ ፍጡራን ምድርን ሞልተዋታል። እናም ይህ ፍጥረተ አለም ራሱን አልፈጠረም። ሊፈጥርም አይቻለውም። ተመልካችን የሚያስደምም ድንቅና የተሟላ ስርዓቱን ያስገኘው፣ ባስተዋይም ተአምር ያደረገው ሐያልና ብቸኛ የሆነ አምላክ እንጅ ሌላ አይደለም፡-

﴿ أَمْ خُلِقُوا مِنْ غَيْرِ شَيْءٍ أَمْ هُمُ الْخَالِقُونَ (٣٥) أَمْ خَلَقُوا السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ ۚ بَل لَّا يُوقِنُونَ (٣٦) ﴾ الطور: ٣٥ - ٣٦

*«ከምንም ነው የተፈጠሩት? ወይስ እነርሱ ራሳቸውን ፈጣሪዎች ናቸው? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጥረዋል? አይደለም፣ በእውነቱ እነርሱ ጽኑ እምነት የላቸውም።» (ጡር 35-36)*

እነዚህ ሁለት አናቅጽ ሦስት ወሳኝ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ።

1) የሰው ልጅ ከምንም ተገኘን?

2) ራሱን ፈጠረን?

3) ሰማያትንና ምድርንስ ፈጠረን?

የሰው ልጆች ከምንም አለመገኘታቸውና ራሳቸውንም አለመፍጠራቸው፣ እንደዚሁም ሰማያትንና ምድርን አለማስገኘታቸው እውነት ከሆነ ፈጣሪ መኖሩ እርግጥ ሆነ ማለት ነው። እነርሱንም ሆነ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ አምላክ አለ። እርሱም ሐያልና ብቸኛ የሆነው አላህ ነው።

## 2) ተፈጥሮ

ፍጡራን በአፈጣጠራቸው የፈጣሪን መኖር ያጸድቃሉ። አምላክ ከሁሉም ነገር የላቀ፣ የከበረና ምሉእ መሆኑን ይረዳሉ። ይህ እውነታ ከአራቱ የሂሳብ መደቦች ይበልጥ ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ በጥልቀት የሰረጸ ነው። ተፈጥሯዊ ስሜቱ ለተበረዘና ለተቀየረ ሰው ካልሆነ በቀር መረጃ እንኳ አያስፈልጋቸውም። አላህ እንዲህ ብሏል[2]፡

﴿ فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ اللَّهِ الَّتِي فَطَرَ النَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ اللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾ ﴾ الروم: ٣٠

*«ፊትህን ወደ (ትክክለኛው) "ዲን" (ሃይማኖት) አዙር። በርሱ ላይም ጽና። (ይህ) አላህ የሰው ልጆችን የፈጠረበት ተፈጥሯዊ መንገድ (ዲን) ነው። የአላህን ፍጡር አትለውጡ። ይህ ቀጥተኛው ሃይማኖት ነው፤ ግና ብዙዎቹ ሰዎች (ይህን) አያውቁም።»* (አል ሩም 30)

የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡

«እያንዳንዱ ሕጻን ተፈጥሯዊውን ሐይማኖት እንደያዘ ይወለዳል። ከዚያ በኋላ ወላጆቹ አይሁድ፣ ክርስትያን ወይም መጁስ ያደርጉታል። እንደበት እልባ እንስሳት እንደበት እልባ እንስሳትን እንደሚወልዱት ማለት ነው። ባለ እንደበት ይወልዳሉ ብላችሁ ታስባላችሁን?»

አቡ ሁረይራም እንዲህ አሉ፡ ካሻችሁ ተከታዩን የአላህ ቃል አንብቡ።

﴿ فِطْرَتَ اللَّهِ الَّتِي فَطَرَ النَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ اللَّهِ ۚ ﴾ الروم: ٣٠

*«(ይህ) አላህ የሰው ልጆችን የፈጠረበት ተፈጥሯዊ መንገድ (ዲን) ነው። የአላህን ፍጡር አትለውጡ።»* (አል ሩም 30)

[2] ኢብን ተይሚያህ. መጅሙዓል ፈታዋ 1/47፣ 49፣ 73



መልእክተኛው እንዲህም ብለዋል፡

«አዋጅ፣ አምላኬ ዛሬ ያስተማረኝንና እናንተ የማታውቁትን እውነት አስተምራችሁ ዘንድ አዘዘኝ። እርሱም ፡

«ሁሉንም ባሮቼን በቀጥተኛው ሐይማኖት ላይ ፈጠርኳቸው። ግና ሰይጣናት መጡና ከሐይማኖታቸው አስወጧቸው። የፈቀድኩላቸውን እርም አደረጉባቸው። ያለኔ ፈቃድ በኔ ላይ ሌላን አካል እንዲያጋሩም አደረጓቸው።» (አህመድና ሙስሊም)

## 4) የሕዝቦች የጋራ ስምምነት

ጥንትም ሆነ ዛሬ የሰው ልጆች ለዚህ ፍጥረተ ዓለም ፈጣሪ እንዳለው በአንድ ድምጽ ያጸድቃሉ። ይህም አምላክ የዓለማት አምላክ፣ የሰማያትና የምድር ፈጣሪ እንደሆነም ያውቃሉ። በመፍጠሩም በንግስናውም አጋር እንደሌለው ይረዳሉ።

ሕዝቦች የሚያመልኳቸው ከአላህ ሌላ ያሉ የሐሰት አማልክት ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር የአምላክ አጋር እንደሆኑ የሚያምን አንድም ሕዝብ በታሪክ አይታወቅም። ሁሉም ሕዝቦች የነርሱም ሆነ የሐሰት አማልክቶቻቸው ፈጣሪ አላህ እንደሆነ፣ ፈጣሪም፣ ከልካይም ለጋሽም እርሱ መሆኑን፣ ጥቅምና ጉዳት በእርሱ እጅ መሆናቸውን ያውቃሉ። አላህ ጣኦታውያን ፈጣሪነቱን ያምኑ እንደነበር ሲናገር እንዲህ ብሏል፡

﴿ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ وَسَخَّرَ الشَّمْسَ وَالْقَمَرَ لَيَقُولُنَّ اللَّهُ ۖ فَأَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ ﴿٦١﴾ اللَّهُ يَبْسُطُ الرِّزْقَ لِمَن يَشَاءُ مِنْ عِبَادِهِ وَيَقْدِرُ لَهُ ۚ إِنَّ اللَّهَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ ﴿٦٢﴾ ﴾ العنكبوت: ٦١ - ٦٢

*«ሰማያትንና ምድርን ማን እንደፈጠረ፣ ጸሐይንና ጨረቃንም ማን እንደገራ ብትጠይቃቸው። "አላህ ነው።" ይላሉ። ታዲያ እንዴት (ከእውነት) ይሸሻሉ። አላህ ከባሮቹ ለሚሻው ሲሳይን ያሰፋል። (ለሚሻውም) ያጠባል። አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ ነው።*

﴿ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ لَيَقُولُنَّ خَلَقَهُنَّ الْعَزِيزُ الْعَلِيمُ ﴿٩﴾ ﴾ الزخرف: ٩

*«ሰማያትንና ምድርን ማን እንደፈጠረ ብትጠይቃቸው፡- "አሸናፊውና ዐዋቂው (አምላክ) ፈጠራቸው።" የሚል ምላሽ በእርግጥም ይሰጡሃል።» (አል ዙኽሩፍ 9)*

## 5) አእምሮ

የሰው ልጅ አእምሮም ይህ ፍጥረተ ዓለም አንድ ትልቅ ፈጣሪ እንዳለው ያጸድቃል። ምክንያቱም ፍጥረተ ዓለሙ አዲስ ፍጡር እንደሆነና ራሱን እንዳልፈጠረ ያውቃል። ፍጡር የግድ ፈጣሪ ያስፈልገዋል።

የሰው ልጅ አንዳች መከራ ሲያገኘው፣ እርሱ ባለው አቅም መከላከል ከተሳነው ቀልቡ ወደ አምላክ ይዞራል። የርሱን እገዛ ይጠይቃል። ጭንቀቱን እንዲያነሳለት ይማጸነዋል። በሰላማዊው ቀን አምላክን ክዶና ዘንግቶ፣ ጣኦታትን የሚያመልክ እንኳ በጭንቅ ሰአት ይህን ያደርጋል። የሰው ልጅ ቀርቶ እንስሳ እንኳ አንዳች ጭንቀት ሲያገኘው ራሱን ወደ ሰማይ ያቀናል። የሐሰት አማልክቱን ይረሳል። አላህ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَإِذَا مَسَّ ٱلْإِنسَـٰنَ ضُرٌّ دَعَا رَبَّهُۥ مُنِيبًا إِلَيْهِ ثُمَّ إِذَا خَوَّلَهُۥ نِعْمَةً مِّنْهُ نَسِىَ مَا كَانَ يَدْعُوٓا۟ إِلَيْهِ مِن قَبْلُ وَجَعَلَ لِلَّهِ أَندَادًا ﴾ الزمر: ٨

*«የሰው ልጅ አንዳች ችግር ባገኘው ጊዜ ጌታውን ወደርሱ በዐት ተመልሶ ይማፀናል። ከዚያም ከርሱ የሆነን ፀጋ ሲለግሰው ያን ከዚያ በፊት ይማፀነው የነበረውን ይዘነጋል። ለአላህም ባላንጣዎች ያደርጋል፤» (አል ዙመር 8)*

የጣኦታውያንን ባህሪ በተመለከተም ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

﴿ هُوَ ٱلَّذِى يُسَيِّرُكُمْ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ حَتَّىٰٓ إِذَا كُنتُمْ فِى ٱلْفُلْكِ وَجَرَيْنَ بِهِم بِرِيحٍ طَيِّبَةٍ وَفَرِحُوا۟ بِهَا جَآءَتْهَا رِيحٌ عَاصِفٌ وَجَآءَهُمُ ٱلْمَوْجُ مِن كُلِّ مَكَانٍ وَظَنُّوٓا۟ أَنَّهُمْ أُحِيطَ بِهِمْ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ لَئِنْ أَنجَيْتَنَا مِنْ هَـٰذِهِۦ لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلشَّـٰكِرِينَ ﴿٢٢﴾ فَلَمَّآ أَنجَىٰهُمْ إِذَا هُمْ يَبْغُونَ فِى ٱلْأَرْضِ بِغَيْرِ ٱلْحَقِّ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّمَا بَغْيُكُمْ عَلَىٰٓ أَنفُسِكُم مَّتَـٰعَ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ثُمَّ إِلَيْنَا مَرْجِعُكُمْ فَنُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾ يونس: ٢٢ - ٢٣



*«እርሱ በየብስም በባሕርም እንድትጓዙ ያስቻላችሁ (አምላክ) ነው። በመርከቦችም ውስጥ በሆናችሁ ጊዜ (መርከቦች) እነርሱን (ተጓዦችን) ተሸክመው በመልካም ነፋስ እንዲጓዙ እናደርጋለን። (ተሳፋሪዎችም በጉዟቸው) ይደሰታሉ። በድንገትም ኃይለኛ ነፋስ መጥቶባቸው (በመከራ) መከበባቸውን እርግጠኛ ሲሆኑ አላህን፡- "ከዚህ (መከራ) ካዳንከን ከአመስጋኞች እንሆናለን።" በማለት በፍፁም ቅንነትና ታማኝነት ይማፀናሉ። ግና (ከመከራው) ባዳናቸው ጊዜ ምድር ላይ ያለአግባብ ወሰንን ይጥሳሉ። የሰው ልጅ ሆይ! በአመጻችሁ ተጉጂዎቹ እናንተው ናችሁ። በዚህች ዓለም ተድላና ሐሴት (ተጠቀሙ)። ከዚያም መመለሻችሁ ወደኛ ነው። ትሠሩት የነበረውን (ሁሉም) እንነግራችኋለን።» (ዩኑስ 22-23)*

﴿ وَإِذَا غَشِيَهُم مَّوْجٌ كَٱلظُّلَلِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ فَمِنْهُم مُّقْتَصِدٌ وَمَا يَجْحَدُ بِـَٔايَـٰتِنَآ إِلَّا كُلُّ خَتَّارٍ كَفُورٍ ﴿٣٢﴾ ﴾ لقمان: ٣٢

*«እንደ ጥላዎች የሆነ ማዕበል በሸፈናቸው ጊዜ አላህን በፍፁም ቅንነትና ታዛዥነት ይማፀናሉ። ወደየብስ በሰላም ባዘለቃቸው ጊዜ ከነርሱ መካከል የአምላኩን ውለታ የማይረሳ (አመስጋኝ) አለ። (ከሓዲም አለ)። በአንቀጾቻችን፣ አታላዮችና ከዳተኞች እንጂ፣ ሌላ ማንም አይክድም።» (ሉቅማን 32)*

ፍጡራንን ካልነበሩበት ያስገኘ፣ የሰውን ልጅ እጅግ ባማረ ሁኔታ የፈጠረ፣ በተፈጥሮው ውስጥ እርሱን የማምለክና ለእርሱ እጅ የመስጠት ስሜት ያኖረ፣ አእምሮዎች አምላክነቱን ያጸደቁለት፣ ሕዝቦች በጌታነቱ የተስማሙለት ይህ አምላክ ፍጡራንን በመፍጠር እና በመንከባከብ ብቸኛ እንደሆነ ሁሉ በመመለክም ብቸኛ ሊሆን እንደሚገባ አያሌ መረጃዎች ያረጋግጣሉ። ከብዙ በጥቂቱ፡-

1) በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ከአንድ አምላክ ውጭ ሌላ የለም። ፈጣሪም መጋቢም እርሱ ብቻ ነው። ጥቅምም ሆነ ጉዳት የሚሰጠው እርሱ ብቻ ነው። በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ሌላ አምላክ ቢኖር ኖሮ የመፍጠር፣ የመስጠትና የማዘዝ ስልጣን ይኖረው ነበር። ሁለቱ አማልክትም በስልጣን ይጣሉ ነበር። እናም አንዱ እስኪያሸንፍ ድረስ ይፋለማሉ። ተሸናፊው አምላክ ሊሆን አይችልም። እውነተኛ አምላክ አሸናፊው ብቻ ነው። ይህውም አምላክ በአምላክነቱ ተጋሪ አይሻም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

*በትእዛዙ ገራላችሁ። ወንዞችንም ገራላችሁ። ፀሐይንና ጨረቃንም፣ ዘወትር ተጓ ገሮች አድርጐ፣ ገራላችሁ። ሌትንና ቀንንም ገራላችሁ። (ለሕይወት) የሚያስፈልጋችሁንም ነገሮች ሁሉ ሰጥቷችኋል። የአላህን ፀጋዎች ቁጥራችሁ አትዘልቋቸውም። የሰው ልጅ በእርግጥም በዳይ፣ ከሓዲ ነው።» (ኢብራሂም 32-34)*

2) **ለአምላክነቱ ምስክር፡-** ሰማያትና ምድር እንዲሁም ሌሎች ፍጡራን የአላህን አምላክነት ያረጋግጣሉ። አንድነቱን ይመሰክራሉ። እነሆ በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር የአላህን ሕልውና፣ አምላክነትና አንድነት ማጽደቅና ማመን ነው። ይህ እምነት ትልቅ ቁም ነገር በመሆኑ ትልቅ እማኝና መረጃ አበጅቶለታል። ግዙፍ ተአምር አኑሮለታል። በጠንካራ አስረጅ አጽንቶታል። ሰማያትንና ምድርን እንደዚሁም ሌሎች ፍጡራንን ለዚህ ቁም ነገር ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ አበጅቷቸዋል። ይህም በመሆኑ በቁርአን ውስጥ «ከተአምራቱ ነው» (ወሚን አያቲሂ) የሚሉ ሃረጎችን በተደጋጋሚ እናገኛለን። ለምሳሌ፡-

﴿ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ خَلْقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَٱخْتِلَٰفُ أَلْسِنَتِكُمْ وَأَلْوَٰنِكُمْ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّلْعَٰلِمِينَ ﴿٢٢﴾ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ مَنَامُكُم بِٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱبْتِغَآؤُكُم مِّن فَضْلِهِۦٓ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَسْمَعُونَ ﴿٢٣﴾ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ يُرِيكُمُ ٱلْبَرْقَ خَوْفًا وَطَمَعًا وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَيُحْىِۦ بِهِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَآ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿٢٤﴾ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَن تَقُومَ ٱلسَّمَآءُ وَٱلْأَرْضُ بِأَمْرِهِۦ ۚ ثُمَّ إِذَا دَعَاكُمْ دَعْوَةً مِّنَ ٱلْأَرْضِ إِذَآ أَنتُمْ تَخْرُجُونَ ﴿٢٥﴾ ﴾ الروم: ٢٢ - ٢٥

*«የሰማያትና የምድር መፈጠር፣ ቋንቋችሁና ቀለማችሁ መለያየቱም ከተአምራቱ ነው። በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ተአምራት አሉ። በሌሊትም በቀንም መተኛታችሁ፣ ከችሮታው መፈለጋችሁ ከተአምራቱ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ሰዎች ተአምራት አሉ፡ ብልጭታንም በፍርሃትና በተስፋ (ስሜት) እንድታዩ ማድረጉ፣ ከሰማየትም ውሃ ማውረዱና በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ማድረጉ ከተአምራቱ ነው። በዚህ ውስጥ ለአስተዋዮች ተአምራት አሉ፡ ሰማያትና ምድር በትእዛዙ መቆማቸው፣ ከምድርም ጥሪ*



*ባደረገላችሁ ጊዜ ወዲያውኑ የምትወጡ መሆናችሁ ከተአምራቱ ነው።» (አል ሩም 22-25)*

3) **ከሞት መነሳት ለመኖሩ መረጃ እንዲሆኑ፡-** ሕይወት ሁለት እርከን አላት። የዚህች አለምና የመጭው አለም። እውነተኛ ሕይወት የመጭው ዓለም ሕይወት ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَا هَٰذِهِ ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَآ إِلَّا لَهْوٌ وَلَعِبٌ ۚ وَإِنَّ ٱلدَّارَ ٱلْءَاخِرَةَ لَهِىَ ٱلْحَيَوَانُ ۚ لَوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ﴿٦٤﴾ ﴾ العنكبوت: ٦٤

*«ይህች ዓለም ቀልድና ጨዋታ እንጅ ሌላ አይደለችም። (እውነተኛ) ሕይወት የመጭው ዓለም ሕይወት ነው። ዐዋቂዎች ቢሆኑ ኖሮ (ቀጣዩን ዓለም ይመርጡ ነበር)።» (አል አንከቡት 64)*

ምክንያቱም ሰዎች የሰሩትን ውጤት የሚያገኙበት፣ በዘልዓለማዊ ድሎት ወይም በዘልዓለማዊ ስቃይ ውስጥ የሚሆኑበት ዓለም ነውና።

የሰው ልጅ ወደዚያኛው ዓለም የሚሸጋገረው በሞት አማካይነት በመሆኑ ከአምላክ ጋር ግንኙነት የሌላቸው፣ ተፈጥሯቸው የተበረዘ፣ የአስተሳሰብ ሚዛናቸው የተዛባ ሰዎች ሁሉ ክደውታል። ይህም በመሆኑ አላህ ለመጭው ዓለም መኖር ጠንካራ መረጃዎችን ገልጿል። ነፍስ ከሞት በመነሳት እንድታምን፣ ቀልብ እርግጠኛ እንድትሆን ለመርዳት ይህን አድርጓል። የሰውን ልጅ ከሞት ዳግም ማስነሳት፣ መጀመሪያ ካልነበረበት ከማስገኘት ይበልጥ ቀላል ነው። የሰውን ልጅ ከሞት ከመቀስቀስ ይልቅ ሰማያትንና ምድርን ማነጽ ይከብዳል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَهُوَ ٱلَّذِى يَبْدَؤُا۟ ٱلْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَهُوَ أَهْوَنُ عَلَيْهِ ۚ ﴾ الروم: ٢٧

*«እርሱ ፍጡራንን ከምንም የሚያስ ገኝ፣ ከዚያም የሚመልሳችሁ (አምላክ) ነው። » (አል ሩም 27)*

﴿ لَخَلْقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ أَكْبَرُ مِنْ خَلْقِ ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٥٧﴾ ﴾ غافر: ٥٧

*«ሰማያትና ምድርን መፍጠር የሰውን ልጅ ከመፍጠር የበለጠ ትልቅ (ነገር) ነው፤ ግን አብዛኞቹ ሰዎች (ይህን) አያውቁም።» (ጋፊር 57)*

﴿ اللَّهُ الَّذِي رَفَعَ السَّمَاوَاتِ بِغَيْرِ عَمَدٍ تَرَوْنَهَا ۖ ثُمَّ اسْتَوَىٰ عَلَى الْعَرْشِ ۖ وَسَخَّرَ الشَّمْسَ وَالْقَمَرَ ۖ كُلٌّ يَجْرِي لِأَجَلٍ مُسَمًّى ۚ يُدَبِّرُ الْأَمْرَ يُفَصِّلُ الْآيَاتِ لَعَلَّكُم بِلِقَاءِ رَبِّكُمْ تُوقِنُونَ ﴿٢﴾ ﴾ الرعد: ٢

*«አላህ ያ ሰማያትን -የምታዩት ምሰሶ ሳይኖር- ከፍ ያደረገ፣ ከዚያም ከዙፋኑ ላይ የተስየመ (አምላክ) ነው። ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ ነው። ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ (በየምህዋራቸው) ይጓዛሉ። ነገሮችን ሁሉ ያስተናብራል (ይመራል)። አንቀጾቹንንም ያብራራል። ጌታችሁን መገናኘታችሁ የማይቀር መሆኑን በእርግጥ ታምኑ ዘንድ (ይህን ያደርጋል)።» (አል ረእድ 2)*

የሰው ልጅ ሆይ፣ ፍጥረተ ዓለሙ ላንተ መፈጠሩ ተአምራቱና ምልክቶቹ ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና አጋር አልባ መሆኑ ሊመሰክሩ መሰየማቸው እውነት ነው። አንተን ከሞት መቀስቀስና ማስነሳትም ሰማያትንና ምድርን ከመፍጠር ይቀላል። አምላክን ከሞት በኋላ ትገናኘዋለህ። የስራህን ዋጋም ይሰጥሐል። ፍጥረተ ዓለሙ በሙሉ አምላክን ያመልካል። ክብሩን ይገልጻል። ያወድሰዋል። ይቀድሰዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الْأَرْضِ الْمَلِكِ الْقُدُّوسِ الْعَزِيزِ الْحَكِيمِ ﴿١﴾ ﴾ الجمعة: ١

*«በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያሉ ሁሉ ንጉስ፣ ቅዱስ፣ አሸናፊም ጥበበኛም የሆነውን አላህን (ከጉድለቱና ለርሱ ከማይገቡ ባሕሪያት) ያጠራሉ (ክብሩንና ልዕልናውን ይመሰክራሉ)።» (አል ጁሙዓህ 1)*

ለልቅናው ፍጡራን ይሰግዳሉ።

﴿ أَلَمْ تَرَ أَنَّ اللَّهَ يَسْجُدُ لَهُ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَمَن فِي الْأَرْضِ وَالشَّمْسُ وَالْقَمَرُ وَالنُّجُومُ وَالْجِبَالُ وَالشَّجَرُ وَالدَّوَابُّ وَكَثِيرٌ مِّنَ النَّاسِ ۖ وَكَثِيرٌ حَقَّ عَلَيْهِ الْعَذَابُ ﴾ الحج: ١٨

*«በሰማያትና በምድር ውስጥ ያሉ (ፍጡራን ሁሉ)፣ ፀሐይም፣ ጨረቃም፣ ከዋክብትም፣ ተራሮችም፣ እጽዋትም፣ እንስሳትም በርካታ ሰዎችም ለአላህ እንደሚሰግዱለት አላየህምን? (ግና) ከሰዎች ብዙዎቹ (ከዚህ ሥርዓት) ያፈነግጣሉ። (እናም) ብዙዎቹ ቅጣት ተረጋግጦባቸዋል።» (አል ሐጅ 18)*



በየራሳቸው ስልትና ቋንቋ ይጸልያሉ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَلَمْ تَرَ أَنَّ اللَّهَ يُسَبِّحُ لَهُ مَن فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَالطَّيْرُ صَافَّاتٍ ۖ كُلٌّ قَدْ عَلِمَ صَلَاتَهُ وَتَسْبِيحَهُ ۗ وَاللَّهُ عَلِيمٌ بِمَا يَفْعَلُونَ ﴿٤١﴾ ﴾ النور: ٤١

*«አላህ፣ በሰማያትም በምድርም ያሉ (ፍጡራን)፣ አዕዋፋትም እንዲሁ ክንፎቻቸውን ዘርግተው የሚያወድሱት መሆኑን አላየህምን? ሁሉም የየራሳቸውን የሶላትና የውዳሴ (ስልት) ጠንቅቀው ያውቃሉ። አላህም የሚሠሩትን (ሁሉ) ዐዋቂ ነው።» (አል ኑር 41)*

አካልህም እርሱ በዘረጋው ስርዓት ይመራል። ልብ፣ ኩላሊት፣ ጉበትና ሌሎች አካላት ለአምላካቸው እጅ ሰጥተዋል። ለሕጉና ለፈቃዱ አድረዋል።

የሰው ልጅ ሆይ፣ ይህን ሁሉ ካወቅክ አላህ ከፈለግክ በርሱ እንድታምን፣ ካልፈለግክም እንድትክድ የሰጠህ የእምነት ነጻነት ፍጥረተ ዓለሙም ሆነ አካላዊ ማንነትህ ከሚመራበት ጉዞና ስርዓት እንድታፈነግጥ ምክንያት ሊሆን ይገባልን?

ትክክለኛ አእምሮ፣ አስተዋይ ልቦና ያለው ሰው ከዚህ ግዙፍ ዩኒቨርስ የጉዞ አቅጣጫ ያፈነገጠን ጎዳና ለመከተል አይፈቅድም።

# የሰው ልጅ መፈጠርና ልቅናው

አላህ አለምን ለማነጽና ለማስዋብ ተገቢ የሆነ ፍጡር ለመፍጠር ወሰነ። ይህም ፍጡር የሰው ልጅ እንዲሆን ፈቃዱ ሆነ። የሰው ልጅ የሚፈጠርበት ቁስ መሬት እንዲሆንም ወሰነ። እናም ከጭቃ ፈጠረው። ቅርጹንም አሳመረው። አካላዊ ማንነቱ ሲሟላ ከርሱ የሆነን መንፈስ ነፋበት። ያማረ አቋም ያለው፣ የሚያይ፣ የሚሰማ፣ የሚንቀሳቀስና የሚናገር ሰው ሆነ። ጌታውም በጀነት ውስጥ አስቀመጠው። ማወቅ ያለበትን ነገር ሁሉ አስተማረው። በጀነት ውስጥ ያሉ ምግቦችን ሁሉ እንዲመገብም ፈቀደለት። አንዲት ዛፍ ስትቀር። እርሷን ግን ለፈተና ሲል ከለከለው። ልቅናውን ለመግለጽ በመሻትም መላእክት እንዲሰግዱለት አዘዘ። ሁሉም መላኢኮች ሰገዱ። ኢብሊስ ብቻ ሲቀር። እርሱ ግን በኩራትና በትእቢት ምክንያት ለመስገድ አልፈቀደም። አምላክም ትእዛዙን ስለጣሰ ተቆጣበት። ከእዝነቱም አባረረው። ኢብሊስም የመኖር እድል እንዲሰጠው፣ እስከ እለተ ቀያማ እንዲያቆየው አምላኩን ጠየቀ። አምላክም ይህ ይሆን ዘንድ ፈቀደለት። እስከ ምድር ፍጻሜ እድሜውን አስረዘመለት። ሰይጣን አደምን፣ አምላክ ለርሱና ለዝርያዎቹ ክብር ስለቸረ ተመቀኘው። የሰው ልጆችን ባጠቃላይ መንገድ ለማሳት፣ በቀኝ በግራ፣ በፊት በኋላ አካቦ ሊያጠቃቸው፣ ሊያሳስታቸው፣ ሊያጠማቸው በአምላኩ ስም ማለ። የአላህ ቅን አገልጋዮች ሲቀሩ ከርሱ ጥቃት የሚያመልጥ የለም። ደጋጎችን ግን አላህ ከሰይጣን ጥቃት ጠብቋቸዋል።

አላህ አደምን ከሰይጣን ተንኮል አስጠነቀቀ። ሰይጣን ግን ጎተጎታቸው። ከጀነት ሊያስወጣቸው፣ የተሸፈነ ነውራቸውንም ሊገልጥባቸው ይህን አደረገ። ጥሩ መካሪ መስሎ ቀረባቸው። አላህ ይህችን ዛፍ እንዳትነኩ የከለከላችሁ መላኢኮች ወይም ዘልዓለማዊ ነዋሪዎች እንዳትሆኑ ስለፈለገ ነው አላቸው። አደምና ሐዋ ለጉትጎታው በመሸነፍ፣ ምክሩን በመቀበል አላህ የከለከላቸውን ዛፍ ተመገቡ። የአላህን ትእዛዝ በመጣሳቸው መጀመሪያ ያገኛቸው ቅጣት የነውራቸው መገለጥ ነበር። አምላካቸውም የሰይጣንን ተንኮል ዳግም አስታወሳቸው። እነርሱም ለጥፋታቸው ምህረት ለመኑ። እርሱም ንስሐቸውን ተቀበለ። ምህረትም አደረገላቸው። መረጣቸውም።



አቀናቸውም። ይኖሩባት ከነበረችው የገነት ምድርም እንዲወርዱ አዘዛቸው። ምድር ሊኖሩባት ተፈጥራለች። ለሕይወት የሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ከርሷ ውስጥ ተመቻችቷል። የሰው ልጅ ከርሷው ተፈጠረ፣ ከውስጧም ይኖራል፣ ሲሞትም ወደርሷው ይመለሳል፣ ከርሷውም ይቀሰቀሳል።

አደምና ባለቤታቸው ሐዋ ወደ ምድር ወረዱ። ዝርያዎቻቸው እየተበራከቱ ሄዱ። አደም ነብይ ነበሩና እርሳቸውና ቤተሰቦቻቸው አላህን በትእዛዙ መሠረት ያመልኩ ጀመር። አላህ ይህን የሰው ልጆች የመነሻ ታሪክ እንዲህ ተርኮልናል፡-

﴿ وَلَقَدْ خَلَقْنَٰكُمْ ثُمَّ صَوَّرْنَٰكُمْ ثُمَّ قُلْنَا لِلْمَلَٰٓئِكَةِ ٱسْجُدُوا۟ لِءَادَمَ فَسَجَدُوٓا۟ إِلَّآ إِبْلِيسَ
لَمْ يَكُن مِّنَ ٱلسَّٰجِدِينَ (١١) قَالَ مَا مَنَعَكَ أَلَّا تَسْجُدَ إِذْ أَمَرْتُكَ ۖ قَالَ أَنَا۠ خَيْرٌ مِّنْهُ خَلَقْتَنِى مِن نَّارٍ
وَخَلَقْتَهُۥ مِن طِينٍ (١٢) قَالَ فَٱهْبِطْ مِنْهَا فَمَا يَكُونُ لَكَ أَن تَتَكَبَّرَ فِيهَا فَٱخْرُجْ إِنَّكَ مِنَ ٱلصَّٰغِرِينَ
(١٣) قَالَ أَنظِرْنِىٓ إِلَىٰ يَوْمِ يُبْعَثُونَ (١٤) قَالَ إِنَّكَ مِنَ ٱلْمُنظَرِينَ (١٥) قَالَ فَبِمَآ أَغْوَيْتَنِى لَأَقْعُدَنَّ لَهُمْ
صِرَٰطَكَ ٱلْمُسْتَقِيمَ (١٦) ثُمَّ لَءَاتِيَنَّهُم مِّنۢ بَيْنِ أَيْدِيهِمْ وَمِنْ خَلْفِهِمْ وَعَنْ أَيْمَٰنِهِمْ وَعَن شَمَآئِلِهِمْ ۖ وَلَا تَجِدُ
أَكْثَرَهُمْ شَٰكِرِينَ (١٧) قَالَ ٱخْرُجْ مِنْهَا مَذْءُومًا مَّدْحُورًا ۖ لَّمَن تَبِعَكَ مِنْهُمْ لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنكُمْ
أَجْمَعِينَ (١٨) وَيَٰٓـَٔادَمُ ٱسْكُنْ أَنتَ وَزَوْجُكَ ٱلْجَنَّةَ فَكُلَا مِنْ حَيْثُ شِئْتُمَا وَلَا تَقْرَبَا هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةَ فَتَكُونَا
مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ (١٩) فَوَسْوَسَ لَهُمَا ٱلشَّيْطَٰنُ لِيُبْدِىَ لَهُمَا مَا وُۥرِىَ عَنْهُمَا مِن سَوْءَٰتِهِمَا وَقَالَ مَا
نَهَىٰكُمَا رَبُّكُمَا عَنْ هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةِ إِلَّآ أَن تَكُونَا مَلَكَيْنِ أَوْ تَكُونَا مِنَ ٱلْخَٰلِدِينَ (٢٠) وَقَاسَمَهُمَآ إِنِّى
لَكُمَا لَمِنَ ٱلنَّٰصِحِينَ (٢١) فَدَلَّىٰهُمَا بِغُرُورٍ ۚ فَلَمَّا ذَاقَا ٱلشَّجَرَةَ بَدَتْ لَهُمَا سَوْءَٰتُهُمَا وَطَفِقَا
يَخْصِفَانِ عَلَيْهِمَا مِن وَرَقِ ٱلْجَنَّةِ ۖ وَنَادَىٰهُمَا رَبُّهُمَآ أَلَمْ أَنْهَكُمَا عَن تِلْكُمَا ٱلشَّجَرَةِ وَأَقُل لَّكُمَآ إِنَّ
ٱلشَّيْطَٰنَ لَكُمَا عَدُوٌّ مُّبِينٌ (٢٢) قَالَا رَبَّنَا ظَلَمْنَآ أَنفُسَنَا وَإِن لَّمْ تَغْفِرْ لَنَا وَتَرْحَمْنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ
ٱلْخَٰسِرِينَ (٢٣) قَالَ ٱهْبِطُوا۟ بَعْضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ ۖ وَلَكُمْ فِى ٱلْأَرْضِ مُسْتَقَرٌّ وَمَتَٰعٌ إِلَىٰ حِينٍ
(٢٤) قَالَ فِيهَا تَحْيَوْنَ وَفِيهَا تَمُوتُونَ وَمِنْهَا تُخْرَجُونَ (٢٥) ﴾ الأعراف: ١١ - ٢٥

*«ፈጠርናችሁ። (እጅግ የተዋባችሁ አድርገን) ቀረጽናችሁም። ከዚያም መላእክትን፡- "ለአደም ስገዱ።" በማለት አዘዝን። ሰገዱ -ዲያብሎስ ሲቀር። እርሱ ከሰጋጆቹ አልነበረም። (አላህም)፡- "ባዘዝኩህ ጊዜ እንዳትሰግድ የከለከለህ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው። "እኔ ከርሱ የተሻልኩ ነኝ። እኔን የፈጠርከኝ ከእሳት ሲኾን፤ እርሱን ግን*

*የፈጠርከው ከጭቃ ነው።" አለ። "ከርሷ (ከገነት) ውረድ። ከውስጧ ሆነህ ልትኮራ አይገባም። ውጣ። አንተ ከወራዶች ነህና።" አለው። (ዲያቢሎስም)፦ "እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ።" ሲል ጠየቀ። (አላህም)፦"አንተ (እስከተወሰነ ወቅት ድረስ) ከሚቆዩት ተደርገሃል።" አለው። "መንገድ እንድስት ስላደረግከኝ ከቀና ጐዳና መካከል እቀመጥባቸዋለሁ።" አለ፤ "ከዚያም ከፊት ለፊታቸውም፣ ከበስተኋላቸውም፣ ከበስተቀኛቸውም፣ ከበ ስተግራቸውም እመጣባቸዋለሁ። አብዛኛዎቹንም (ለፀጋዎችህ) ምስጋና አድራቾች ሆነው አታገኛቸውም።" (አላህም) አለው፦"የተዋረድክና የተባረርክ ሆነህ ከርሷ ውጣ። ከነርሱ መሐል የተከተለህን፥ ገሃነምን በእር ግተም በናንተ እሞላለሁ።" "አደም ሆይ! አንተና ሚስትህ ገነት ውስጥ ተቀመጡ። የከጀላችሁትንም ተመገቡ። ግና ይህችን ዛፍ አትቅረቡ፤ ከበዳዮች ትሆናላችሁና።" ሰይጣንም ዕፍረተ ገላቸውን ሊያጋልጣቸው ጐተጐታቸው፤ ፡"ጌታችሁ ይህችን ዛፍ እንዳትመገቡ የከለከላችሁ መላእክት እንዳትሆኑ ወይም ዘንተ ዓለም ከሚኖሩት መሆን እንዳትችሉ ነው።" አላቸው። "እኔ ለናንተ (በጐ) መካሪያችሁ ነኝ።" ሲል ማለላቸው። በመሐላው አታለለ። ለውድቀት ዳረጋቸው። ዛፏን በቀመሱ ጊዜ ነውራቸው ተገለፀላቸው። በላያቸው ላይም የገነትን ቅጠል ይደርቱ ጀመር። ጌታቸውም፦ "ይህችን ዛፍ እንዳትነኩ አልከለከልኳችሁምን ሰይጣንም ግልጽ ጠላታችሁ መሆኑን አልነገርኳችሁም ነበር?" ሲል ተጣራ። "ጌታችን ሆይ! ራሳችንን በድለናል። ካልማርከንና ካላዘንክልን ከከሣሪዎች እንሆናለን።" በማለት (ጌታቸውን) ተማፀኑ። "ከፊላችሁ የከፊሉ ጠላት ሆናችሁ (ወደ መኖሪያ ሥፍራችሁ) ውረዱ። ምድር ላይ ጊዜያዊ ማረፊያና ለመኖር የሚያስፈልጓችሁ ነገሮች ተዘጋጅተውላችኋል።" አላቸው። "ከርሷ ላይ ትኖራላችሁ፤ ከርሷም ላይ ትሞታላችሁ። (ከሞት በኋላም) ከውስጧ (ዳግም) ትቀሰቀሳላችሁ።" አላቸውም።» (አል አእራፍ 11-25)*

አላህ ለሰው ልጅ የዋለውን ውለታ ስታስብ በአግራሞት ትዋጣለህ። በጥሩ አቋም ፈጠረው። የልቅናን እልባሳት ሁሉም አጎናጸፈው። አእምሮ፣ እውቀት፣ ሐሳቡን የመግለጽ ችሎታና አንደበት፣ የተደላደለ አካል፣ የሚያምር ተክለ ሰውነት፣ አዳዲስ እውቀቶችን የመሸመት ችሎታ፣ በላቁ ስነ ምግባሮች የመዋብ አቅም ለገሰው። በማሕጸን ውስጥ የዘር ፈሳሽ በሆነውና ጀነት ውስጥ በመላእክ በሚጎበኘው የሰው ልጅ መካከል ያለው ርቀት ይገርማል።



﴿ فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ أَحۡسَنُ ٱلۡخَٰلِقِينَ ﴾ المؤمنون: ١٤

*«አቻ የለሽ ፈጣሪ የሆነው አላህ ተባረከ።» (አል ሙእሚኑን 14)*

ይህች አለም የመኖሪያ መንደር ናት። የሰው ልጆችም ነዋሪዎቿ ናቸው። ሁሉም ነገር የሰውን ልጅ ለማገልገል፣ ጉዳዩን ለመሙላት፣ ፍላጎቱን ለማሳካት ተሰልፏል፡ መላእክት ሌት ከቀን ይጠብቁታል። ያገለግሉታል። ዩኒቨርሱ እርሱን በሚጠቅም አኳኋን ተገንብቷል። ጸሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ለርሱ ጥቅም ተገርተዋል። ለጊዜ ስሌቱ በሚያመች ሁኔታም ይንቀሳቀሳሉ። ሕዋው፣ እንዲሁም ያዘለው አየርና በራሪ እርሱን ለማገልገል ተገርተዋል። ምድርና ያዘለቻቸው ነገሮች እርሱን ያገለግላሉ። ለኑሮው ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። ምድር፣ ጋራዎች፣ ባህሮች፣ ወንዞች፣ ዛፎች እና ፍሬዎች፣ እጽዋትና እንስሳት ያገለግሉታል።[6] አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿ ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَخۡرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزۡقٗا لَّكُمۡۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡفُلۡكَ لِتَجۡرِيَ فِي ٱلۡبَحۡرِ بِأَمۡرِهِۦۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡأَنۡهَٰرَ ۝٣٢ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ دَآئِبَيۡنِۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ ۝٣٣ وَءَاتَىٰكُم مِّن كُلِّ مَا سَأَلۡتُمُوهُۚ وَإِن تَعُدُّواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ لَا تُحۡصُوهَآۗ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَظَلُومٞ كَفَّارٞ ۝٣٤ ﴾ إبراهيم: ٣٢ - ٣٤

*«አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ፣ ከሰማይም ውሃን ያወረደና በርሷም ለናንተ ሲሳይ ይሆናችሁ ዘንድ (የተለያዩ) ፍራፍሬዎችን ያበቀለ (አምላክ) ነው። መርከብንም ባሕሩ ላይ መንዝ ትችል ዘንድ - በትእዛዙ ገራላችሁ። ወንዞችንም ገራላችሁ። ፀሐይንና ጨረቃንም፣ ዘውትር ተጓዦች አድርጐ፣ ገራላችሁ። ሌትንና ቀንንም ገራላችሁ።» (ለሕይወት) የሚያስፈልጓችሁንም ነገሮች ሁሉ ሰጥቷችኋል። የአላህን ፀጋዎች ቆጥራችሁ አትዘልቋቸውም። የሰው ልጅ በእርግጥም በዳይ፣ ከሓዲ ነው። (ኢብራሂም 32-34)*

[6] ሚፍታህ ዳሩ ስአዳህ 1/327-328

አስተሳሰብ ላይ ሐይማኖት ጠንካራ የመረጃ ጉልበት ባለቤት እንደሆነ ይቀጥላል።»[11]

ሙሐመድ ፈሪድ ወጅዲ እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

«የሐይማኖት አስተሳሰብ ሊሚሸሽ አይችልም። ምክንያቱም የነፍስ የተከበረ ዝንባሌ፣ እጅግ የላቀ ስሜት ነውና። የሰውን ልጅ አንገቱን ቀና እንዲያደርግ የሚያስችልና የሚያኮራ ስሜትም ነው። ይህ ዝንባሌ በእርግጥም እየጨመረ ይሄዳል እንጅ አይቀንስም። ጥሩውን ከመጥፎ፣ የሚለይበት አእምሮ ባለቤት እስከሆነ ድረስ የሐይማኖት አስተሳሰብ ምንጊዜም አብሮት ይኖራል። እውቀትና ግንዛቤው ባደገ ቁጥርም ይህ ዝንባሌው አብሮት ያድጋል።»[12]

የሰው ልጅ ከአምላኩ ሲርቅ ራሱን እንዳጥቂ ሊቆጥር ይችላል። ግና ግንዛቤው በጨመረ ቁጥር አምላኩን ባለማወቁ እና ለነፍሱ የሚበጃትን ከሚከፋት መምረጥ ባለመቻሉ የተሸከመው መሐይምነት ይበልጥ ግልጽ ይሆንለታል። ስለ ተፈጥሮ ያለው ሳይንሳዊ እውቀትም ከማያውቀው አንጻር ኢምንት እንደሆነ ይገነዘባል። በዚህ ጊዜ ከትእቢቱ ተመልሶ እጅ ይሰጣል። ትሁትም ይሆናል። ከእውቀቶች በስተጀርባ አዋቂና ጥበበኛ፣ ከተፈጥሮ በስተጀርባ በችሎታው ወሰን የሌለው ፈጣሪ መኖሩን ይናዘዛል። ቅንና ታማኝ አጥኝ ይህ ግንዛቤው በሩቅ ሚስጥር ወደማመንና ትክክለኛውን ሐይማኖት ወደመቀበል፣ እንዲሁም ለተፈጥሯዊው ጥሪ ምላሽ ወደመስጠት ይመራዋል። የሰው ልጅ ከዚህ ሲያፈነግጥ ተፈጥሯዊ ባህሉ ተበላሽቶ ወደ እንስሳዊነት ደረጃ ያሽቆለቁላል።

የእስካሁኑ ገለጻችን መቋጠሪያ ውል የሰው ልጅ የአለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ተገዥ እንዲሆንና ከሁለቱም አለማት መከራ ተገላግሎ ደስታን እንዲጎናጸፍ የሚያስችለው፣ እንደዚሁም የሰው ልጅ የሚስብ ጉልበት የተሟላ ይሆን ዘንድ አላህን በብቸኝነት በማምለክና ለሕግጋቱ በማደር ላይ የተመሰረተ እውነተኛ ሐይማኖት መሠረታዊ የሕይወት አስፈልጎት ነው። አእምሮ የሚረካውና የመጨረሻ ግቡ የሚሳካለትም በርሱ ብቻ ነው።

[11] አል ዲን ዶክተር አብደላህ አልደራዚ ገጽ 87
[12] ያለፈው ምንጭ ገጽ 88



እውነተኛ ሐይማኖት መንፈስን ለማጽዳት፣ የሕሊናን ንቃት ለመጨመርም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ንጹህ ስሜቶች በሐይማኖት ውስጥ የሰፋ መስክ፣ የማይነጥፍ የሐይል ምንጭ ያገኛሉና። እውነተኛ ሐይማኖት ወደውስጥ የሚያስርጸው የተነሳሽነት ጉልበት፣ ተስፋ መቁረጥንና ስንፍናን በመከላከል የሰውን ልጅ የመወሰንና የመስራት አቅም በእጅጉ ይጨምራል።

ይህም በመሆኑ፡- «የሰው ልጅ በባህሪው ስልጡንና ማሕበራዊ ነው» እንደምንለው ሁሉ፡- «የሰው ልጅ በባህሪው ሐይማኖተኛ ነው» ልንልም ይገባል።[13] ምክንያቱም የሰው ልጅ ሁለት ሃይሎች አሉት። የእውቀትና የመወሰን ሐይል። ደስታው የተሟላ ሊሆን የሚችለው እነዚህ ሁለቱ አቅሞቹ የተሟሉ ሲሆኑ ነው። እውቀታዊ ክሕሎቱ ሊሟላ የሚችለው የሚከተሉትን ነገሮች ሲያውቅ ነው፡-

1) የሰውን ልጅ ካልነበረበት ያስገኘውንና ብዙ ጸጋዎችን የለገሰውን ፈጣሪና ሲሳይ ለጋሽ አምላክ ማወቅ፣
2) የአላህን ስሞችና ባህሪያት፣ ለርሱ የሚገቡትንና እነዚህ ባህሪያት በፍጡራኑ ላይ ያላቸውን ተጽእኖ ማወቅ፣
3) ወደ አላህ የሚያደርሰውን ጎዳና ማወቅ፣
4) የሰውን ልጅ ከዚህ ጎዳና እና በርሱ አማካይነት ከሚያገኘው ታላቅ ጸጋ የሚያቅቡትን እንቅፋቶች ማወቅ፣
5) የራስን ማንነት፣ የሚበጀውንና የሚከፋውን፣ ልዩ ችሎታና ጉድለቶችን ማወቅ።

በነዚህ አምስት የእውቀት ዘርፎች የሰው ልጅ የማወቅ ጉልበት ይሟላል።

የእውቀትና የመወሰን ክህሎት ሊሟላ የሚችለው አላህ በባሮቹ ላይ ያለውን መብት በመጠበቅ፣ በቅንነትና በታማኝነት፣ ለውለታው ምላሽ በመስጠት ስሜት በመፈጸም ብቻ ነው። የእርሱ እገዛም

[13] ያለፈው ምንጭ 84-98

ያስፈልጋል። ደጋግ ባሮቹን ወደመራበት ቅን ጎዳና ይመራው ዘንድ የግድ ነው።[14]

እውነተኛ ሐይማኖት የሰውን ልጅ የተለያዩ ተፈጥሯዊ ጉልበቶች የሚያጠነክርና የሚያጎለብት እንደሆነ ሁሉ ሕብረተሰቡንም ከክፋት ይጠብቃል። ምክንያቱም የሰው ልጅ ሕይወት በአባላቶቹ መካከል መረዳዳት ከሌለ በአግባቡ አይሄድም። ይህ መረዳዳት ሊከናወን የማችለው በግለሰቦች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚገዛ፣ መብትና ግዴታዎችን በአግባቡ የሚያስቀምጥ ስርዓት ሲኖር ነው። ይህ ስርዓት እጅግ የተከበረና የታፈረ፣ አስፈጻሚ ባለ ስልጣን ያስፈልገዋል።

ይህ ባለስልጣን ማን ሊሆን ይችላል? ስርዓትን ለማስከበር፣ የሕብረሰተቡን ትስስር ለማጠንከር፣ ስርዓቱን ለማርጋት እና የሰላም መስፈርቶችን ለማሟላት ከሐይማኖት የበለጠ ስልጣን እና ጉልበት በምድር ላይ እንደሌለ በእርግጠኝነት መግለጽ እችላለሁ።

የዚህ ሁሉ ሚስጥር የሰው ልጅ ከሌሎች እንስሳት የተለየ ባህሪ ስላው ነው። ይህውም ወደና ፈቅዶ የሚያከናውናቸውን ድርጊቶች የሚመራው በዓይን የማይታይ እና በጆሮ የማይሰማ ነገር ሲሆን፣ እርሱም መንፈስን የሚያውድና የሚያመጥቅ፣ አካልን የሚገራ እምነት ነው። የሰውን ልጅ ምን ጊዜም የሚመራው ትክክለኛ ወይም የተበላሸ የሆነ እምነቱ ነው። እምነቱን ካስተካከልክ ሁሉ ነገሩ ይስተካከላል። እምነቱ ከተበላሸ ሁለ ነገሩም ይበላሻል።

እምነት ለሰው ልጆች ውስጣዊ ተቆጣጣሪ ነው። ይህም ለሁለት ነገሮች ጋር የተያያዘ ነው፡

- በመልካም ስነ ምግባር፣ በሰው ልጅ ልቅናና በሌሎችም የመጠቀ እሴቶች ማመን። ታላላቅ ነፍሶች ከቁሳዊ ግዴታና ቅጣት እንደሚያመልጡ በእርግጠኝነት ቢያውቁ እንኳ እነዚህን እሴቶች ተቃርነው ለመገኘት ነፍሳቸው ይሉኝታ ይይዛታል።
- ውስጥን በሚያውቀው፣ ሚስጥር በማይደብቅበት አምላክ ማመን። ሸሪዓ ስልጣኑን የሚያገኘው ከርሱ ትእዛዝና እቀባ ነው። ስሜቶች

[14] አል ፈዋኢድ 18-19



እርሱን በመውደድ ወይም በመፍራት ትእዛዙን ለመታረን በይሉኝታ ይሞላሉ።

ይህ ዓይነቱ እምነት በሰው ልጅ ነፍስ ላይ ከፍተኛ ጉልበትና ስልጣን እንዳለው፣ የከንቱ ፍላጎትን እውሎነፋስና የስሜትን መለዋወጦች ለመቋቋም ያለው ጥንካሬ ከፍተኛ መሆኑና በሁሉም የማሕበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ፈጣን ተጽእኖ እንደሚያሳድር ጥርጥር የለውም።

ይህም በመሆኑ የሰዎች ግንኙነት በፍትህ መሠረት ላይ እንዲቆም ሐይማኖት አስፈላጊ ነው። እናም ሐይማኖት ማሕበራዊ አስፈልጎት ይሆናል። ሐይማኖት በሕብረተሰቡ ውስጥ ያለው ቦታ ልብ በአካል ውስጥ ያላትን ቦታ ይመጥናል።[15]

ትክክለኛው ሐይማኖት ለሰው ልጅ ይህን ያህል ጠቃሚ ቢሆንም በአሁኑ ሰአት በርካታ ሐይማኖቶች በምድር ላይ ይታያሉ። እያንዳንዱ አማኝ የራሱን ሐይማኖት ከሌላው የላቀ አድርጎ ያያል። ከዚህ አኳያ የሰው ልጅ ነፍስ የምትከጅለውን ሊያሟላለት፣ ሕልሟን እውን ሊያደርግላት የሚችለው ትክክለኛ ሐይማኖት የትኛው ነው? የእውነተኛ ሐይማኖት መስፈርቱስ ምንድን ነው?

[15] አዲን-ዶክተር አብደላህ አልደራዚ ገጽ 98-102

# የእውነተኛ ሐይማኖት መስፈርቶች

የእያንዳንዱ ሐይማኖት ተከታይ የርሱ ሐይማኖት ብቻ እውነተኛና ሊከተሉት የሚገባ እንደሆነ ያምናል። የተሳሳቱ እምነቶች ወይም የሰው ሰራሽ አስተሳሰቦች ተከታዮች ለእምነታቸው ትክክለኛነት መረጃ ስትጠይቃቸው አያት ቅድመ አያቶቻቸው በዚህ እምነት ላይ እንደነበሩና እነርሱን ፈለጋቸውን መከተላቸውን ይገልጹልሐል። ከዚያም ከሰነድም ከይዘትም አኳያ በግድፈት የተሞሉ አፈታሪኮችን ይዘከሩልሐል። ማን እንደተናገራቸው፣ ማን እንደጻፈፋቸው፣ መጀመሪያ በምን ቋንቋ እንደተጻፉና በየት አገር ውስጥ እንደተገኙ የማይታወቁ፣ የይዘትም ሆነ የሰነድ ትክክለኛነታቸውን የሚያረጋግጥ ምንም ዓይነት ሳይንሳዊ ፍተሻ ሳይካሄድባቸው ከትውልድ ትውልድ እንደ ቅዱስ እየታዩና እየተከበሩ የመጡ በመጽሐፍ መልክ የተጠረዙ የጽሑፍ ጥርቅሞችን መሠረት ያደርጋሉ።

እነዚህ ምንጫቸው በማይታወቅ መጽሐፍትና መሠረት አልባ አፈታሪኮች በሐይማኖት መስክ መረጃ ሊሆኑ አይችሉም። እነዚህ የተበረዙና የተከለሱ ሰው ሰራሽ እምነቶች ትክክለኛ ናቸው ወይስ ስህተት? ሁሉም እውነት ሊሆኑ አይችሉም። ምክንያቱም እውነት አንድ ብቻ ነው። እናም እነዚህ የተበረዙ እምነቶች እና አስተሳሰቦች ሁሉ በአንድነት ከአላህ የመነጩና እውነተኛ ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ የትኛው ነው እውነት?

እውነተኛውን እምነት ከሐሰት ለመለየት የሚያስችሉትን ትክክለኛ መስፈርቶች ሊኖሩን ይገባል። እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟላ ሐይማኖት ካገኘን እውነተኛው ሐይማኖት እርሱ ነው። እነዚህን መስፈርቶች የማያሟሉት ሁሉ ደግሞ ሐሰተኛ ሐይማኖቶች ናቸው።

## የመስፈርቶች ይዘት

<u>አንደኛ</u>፡- ከአላህ በመላኢካ አማካይነት ከመልእክተኞች ወደ እንዱ፣ ለሰው ልጆች ያስተምረው ዘንድ፣ የወረደ መሆን አለበት። ምክንያቱም እውነተኛ ሐይማኖት የአላህ ሐይማኖት ብቻ ነው። ሰዎች ሊታዘዙት የሚገባና በእለተ ትንሳኤም ከላከላቸው ሐይማኖት አኳያ የሚመረምራቸውም እርሱ ብቻ ነውና። አላህ እንዲህ ብሏል፡-



﴿ إِنَّآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ كَمَآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ نُوحٖ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعۡدِهِۦۚ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَٱلۡأَسۡبَاطِ وَعِيسَىٰ وَأَيُّوبَ وَيُونُسَ وَهَٰرُونَ وَسُلَيۡمَٰنَۚ وَءَاتَيۡنَا دَاوُۥدَ زَبُورٗا ١٦٣ ﴾ النساء: ١٦٣

*«እኛ ለኑሕና ከርሱ በኋላ ለተነሱ ነቢያት ራዕይ እንደገለጽን ለአንተም ገለጽንልህ። ለኢብራሂምም፣ ለኢስማ ኢልም፣ ለኢስሐቅም፣ ለየዕቁብም፣ ለነገዶችም፣ ለዒሳም፣ ለአዩብም፣ ለዩኑስም፣ ለሃሩንም፣ ለሱለይማንም ራዕይን ገለጽን። ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው።»* (አል ኒሳእ 163)

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ٢٥ ﴾ الأنبياء: ٢٥

*«ከአንተ በፊት መልዕክተኛን አልላክነም፣ "እነሆ፣ ከኔ ሌላ አምላክ የለም። ስለሆነም (በብቸኝነት) አምልኩኝ።" የሚል መልዕክት የምናወርድለት ቢሆን እንጅ።»* (አል አንቢያእ 25)

ከዚህ መስፈርት አኳያ አንድ ሰው ከአእምሮው ያፈለቀውና ወደ አላህ ሳይሆን ወደራሱ የሚያስጠጋው ሐይማኖት እውነተኛ ሐይማኖት ሊሆን አይችልም። ሐሰተኛ መሆኑም ጥርጥር የለውም።

<u>ሁለተኛ</u>፡- አላህን ብቻ በብቸኝነት ማምለክን የሚያስተምር፣ በርሱ ላይ ሌላን አካል ማጋራትን፣ ወይም በአምላክና በሰዎች መካከል የመንፈስ ደላላ ማድረግን የሚከለክል ሐይማኖት መሆን አለበት። ምክንያቱም አላህን በብቸኝነት ማምለክ የነብያት ሁሉ ትምህርት ነበር። ሁሉም ነብያት ለየ ሕዝቦቻቸው እንዲህ ብለዋል፡-

﴿ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥٓ ﴾ الأعراف: ٧٣

*«አላህን (ብቻ) አምልኩ። ከርሱ ሌላ አምላክ የላችሁም።»* (አል አእራፍ 73)

<u>ሦስተኛ</u>፡- ትምህርቶቹ ሁሉም ነብያትና የአላህ መልእክተኞች ካስተማሩት ትምህርት ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት። ይህውም አምላክን በብቸኝነት ማምለክን፣ ከርሱ ጋር ሌላን አካል

አለማጋራትን የሚያስተምር፣ ወደርሱ መንገድ የሚጠራ፣ የወላጆችን መብት መጣስንና ነፍስን ያለ አግባብ መግደልን፣ እንደዚሁም ግልጽም ስውርም የሆኑ ጸያፍ ተግባራትን እርም የሚያደርግ መሆን አለበት። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَمَآ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِىٓ إِلَيْهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعْبُدُونِ ﴿٢٥﴾﴾
الأنبياء: ٢٥

ከአንተ በፊት መልዕክተኛን አላክ ንም፣ "እነሆ፣ ከኔ ሌላ አምላክ የለም። ስለሆነም (በብቸኝነት) አምልኩኝ።" የሚል መልዕክት የምናወርድለት ቢሆን እንጅ። (አል አንቢያእ 25)

﴿قُلْ تَعَالَوْا۟ أَتْلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمْ عَلَيْكُمْ ۖ أَلَّا تُشْرِكُوا۟ بِهِۦ شَيْـًٔا ۖ وَبِٱلْوَٰلِدَيْنِ إِحْسَٰنًا ۖ وَلَا تَقْتُلُوٓا۟ أَوْلَٰدَكُم مِّنْ إِمْلَٰقٍ ۖ نَّحْنُ نَرْزُقُكُمْ وَإِيَّاهُمْ ۖ وَلَا تَقْرَبُوا۟ ٱلْفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنْهَا وَمَا بَطَنَ ۖ وَلَا تَقْتُلُوا۟ ٱلنَّفْسَ ٱلَّتِى حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلْحَقِّ ۚ ذَٰلِكُمْ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ ﴿١٥١﴾﴾ الأنعام: ١٥١

*"ሙሐመድ ሆይ፣ ኑ፣ ጌታችሁ (በትክክል) እርም ያደረጋቸውን ነገሮች አነብላችኋለሁ።" በላቸው፣ "በርሱ ምንንም አታጋሩ፣ ለወላጆቻችሁም በጐ ዋሉ፣ ልጆቻችሁንም ድህነትን በመስጋት አትግደሉ። ለናንተም ለነርሱም ሲሳይን እንለግሳችኋለን። ግልጽም ስውርም የሆኑ ፀያፍ ተግባራትንም አትቅረቡ። አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስም -ያለ አግባብ- አታጥፉ። ይህ (አላህ) ትገነዘቡ ዘንድ የደነገገላችሁ መመሪያ ነው።»(አል አንዓም 151)*

﴿وَسْـَٔلْ مَنْ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رُّسُلِنَآ أَجَعَلْنَا مِن دُونِ ٱلرَّحْمَٰنِ ءَالِهَةً يُعْبَدُونَ ﴿٤٥﴾﴾ الزخرف: ٤٥

*«(ሙሐመድ ሆይ!) ከ"አር-ረሕማን" ውጭ ሌሎች የሚመለኩ አማልክትን አድርገን እንደሆነ፣ ከአንተ በፊት የላክናቸውን መልዕክተኞች፣ ጠይቅ።» (አል ዙኽሩፍ 45)*

አራተኛ፡- እርስ በርስ የማይቃረን መሆን አለበት። አንድን ነገር የሚያዝ፣ መልሶም የሚከለክል፣ አንድን ነገር እርም አድርጎ



ተመሳሳይን ነገር ያለ ምክንያት የሚፈቅድ፣ አንድን ነገር ለተለዩ የሰው ዓይነቶች የሚፈቅድና ለሌሎች የሚከለክል መሆን የለበትም። አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ٱلْقُرْءَانَ ۚ وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُوا۟ فِيهِ ٱخْتِلَٰفًا كَثِيرًا ﴿٨٢﴾﴾
النساء: ٨٢

*«ቁርአንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ከሆነ አካል (የመነጨ) ቢሆን ኖሮ ከውስጡ በርካታ ተቃርኖዎችን ባገኙ ነበር።» (አል ኒሳእ 82)*

አምስተኛ፡- የሰው ልጆችን እምነት፣ ክብር፣ ገንዘብ፣ ሕይወትና የዘር ቀጣይነት መብቶች ለመጠበቅ ያለሙ ትእዛዞችንና አስተምህሮቶችን የያዘ ሊሆን ይገባል።

ስድስተኛ፡- የሰው ልጆች እርስ በርስ እንዳይበዳደሉ የሚያቅብ እዝነትና ችሮታ ሊሆን ይገባል። ይህ በደል መብትን በመጋፋት ወይም በበጎ ነገሮች ራስን ብቻ ተጠቃሚ በማድረግ ወይም ታላላቆች ተራውን ሕዝብ መንገድ በማሳት የሚከሰት ሊሆን ይችላል። አላህ በሙሳ ላይ ያወረደው ተውራት የቋጠረውን እዝነትና ችሮታ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡

﴿وَلَمَّا سَكَتَ عَن مُّوسَى ٱلْغَضَبُ أَخَذَ ٱلْأَلْوَاحَ ۖ وَفِى نُسْخَتِهَا هُدًى وَرَحْمَةٌ لِّلَّذِينَ هُمْ لِرَبِّهِمْ يَرْهَبُونَ ﴿١٥٤﴾﴾ الأعراف: ١٥٤

*«ሙሳ ቁጣው ሲበርድለት ሰሌዳዎ ችን ያዛቸው። ለነዚያ ጌታቸውን ለሚፈሩት ችን መመሪያንና እዝነትን ያዘለ መልዕክት ሰፍሮባቸዋል።» (አል አእራፍ 154)*

የእሳን መላክ አስመልክቶም፡

﴿وَلِنَجْعَلَهُۥٓ ءَايَةً لِّلنَّاسِ وَرَحْمَةً مِّنَّا﴾ مريم: ٢١

*«ለሰው ልጆች ተአምርና ከኛ የሆነ ችሮታ ልናደርገው (አቅደናል)።» (መርየም 21)*

ሷሊሁን አስመልክቶም፡

ለዝገት እንዳይተውት ይታዘዙ ነበር። ምክንያቱም ማእድን ከነርሱ ዘንድ የተቀደሰ ነገር ነበርና።[22]

በሁሉም ዘመናቸው በአምላክ ጥንድነት ያምኑ ነበር። አንደኛው የብርሃን ወይም የደግ አምላክ ሲሆን «አሁወር መሪዝድ» ወይም «የዝዲን» በሚል ስያሜ ይጠሩት ነበር። ሁለተኛው የጨለማ ወይም የክፋት አምላክ ሲሆን «አሀረመን» በሚል ስያሜ ይጠሩት ነበር። በሁለቱ አማልክት መካከል ምንጊዜም ጦርነትና ግጭት እንዳለ ያምኑ ነበር።[23]

ቡድሂዝም በሕንድና በመካከለኛው እስያ የተስፋፋ ሐይማኖት ሲሆን የጣኦት አምልኮ ሐይማኖት ነው። አማኞቹ በየሄዱበት ቦታ ጣኦታቸውን ተሸክመው ይጓዛሉ። ቤተ ጣኦት ይገነባሉ። በሰፈሩባቸው ቦታዎች ሁሉ የቡድሐን ሐውልት ይተክላሉ።[24]

* * *

ሂንዱይዝም በአማልክት ብዛት የሚታወቅ ሐይማኖት ነው። በ6ኛው ክፍለ ዘመን የአማልክቶቻቸው ቁጥር 330 ሚሊዮን ደርሶ ነበር።[25]

ቆንጆ፣ ግዙፍ ወይም ጠቃሚ ነገሮች ሁሉ አምላክ ይደረጋሉ። በዚህ ዘመን የሐውልት ስራ ጥበብ ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። ባለሙያዎችም እጅግ የተካኑበት ሁኔታ ነበር።

«የመካከለኛው ዘመን የሕንድ ታሪክ» በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ስለ ንጉስ ሐሪሽ (606-648 ዓ.ል)፣ ማለትም እስልምና በዓረቢያ ምድር ይፋ በሆነበት ጊዜ ስለነበረው የሕንድ ሁኔታ ሲገልጽ፡- «የሂንዱይዝምና የቡድሂዝም እምነቶች ሙሉ በሙሉ የጣኦት አምልኮዎች ነበሩ። ምን አልባትም ቡድሂዝም ከሂንዱይዝም ይበልጥ በጣኦት አምልኮ ውስጥ ተዘፍቆ ነበር ማለት ይቻላል። የቡድሂዝም እምነት የተጀመረው የአምላክን ሕልውና በመካድ ነው። በሂደት ግን ቡዛን የተላቀ አምላክ አደረጉ። በመቀጠልም እንደ bodhistavas አይነት ተጨማሪ አማልክትን አከሉ። ቡድሂዝም በሕንድ በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፋ። እናም ቡድሃ ማለት ጣኦት ማለት ተደርጎ በአንዳንድ የምስራቅ ቋንቋዎች ውስጥ እስኪታወቅ ድረስ የጣኦት አምልኮ ሕንድን አጥለቀለቀ።

በዚያ ዘመን አለም ባጠቃላይ በጣኦት አምልኮ የተዋጠች እንደነበረች ጥርጥር የለውም። ክርስትናን ጨምሮ የሴማዊያን እምነትና የቡድሃ እምነቶች ጣኦታትን በማላቅ የሚሽቀዳደሙ ይመስል ነበር።»[26]

ሌላ ሕንዳዊ ጸሐፊ እንዲህ ሲል ጽፏል፡-

«አማልክትን የመስራት ባህል በዚህ ብቻ አላበቃም። በተለያዩ የታሪክ ወቅቶች አዳዲስ አማልክት ወደ አማልክቱ ማሕበረሰብ በከፍተኛ ቁጥር ሲቀላቀሉ ኖረዋል። በመጨረሻም ቁጥራቸው በትክክል ከማይታወቅበት ደረጃ ላይ ደርሷል።»[27]

* * *

የሐይማኖቶች ተጨባጭ ሁኔታ ከላይ እንደተገለጸው ነበር። ታላላቅ መንግስታት የተገነቡባቸው እና የተስፋፉባቸው የስልጣኔ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም የስነ ጽሑፍ ማእከላት የነበሩ ስልጡን ሃገሮችን በተመለከተ ሐይማኖቶች የጠፉባቸው፣ ስረ መሰረታቸውንና ጉልበታቸውን ያጡባቸው ከተሞች ነበሩ። የተሐድሶ ሰዎች ጠፍተዋል። መምህራኑ ከስመዋል። አምላክ የለሽነት ነግሶባቸዋል። ብክለት ተንሰራፍቶባቸዋል። የሰው ልጅ ራሱን አዋርዷል፣ ንቋል። በመሆኑም ራስን ማጥፋት ይበዛባቸዋል። ቤተሰባዊ ትስስር ላልቷል። ማሕበራዊ ትስስርም ተበጥሷል። የስነ ልቦና ሐኪሞች በዝተዋል። ጠንቋዮች ማሕበረሰቡን አጨናንቀዋል። የሰው ልጅ ደስታ ይሰጠኛል ያላቸውን ነገሮች ሁሉ ሞክሯል። ሰላም ላጣች ነፍሱ ረፍት ፍለጋም አዳዲስ እምነቶችንና አመለካከቶችን ሁሉ ፈትሿል። ግና ያሰበው አልተሳካም። የከጀለው አልሆንም። ውስጣዊ መከራው፣ የመንፈስ ስቃዩ ቀጥሏል። እውነተኛውን አምላክ አግኝቶ እርሱ በሚሻው መልኩ እስካላመለከው ድረስ ነፍሱ ሰላም አታገኝም።

[22] ኢራን በሳሳንዮች ዘመን ገጽ 155
[23] ያለፈው ምንጭ ገጽ 183
[24] The discovery of India p 201-202
[25] የጥንቷ ሕንድ 3/276

[26] C.V.Vida : History of mediavel Hindu India Vol.1
[27] የነቢዩ መሐመድ ታሪክ-በፕሮፌሰር አቡል ሐሰን አሊ ሐሰን አልነደዊ ገጽ 19-28

አላህ ከርሱ መንገድ ያፈነገጡ ወገኖችን የመከራ ሕይወት ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِي فَإِنَّ لَهُ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُ يَوْمَ الْقِيَامَةِ أَعْمَى ﴿١٢٤﴾ ﴾ طه: ١٢٤

*"ግና ከመልዕክቴ ያፈገፈገ ሕይወቱ ጭንቅ የበዛበት ይሆናል። በትንሳኤ ቀንም እውር አድርገን እንቀሰቅሰዋለን።» (ጧሃ 124)*

አማኞች በዚህች አለም ውስጥ የሚያገኙትን ደስታ ሲያብራራም እንዲህ ብሏል፡-

﴿ الَّذِينَ آمَنُوا وَلَمْ يَلْبِسُوا إِيمَانَهُم بِظُلْمٍ أُولَٰئِكَ لَهُمُ الْأَمْنُ وَهُم مُّهْتَدُونَ ﴿٨٢﴾ ﴾

الأنعام: ٨٢

"እነዚያ ያመኑትና እምነታቸውን በበደል ያልበከሉት ሰላም የነርሱ ብቻ ነው። ቅኑን ጉዳና የተመሩትም እነርሱ ብቻ ናቸው።" (አል አንዓም 82)

የመጭውን ዓለም ስኬታቸውንም እንዲህ ገልጾታል፡-

﴿ وَأَمَّا الَّذِينَ سُعِدُوا فَفِي الْجَنَّةِ خَالِدِينَ فِيهَا مَا دَامَتِ السَّمَاوَاتُ وَالْأَرْضُ إِلَّا مَا شَاءَ رَبُّكَ عَطَاءً غَيْرَ مَجْذُوذٍ ﴿١٠٨﴾ ﴾ هود: ١٠٨

*«(በእንጻሩ) እነዚያ እድለኞች ገነት ውስጥ ይሆናሉ። በውስጧም፣ በጌታህ በጐ ፈቃድ፣ ዘንተ ዓለም ይኖራሉ። የማይቋረጥ ስጦታም (ይጐርፍላቸዋል)።» (ሁድ 108)*

* * *

ከእስልምና ውጭ ያሉ ሐይማኖቶች ከላይ ባሰፈርናቸው የትክክለኛ ሐይማኖት መስፈርቶች ሲመዘኑ አብዛኞዎቹን መመዘኛዎች የማያሟሉ ሆነው እንደሚገኙ ከላይ ያሰፈርነው አጭር ማብራሪያ ያመለክታል።

እነዚህ ሐይማኖቶች ያጡት አንኳር ቁም ነገር አላህን በብቸኝነት የማምለክን ጽንሰ ሐሳብ ነው። ተከታዮቻቸው ከአላህ ጋር ሌሎች አማልክትን ያመልካሉ። በተጨማሪም እነዚህ ሐይማኖቶች



በየትኛውም ቦታና ጊዜ ለሚገኘው የሰው ልጅ እምነቱን፣ ክብሩን፣ ንብረቱን፣ ሕይወቱንና የዘር ቀጣይነት ዋስትናውን የሚጠብቅለትና የሚያረጋግጥለት ሕግና ስርዓት የላቸውም። የአላህ ፈቃድ ወደሆነው ሕግ አያመላክቱም። እርስ በርስ በሚቃረኑ ሐሳቦች የተሞሉ በመሆናቸውም ለተከታዮቻቸው ደስታንና ውስጣዊ ሰላምን አይለግሱም።

እስልምናን በተመለከተ ግን አላህ የወደደውና ለሰው ልጆች የመረጠው እውነተኛና ዘልዓለም ነዋሪ የአላህ ሐይማኖት መሆኑን የሚያብራሩ ነጥቦች ወደፊት በዚህ መጽሐፍ ይዳሰሳሉ። እስካሁን ለሰጠነው ማብራሪያ ማሳረጊያ ይሆነን ዘንድም የነብይነትን ምንነትና ምልክቶች እንዲሁም ለሰው ልጅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ቀጥሎ እንገልጻለን። የነብያትን መልእክት መሠረታዊ ጭብጦችና የመጨረሻውን መለኮታዊ መልእክት ምንነትም እንዳስሳለን።

# የነብይነት ምንነት

የሰው ልጅ በዚህች አለም ሕይወት ውስጥ ሊያውቀው ይበልጥ ግዴታ የሚሆነው ትልቁ ቁም ነገር ከምንም ያስገኘውንና ጸጋዎችን የለገሰውን አምላኩን ማወቅ ነው። አላህ የሰውን ልጅ የፈጠረበት ትልቁ አላማ እርሱን በብቸኝነት ሊያመልኩት መሆኑንም መረዳት ያስፈልጋል።

የሰው ልጅ አምላኩንና መብቶቹን፣ እንዲሁም በርሱ ላይ ያሉበትን ግዴታዎች እንዴት ሊያውቅ ይችላል? እንዴትስ ያመልከዋል?

የሰው ልጅ አለማዊ ችግሮቹን የሚፈቱለት ጠቢባን ሊያገኝ ይችላል። ለምሳሌ ሲታመም የሚያክሙት፣ ለበሽታው መድሐኒት የሚፈበርኩለት፣ ቤት የሚያንጹለት ወዘተ። ግና ከአምላኩ ጋር የሚያስተዋውቁትንና እንዴት እንደሚያመልከው የሚያብራሩለትን ሰዎች አያገኝም። ምክንያቱም አእምሮ የአላህን ፍላጎት በራሱ ጥረት ሊያውቅ አይችልምና። የአምላክን ይቅርና የመሰሉን ሰው ፍቃድና ሐሳብ እንኳ ሰውየው ሳይነግረው በፊት የመረዳት አቅም የለውም። በመሆኑም ይህ ተግባር አላህ መልእክቱን ያደርሱ ዘንድ የመረጣቸው ነብያትና መልእክተኞች፣ እንደዚሁም የነርሱ ወራሾችና ፈለጋቸውን ተከታዮች የሆኑት ቅን የሐይማኖት መሪዎች ሚናና ተግባር ነው። ምክንያቱም ከነብያት ውጭ ሌሎች ግለሰቦች ከአላህ በቀጥታ መልእክት ሊደርሳቸው አይችልምና። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَا كَانَ لِبَشَرٍ أَن يُكَلِّمَهُ ٱللَّهُ إِلَّا وَحْيًا أَوْ مِن وَرَآيِٕ حِجَابٍ أَوْ يُرْسِلَ رَسُولًا فَيُوحِيَ بِإِذْنِهِۦ مَا يَشَآءُ ۚ إِنَّهُۥ عَلِيٌّ حَكِيمٌ ﴿٥١﴾ ﴾ الشورى: ٥١

*«የሰው ልጅ አላህ ሊያናግረው ተገቢው አይደለም፣ በራዕይ ወይም ከግርዶ በስተጀርባ ወይም ደግሞ መልዕክተኛን በመላክና የሚሻውን በራዕይ በመግለጽ ቢሆን እንጅ። እርሱ ልዑልና ጥበበኛ ነው።» (አል ሹራ 51)*

ስለዚህም የአላህን ሕግ ለሰው ልጆች የሚያደርሱ አምባሳደሮች ያስፈልጋሉ። እነርሱም የአላህ ነብያትና መልእክተኞች ናቸው። ይህውም መላኢካ ለነብዩ የአላህን መልእክት ያደርሳል። ነብዩም



መልእክቱን ለሰው ልጆች ያስተላልፋል። ግና መላኢካ ለእያንዳንዱ ግለሰብ እየዞረ መልእክት የሚያስተላልፍበት ሁኔታ የለም። የመላእክት አለምና የሰው ልጅ ዓለም ይለያያሉና።

﴿ ٱللَّهُ يَصْطَفِي مِنَ ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ رُسُلًا وَمِنَ ٱلنَّاسِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌۢ بَصِيرٌ ﴿٧٥﴾ ﴾ الحج: ٧٥

*«አላህ ከመላእክት መልዕክተኞችን ይመርጣል። ከሰው ልጆችም እንዲሁ። አላህ ሰሚ፣ ተመልካች ነው።» (አል ሃጅ 75)*

ለሰው ልጆች የተላኩ መልእክተኞች ከራሳቸው ከሰው ልጆች ወገን እንዲሆኑ አላህ በጥበቡ ወሰነ። ይህም የሆነበት ሰበቡ ሐሳባቸውን በቀላሉ እንዲረዷቸውና በአርአያነትም እንዲከተሏቸው ለማድረግ ነው። የመላእክት መልእክተኛ ለሰው ልጅ ቢላክ ኖሮ እርሱን መጋፈጥና ከርሱ መማር፣ አርአያነቱንም መከተል አይችሉም ነበር።[28]

አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَقَالُوا لَوْلَآ أُنزِلَ عَلَيْهِ مَلَكٌ ۖ وَلَوْ أَنزَلْنَا مَلَكًا لَّقُضِيَ ٱلْأَمْرُ ثُمَّ لَا يُنظَرُونَ ﴿٨﴾ وَلَوْ جَعَلْنَٰهُ مَلَكًا لَّجَعَلْنَٰهُ رَجُلًا وَلَلَبَسْنَا عَلَيْهِم مَّا يَلْبِسُونَ ﴿٩﴾ ﴾ الأنعام: ٨ - ٩

*"ለርሱ (ለሙሐመድ) (ነቢይነቱን የሚያፀድቅ) መልአክ አያወርድለትም ኖሯልን?" አሉ። መልአክ አውርደን ቢሆን ኖሮ ነገሩ በቅጽበት ፍጻሜ ባገኘና ከዚያ እነርሱም ጊዜ ባልተሰጣቸውም ነበር። (መልዕክተኛውን) (ከ)መልአክብናደርገው ኖሮ ሰው ባደረግነውና አሁን ግራ የሚጋቡበትን ነገር (ያንኑም) ግራ እንዲጋቡበት ባደረግናቸው ነበር።» (አል አንዓም 8-9)*

﴿ وَمَآ أَرْسَلْنَا قَبْلَكَ مِنَ ٱلْمُرْسَلِينَ إِلَّآ إِنَّهُمْ لَيَأْكُلُونَ ٱلطَّعَامَ وَيَمْشُونَ فِي ٱلْأَسْوَاقِ ۗ وَجَعَلْنَا بَعْضَكُمْ لِبَعْضٍ فِتْنَةً أَتَصْبِرُونَ ۗ وَكَانَ رَبُّكَ بَصِيرًا ﴿٢٠﴾ وَقَالَ ٱلَّذِينَ لَا يَرْجُونَ لِقَآءَنَا لَوْلَآ أُنزِلَ عَلَيْنَا ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ أَوْ نَرَىٰ رَبَّنَا ۗ لَقَدِ ٱسْتَكْبَرُوا۟ فِيٓ أَنفُسِهِمْ وَعَتَوْ عُتُوًّا كَبِيرًا ﴿٢١﴾ ﴾ الفرقان: ٢٠ - ٢١

*«ከአንተ በፊት የላክናቸው መልዕክተኞች፣ (ሁሉም) ምግብ የሚመገቡና ወደ ገበያ ቦታዎችም የሚመላለሱ ነበሩ። ከፊላችሁንም*

---

[28] ተፍሲር ኢብኑ ከሲር 3/64

*ለከፊሉ ፈተና አደረግን። ትታገሳላችሁን? ጌታህ (ሁሉንም ነገሮች) ተመልካች ነው። እነዚያ ከኛ ጋር መገናኘትን የማይጠብቁት፡- "ለምን መላእክት አልወረዱልንም? ወይም ጌታችንን ለምን (በግሃድ) አናይም?" አሉ። ራሳቸውን (ከልክ በላይ) ተመለከቱ። ታላቅ አመጽንም አመጹ።» (አል ፉርቃን 20-21)*

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ إِلَّا رِجَالٗا نُّوحِيٓ إِلَيۡهِمۡۚ ﴾ النحل: ٤٣

«ከአንተ በፊት ራዕይ የምንገልጽላቸውን ወንዶች እንጅ አልላክንም።» (አል ነህል 43)

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوۡمِهِۦ لِيُبَيِّنَ لَهُمۡۖ ﴾ إبراهيم: ٤

*«ከመልዕክተኞች አንዱንም በሕዝቦቹ ቋንቋ እንጅ አላክንም። (መልዕክቱ ለታዳሚያን በሚገባቸው ቋንቋ) ያብራራላቸው ዘንድ (ይህን አደረግን)። (ኢብራሂም 4)*

ነብያትና የአላህ መልእክተኞች በባህሪያቸው የበሳል አእምሮ፣ የንጹህ ተፈጥሮ፣ የቃልም ሆነ የተግባር እውነተኛነት ባለቤቶች ናቸው። መልእክቱን በታማኝነት ያደርሳሉ። ስብእናቸውን ከሚያጠለሽ ግድፈትም የተጠበቁ ናቸው። አካላቸውም ከአስጸያፊ ጉድለት የጸዳ ነው።[20]

አላህ የስነ ምግባር ምጥቀትን፣ የነፍስ ጽዳትን ሰጥቷቸዋል። በባህሪ ከማንም ይበልጣሉ። ነፍሳቸውም ከሁሉም በላይ የጸዳች ናት። እጆቻቸው ቸሮች ናቸው። አላህ ምርጥ ስነምግባርን ከጥሩ ባህሪ አዋዶ፣ ታጋሽነትን ከእውቀት አዛምዶ፣ በቸርነት፣ በጀግንነትና በፍትሃዊነት አድምቆ ፈጥሯቸዋል። በነዚህ ባህሪያት ከወገኖቻቸው መሐል ጎልተው ይለያሉ። የሷሊህ ሕዝቦች እንዲህ ሲሉ መናገራቸውን ቁርአን ተርኮልናል፡-

﴿ قَالُواْ يَٰصَٰلِحُ قَدۡ كُنتَ فِينَا مَرۡجُوّٗا قَبۡلَ هَٰذَآۖ أَتَنۡهَىٰنَآ أَن نَّعۡبُدَ مَا يَعۡبُدُ ءَابَآؤُنَا ﴾ هود: ٦٢

[29] ለዋሚእ አንዋረል በሪየህ 2/265-305 ይመልከቱ።



*"ሷሊሕ ሆይ! ከዚህ ቀደም በኛ ዘንድ ተስፋ የተጣለብህ ሰው ነበርክ። አባቶቻችን ያመልኩት የነበረውን እንዳናመልክ ትከለክለናለህን?» አሉ(ሁድ 62)*

የሹዓይብ ሕዝቦችም እንዲህ ብለዋል፡-

﴿ أَصَلَوٰتُكَ تَأۡمُرُكَ أَن نَّتۡرُكَ مَا يَعۡبُدُ ءَابَآؤُنَآ أَوۡ أَن نَّفۡعَلَ فِيٓ أَمۡوَٰلِنَا مَا نَشَٰٓؤُاْۖ إِنَّكَ لَأَنتَ ٱلۡحَلِيمُ ٱلرَّشِيدُ ٨٧ ﴾ هود: ٨٧

*"ሹዐይብ ሆይ! አባቶቻችን ያመልኩት የነበረውን እንተው ዘንድ ወይም በገንዘቦቻችን የፈለግነውን እንዳናደርግ ሶላትህ ታዝሃለችን? አንተ (እውነትም) ታጋሽና ቅን አዋቂ ነህ።" አሉት።» (ሁድ 87)*

ነብዩ ሙሐመድ በነብይነት ከመላካቸው በፊት ከወገኖቻቸው መሐል «አል አሚን» (ታማኙ) በሚል ቅጽል ስም ይታወቁ ነበር። አምላካቸውም እንዲህ ሲል ገልጿቸዋል።

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٖ ٤ ﴾ القلم: ٤

*«አንተ የላቀ ሥነ-ምግባር ባለቤት ነህ።» (አል ቀለም 4)*

ከፍጡራኑ መካከል አላህ መልእክቱን እንዲሸከሙና አደራውን እንዲያደርሱ የመረጣቸው የአላህ ምርጥ ሰዎች ናቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ٱللَّهُ أَعۡلَمُ حَيۡثُ يَجۡعَلُ رِسَالَتَهُۥۗ ﴾ الأنعام: ١٢٤

*«አላህ፥ መልዕክቱን የት ማድረግ እንዳለበት አሳምሮ ያውቃል።» (አል አንዓም 124)*

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰٓ ءَادَمَ وَنُوحٗا وَءَالَ إِبۡرَٰهِيمَ وَءَالَ عِمۡرَٰنَ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ٣٣ ﴾ آل عمران: ٣٣

*«አላህ አደምን፣ ኑሕንም፣ የኢብራሂምንም ቤተሰብ፣ የዒምራንንም ቤተሰብ ከዓለማት በላይ መረጠ።» (አል ዒምራን 33)*

# መጭው አለም

ሞት አይቀሬ መሆኑን እያንዳንዱ ሰው ያውቃል። ግና ከሞት በኋላ ምን ይከሰታል? ፍጻሜውስ ምን ይሆን? ይድናል ወይስ ይከስራል? ለሚሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን ምላሽ ማንም አያውቅም።

አብዛኞዎቹ የዓለማችን ሕዝቦች ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩን፣ ለበጎም ለክፉም ስራዎቻቸው ምርመራ ተደርጎ ተገቢው ሽልማት ወይም ቅጣት እንደሚሰጣቸውም ያምናሉ። ይህን አጀንዳ ከሞት መቀስቀስንና መመርመርን ጤነኛ አእምሮዎች ያጸድቁታል። መለኮታዊ ሕግጋት ይቀበሉታል።ይህ እምነት ከሦስት መርሆዎች ላይ ይታነጻል፡-

1) የአላህን እውቀተ ምሉእነት ከማጽደቅ፣

2) የአላህን ያሻውን የማድረግ ችሎታ ከማጽደቅና

3) የጥበቡን ምሉእነት ከማጽደቅ ላይ ይገነባል።[35]

የመጭውን ዓለም ሕልውና አእምሮም ስነዳዊም መረጃዎች ሁሉ አጽድቀውታል። እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል፡-

1) የሰማይና የምድር መፈጠር ከሞት በኋላ መቀስቀስን ያረጋግጣሉ። ይህን ግዙፍ ዩኒቨርስ ያነጸ አምላክ ሙታንን መቀስቀስ አይሳነውምና። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿أَوَلَمْ يَرَوْا أَنَّ اللَّهَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ وَلَمْ يَعْيَ بِخَلْقِهِنَّ بِقَادِرٍ عَلَىٰ أَنْ يُحْيِيَ الْمَوْتَىٰ بَلَىٰ إِنَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ ﴿٣٣﴾﴾ الأحقاف: ٣٣

*«ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው፣ እነርሱን በመፍጠሩም ድካም ያልተሰማው አላህ ሙታንን ሕያው ማድረግ እንደሚችል አላወቁምን? በእርግጥም ይህን ማድረግ የሚሳነው አይደለም። እርሱ ሁሉንም ነገር ቻይ ነውና።» (አል አሕቃፍ 33)*

﴿أَوَلَيْسَ الَّذِي خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ بِقَادِرٍ عَلَىٰ أَنْ يَخْلُقَ مِثْلَهُمْ بَلَىٰ وَهُوَ الْخَلَّاقُ الْعَلِيمُ ﴿٨١﴾﴾ يس: ٨١

[35] አልፋዋኢድ ቢን አልቀይም ገጽ 66.7



*«ያ ሰማያትንና ምድርን (ያለ አጋር) የፈጠረ (አምላክ) መሰላቸውን መፍጠር አይችልምን? በፍፁም (አይሳነውም)። እርሱ ሁሉንም ነገር ፈጣሪ፣ (ሁሉንም ነገር) ዐዋቂ ነው።» (ያሲን 81)*

2) ፍጡራንን ከሌላ ሳይቀዳና ሳያስመስል የፈጠረ አምላክ ከሞት በኋላ እንደገና ደግሞ መፍጠር አይሳነውም። አንድን ነገር ካልነበረበት ማስገኘት የቻለ አምላክ መልሶ መገጣጠም አይከብደውም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَهُوَ الَّذِي يَبْدَأُ الْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُ وَهُوَ أَهْوَنُ عَلَيْهِ وَلَهُ الْمَثَلُ الْأَعْلَىٰ فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ وَهُوَ الْعَزِيزُ الْحَكِيمُ ﴿٢٧﴾﴾ الروم: ٢٧

*«እርሱ ፍጡራንን ከምንም የሚያስገኝ፣ ከዚያም የሚመልሳቸው (አምላክ) ነው። ይህ ለእርሱ እጅግ ቀላል (ተግባር) ነው። እርሱ የላቁ ባሕሪያትጅ መገለጫዎች አሉት። በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያሉ ሁሉ (በነኝህ ባሕሪያት ይገልፁታል)። እርሱ ኃያልና ጥበበኛ ነውና። » (አል ሩም 27)*

﴿وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِيَ خَلْقَهُ قَالَ مَنْ يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ ﴿٧٨﴾ قُلْ يُحْيِيهَا الَّذِي أَنْشَأَهَا أَوَّلَ مَرَّةٍ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيمٌ ﴿٧٩﴾﴾ يس: ٧٨ - ٧٩

*«ለኛ ምሳሌ አደረገልን። አፈጣጠሩንም ዘነጋ። "የበሰበሱ አጥንቶችን ሕያው የሚያደርግ ማን ነው?" አለ። ሙሐመድ ሆይ! በል፦ "ያ መጀመሪያ ከምንም ያስገኛቸው (አምላክ) ሕያው ያደርጋቸዋል። እርሱ ፍጡራንን ሁሉ ጠንቅቆ ዐዋቂ ነው።" (ያሲን 78-79)*

3) አላህ የሰውን ልጅ አሁን ባለው ቅርጽ፣ አቅምና ባህሪ፣ ከአጥንትና ከደም፣ ከጅማትና ከነርቭ አዋቅሮ፣ እውቀትን፣የማየት ችሎታን፣ መርጦ የመስራት ክህሎትን፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀትን አስታጥቆ ባማረ አቋም መፍጠሩ ሙታንን ለመቀስቀስ የሚያስችል ወሰን የለሽ ችሎታ እንዳለው አመላካች ነው።

4) አላህ በዚህች ዓለም ውስጥ ሙታንን በመቀስቀስ ከሞት በኋላ የማስነሳት ችሎታ እንዳለው አሳይቷል። ይህም አላህ በላካቸው መለኮታዊ መጽሐፍቱ ውስጥ ተዘክሯል። ከነዚህ ሙታንን የማስነሳት ታሪኮች መካከል በነቢዩ ኢብራሂምና በሌሎች ነብያት የተፈጸሙት በርካታ ክስተቶች ይጠቀሳሉ።

5) የተበታተኑ ነገሮችን ሰብስቦ አንድ ከማድረግ ጋር የሚመሳሰሉ ክስተቶች ከሞት በኋላ መነሳት ለመኖሩ መረጃ ይሆናሉ። ይህውም፡

ሀ) አላህ የሰውን ልጅ የፈጠረው በመላ የሰውነት ክፍል ተሰራጭቶ የነበረውን የዘር ፈሳሽ በመሰብሰብ ነው። ለዚህም ነው በጾታዊ ግንኙነት ወቅት መላ አካሉ የሚሳተፈውና እርካታውን የሚቋደሰው። አላህ ይህን የዘር ፈሳሽ ከሁሉም የአካላችን ክፍሎች ሰብስቦ በብልት በኩል ወደ ማሕጸን እንዲፈስ ያደርገዋል።

ከርሱ የሰውን ልጅ ይፈጥራል። የተበታተነን የዘር ፈሳሽን ሰብስቦ ሰውን ከርሱ ከፈጠረ በሞት አማካይነት የተበታተነን አካሉን መሰብሰብ እንዴት ይሳነዋል? አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿أَفَرَءَيۡتُم مَّا تُمۡنُونَ ٥٨ ءَأَنتُمۡ تَخۡلُقُونَهُۥٓ أَمۡ نَحۡنُ ٱلۡخَٰلِقُونَ ٥٩﴾ الواقعة: ٥٨ - ٥٩

*«(ወደ ሴቶች ማኅፀን) የምትረጩትን (ፍትወት) አያችሁን? የምትፈጥሩት እናንተ ናችሁ ወይስ እኛ ነን ፈጣሪዎቹ?» (አል ዋቂዓህ 58-59)*

ለ) እንዲት ፍሬ ወይም ቅንጣት ከሞተ መሬት ላይ ስታርፍና ውሃና አፈር ሲያገኛት መበላሸት ነበረባት። ምክንያቱም ውሃውና አፈሩ ተደባልቆ ቀርቶ እንዳቸው ብቻ እንኳ ለማበላሸት በቂ ናቸው። ግና ፍሬው ወይም ቅንጣቱ አይበላሽም። ሕይወቱ ተጠብቆ ይቆያል። እያደር እጽዋት ሆኖ ይበቅላል። ይህ ትእይንት የአላህን የተሟላ ጥበብና ችሎታ አያሳይምን? ይህ ሁሉን ቻይና ጥበበኛ የሆነ አምላክ የተበታተነን የሰው አካል ሰብስቦ ከሞት ማስነሳት እንዴት ይሳነዋል? አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿أَفَرَءَيۡتُم مَّا تَحۡرُثُونَ ٦٣ ءَأَنتُمۡ تَزۡرَعُونَهُۥٓ أَمۡ نَحۡنُ ٱلزَّٰرِعُونَ ٦٤﴾ الواقعة: ٦٣ - ٦٤

*«የምትዘሩትንም አያችሁን? የምታበቅሉት እናንተ ናችሁ ወይስ እኛ ነን አብቃዮቹ?» (አል ዋቂዓህ 63-64)*

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِن كُنتُمۡ فِي رَيۡبٖ مِّنَ ٱلۡبَعۡثِ فَإِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن تُرَابٖ ثُمَّ مِن نُّطۡفَةٖ ثُمَّ مِنۡ عَلَقَةٖ ثُمَّ مِن مُّضۡغَةٖ مُّخَلَّقَةٖ وَغَيۡرِ مُخَلَّقَةٖ لِّنُبَيِّنَ لَكُمۡۚ وَنُقِرُّ فِي ٱلۡأَرۡحَامِ مَا



نَشَآءُ إِلَىٰٓ أَجَلٖ مُّسَمّٗى ثُمَّ نُخۡرِجُكُمۡ طِفۡلٗا ثُمَّ لِتَبۡلُغُوٓاْ أَشُدَّكُمۡۖ وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ وَمِنكُم مَّن يُرَدُّ إِلَىٰٓ أَرۡذَلِ ٱلۡعُمُرِ لِكَيۡلَا يَعۡلَمَ مِنۢ بَعۡدِ عِلۡمٖ شَيۡـٔٗاۚ وَتَرَى ٱلۡأَرۡضَ هَامِدَةٗ فَإِذَآ أَنزَلۡنَا عَلَيۡهَا ٱلۡمَآءَ ٱهۡتَزَّتۡ وَرَبَتۡ وَأَنۢبَتَتۡ مِن كُلِّ زَوۡجِۭ بَهِيجٖ ٥﴾ الحج: ٥

*«የሰው ልጆች ሆይ! (ከሞት በኋላ) መቀስቀስን ከተጠራጠራችሁ (አፈጣጠራችሁን አስተውሉ)። እኛ ከአፈር ፈጠርናችሁ። ከዚያም ከፍትወት ጠብታ፣ ከዚያም ከረጋ ደም፣ ከዚያም (በከፊል) ቅርጽ ከያዘና (በከፊልም) ካልያዘ የተላመጠ የሚመስል (ቁራጭ) ሥጋ ፈጠርናችሁ። (ወሰን የለሽ ችሎታችንን) ልንገልጽላችሁ (ይህን ፈፀምን)። በማኅፀን ውስጥም የምንሻውን እስከተወሰነ ወቅት ድረስ እናረጋለን። ከዚያም ሙሉ ጥንካሬን ትጎናፀፉ ዘንድ (እናሳድጋችኋለን)። ከመካከላችሁ (በለጋነቱ) የሚሞት አለ፤ ያወቀውን ሁሉ (ዘንግቶ) ምንም ነገር እንዳላወቀ ወደሚሆንበት የጃጀ እድሜ ድረስ እንዲቆይ የሚደረግም አለ። ምድርንም ደረቅ (በድን) ሆና ታያታለህ። ውሃ በርሷ ላይ በምናወርድላት ጊዜም ትንቃቃለች። ትዳብራለች። ውብ የሆኑ የእጽዋት ዓይነቶችን ሁሉም ታበቅላለች።» (አል ሐጅ 5)*

6) ጥበበኛና ሐያል የሆነ አምላክ የሰውን ልጅ ለቀልድና ለጨዋታ ሊፈጥር፣ እንዲሁም ሊተዋቸው ተገቢው አይደለም። እንዲህ ብሏል፡

﴿وَمَا خَلَقۡنَا ٱلسَّمَآءَ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَا بَٰطِلٗاۚ ذَٰلِكَ ظَنُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْۚ فَوَيۡلٞ لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنَ ٱلنَّارِ ٢٧﴾ ص: ٢٧

*«ሰማይንና ምድርን፣ በመካከላቸውም ያሉትን ፍጡራን በከንቱ አልፈጠርንም። ይህ የነዚያ የካዱት ሰዎች እሳቤ ነው። ከሓዲያን ከእሳት ወዮላቸው።» (ሷድ 27)*

ፍጡራንን የፈጠረው ለላቀ ጥበብ እና ለከበደ ዓላማ መሆኑ ግልጽ ነው፣ እንዲህ ብሏል፡

﴿وَمَا خَلَقۡتُ ٱلۡجِنَّ وَٱلۡإِنسَ إِلَّا لِيَعۡبُدُونِ ٥٦﴾ الذاريات: ٥٦

*«ጂንንንትንም ሰዎችንም ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።» (አል ዛሪያት 56)*

ከዚህ ጥበበኛ አምላክ ዘንድ የታዘዙትና የወነጀሉት እኩል ቢሆኑ አይችሉም። እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَمْ نَجْعَلُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ كَٱلْمُفْسِدِينَ فِى ٱلْأَرْضِ أَمْ نَجْعَلُ ٱلْمُتَّقِينَ كَٱلْفُجَّارِ ﴿٢٨﴾ ﴾ ص: ٢٨

*«እነዚያን ያመኑትንና መልካምን የሚሠሩትን፣ እንደነዚያ በምድር ላይ ብክለትን እንደሚያስፋፉት እናደርጋለን? ወይስ አላህን ፈሪዎችን እንደ አመፀኞች እናደርጋለን?» (ሷድ 28)*

ይህም በመሆኑ የጥበቡ ምሉእነትና የሐያልነቱ አንዱ መገለጫ የሰው ልጆችን ለእያንዳንዳቸው የስራቸውን ዋጋ ሊከፍላቸው መቀስቀሱ፣ በጎ የሰሩትን መሸለሙና ከፉዎችን መቅጣቱ ነው። እንዲህ ብሏል፡-

﴿ إِلَيْهِ مَرْجِعُكُمْ جَمِيعًا ۖ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقًّا ۚ إِنَّهُۥ يَبْدَؤُا۟ ٱلْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ لِيَجْزِىَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ بِٱلْقِسْطِ ۚ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَهُمْ شَرَابٌ مِّنْ حَمِيمٍ وَعَذَابٌ أَلِيمٌۢ بِمَا كَانُوا۟ يَكْفُرُونَ ﴿٤﴾ ﴾ يونس: ٤

*«(በኋላም) መመለሻችሁ ወደርሱ ብቻ ነው። የአላህ ቃልኪዳን እውነትና የተረጋገጠ ነው። እርሱ የመፍጠርን ሂደት ይጀምራል። ከዚያም፣ ለእነዚያ ላመኑትና መልካም ሥራዎችን ለሠሩት ፍትሃዊ ምንዳን ሊሰጣቸ፣ (ፍጡራኑን ከሞት) ይመልሳል። ግና እነዚያ የካዱት ወገኖች ብክህደታቸው ሳቢያ የፍል ውሃ መጠጥ፣ አሳማሚ ቅጣትም ይጠብቃቸዋል።» (ዩኑስ 4)*

በመጭው ዓለም መኖር በግለሰቡም ሆነ በማሕበረሰቡ ሕይወት ውስጥ እጅግ በርካታ በጎ ተጽእኖዎች አሉት። ይህውም፡-

1) የሰው ልጅ የዚያን ቀን የሚያገኘውን የአላህ ምንዳ በመሻት አላህን እንዲታዘዝ፣ ቅጣቱን በመፍራትም ከሐጢአት እንዲታቀብ ያደርገዋል።

2) በመጭው ዓለም ማመን ለአማኞች መጽናኛ ነው። የመጭውን ዓለም ተስፋ በማድረግ በዚህች ዓለም ውስጥ ለሚያልፋቸው ድሎት እንዳይቆጩ ይረዳቸዋል።



3) በመጭው ዓለም ማመን የሰው ልጅ ከሞት በኋላ ፍጻሜውን እንዲያውቅ ያደርገዋል። የመልካምም ሆነ የከፋ ስራውን ዋጋ እንደሚያገኝ፣ ለምርመራ ከአላህ ፊት እንደሚቆም፣ የታደለ እንደሚሳካለት፣ የበደላቸው ሰዎች ካሉም እንደሚካሱ ጠንቅቆ ያውቃል።

4) በመጭው ዓለም ማመን ሌሎችን ከመበደል፣ መብታቸውን ከመጋፋት እንዲጠነቀቅ ያደርገዋል። ይህ እምነት ያላቸው ሰዎች እርስ በርስ አይበዳደሉም። መብቶቻቸውም ይጠታበሉ።

5) በመጭው ዓለም ማመን ሰውየው ይህችን ዓለም እንደ አንድ የሕይወት እርከን ብቻ እንጂ እንደ ሙሉ ሕይወት አድርጎ እንዳያያት ይረዳዋል።

በመጨረሻም «ዋይን ቢት» የተሰኘ አሜሪካዊ የሰጠውን ምስክርነት እናስነብባችኋለን። ሰውየው ክርስትያን ነበር። በአንዲት ቤተክርስትያን ውስጥም ይሰራ ነበር። በኋላ ላይ ሰለመ። በመጭው ዓለም የማመንን ጥቅም በመረዳቱም እንዲህ ሲል መሰከረ፡-

«በአሁኑ ሰአት ሕይወቴን ሙሉ አእምሮዬን ሲያስጨንቁ ለኖሩት አራት ጥያቄዎች መልሳቸውን በትክክል አውቃለሁ። እነርሱም እኔ ማን ነኝ? ምን እፈልጋለሁ? ለምን መጣሁ? ወደየትስ እሄዳለሁ? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው።»[36]

[36] አልዳእዋ ከተሰኘው የሳኡዲ መጽሔት ቁጥር 1722 የ19/09/1429 ሂጅሪያ እትም ገጽ 37

# የነብያት ትምህርት መሠረቶች

ሁሉም ነብያት በተወሰኑ መሠረታዊ ትምህርቶች ላይ አተኩረው አስተምረዋል።[37] በአላህ፣ በመላኢኮች፣ በመጽሐፍት፣ በመልእክተኞች፣ በመጭው ዓለምና በቀደር መልካምም ሆነ ክፉ ማመን ይጠቀሳሉ። አላህን በርሱ ላይ ሌላ አካል ሳያጋሩ በብቸኝነት ማምለክ፣ የርሱን መንገድ መከተልና ከርሱ ጎዳና ተቃርኖ አለመገኘት የትኩረታቸው መስኮች ናቸው። ከአራት የወንጀል ዘርፎች ማለትም ከግልጽም ,ከስውርም ጸያፍ ድርጊት፣ ከሐጢአት፣ ከወሰን አላፊነት፣ በአላህ ከማጋራትና ከጣኦት አምልኮ መታቀብንም በዋናኛነት አስተምረዋል። አላህ ሚስትም ሆነ ልጅ፣ አጋርም ሆነ ቢጤ እንደሌለው ሰብከዋል። በአላህ ላይ ተገቢ ያልሆነ ቃል እንዳይነገር አስተምረዋል። ልጅን መግደልን፣ ነፍስን ያለ አግባብ ማጥፋትን አቅበዋል። አራጣን፣ የየቲምን ገንዘብ ያለ አግባብ መብላትን ከልክለዋል። ቃልን መሙላትን፣ ሚዛንን ማስተካከልን፣ የወላጆችን መብት መጠበቅን፣ በሰዎች መካከል ፍትሃዊ መሆንን፣ በቃልም ሆነ በተግባር እውነተኛነትን አዘዋል። ማባከንን፣ ኩራትንና የሰዎችን ገንዘብ ያለ አግባብ መብላትንም ኮንነዋል።

ኢብኑል ቀይም እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፡-

«መለኮታዊ ሕግጋት በመሠረታዊ ባህሪያቸው ይመሳሰላሉ። አእምሮ በጎነታቸውን ያጸድቀዋል። አሁን ከተደነገጉበት ሁኔታ ውጭ ቢሆኑ ኖሮ ከጥበብ፣ ለሰው ልጅ ፋይዳ ከማስገኘትና ከእዝነት ክልል በወጡ ነበር። አሁን ካሉበት በተለየ ሁኔታ ሊመጡ ፈጽሞ አይችሉም።»

﴿ وَلَوِ ٱتَّبَعَ ٱلْحَقُّ أَهْوَآءَهُمْ لَفَسَدَتِ ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلْأَرْضُ وَمَن فِيهِنَّ ﴾ المؤمنون: ٧١

*«እውነት ከንቱ ስሜቶቻቸውን የሚከተል ቢሆን ኖሮ ሰማያትና ምድር፣ እንዲሁም በውስጣቸው ያሉ (ፍጡራን) በተበላሹ ነበር።» (አል ሙእሚኑን 71)*

[37] እነዚህ መርሆዎች በአልበቀራህ 285-286፣ በአልአንዓም 151-153፣ በአል አእራፍ 35ና በአል ኢስራእ 23-37 ተገልጸዋል።



መለኮታዊ ሕግጋት አሁን ካሉበት በተለየ መልኩ ሊሆኑ የመቻላቸውን ነገር ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው እንዴት ሊያስብ ይችላል?»[38]

ይህም በመሆኑ የሁሉም ነብያት ሐይማኖት አንድ አይነት ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلرُّسُلُ كُلُوا۟ مِنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَٱعْمَلُوا۟ صَٰلِحًا ۖ إِنِّى بِمَا تَعْمَلُونَ عَلِيمٌ ﴿٥١﴾ وَإِنَّ هَٰذِهِۦٓ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَٰحِدَةً وَأَنَا۠ رَبُّكُمْ فَٱتَّقُونِ ﴿٥٢﴾ ﴾ المؤمنون: ٥١ - ٥٢

*"እናንተ መልዕክተኞች ሆይ! መልካም ነገሮችን (ሁሉ) ተመገቡ። በጎ ሥራንም ሥሩ። እኔ የምትሠሩትን (ሁሉ) ዐዋቂ ነኝ።ይህች ሕዝባችሁ አንድ ሕዝብ ናት። እኔም (ብቸኛ) አምላካችሁ ነኝ። ስለዚህም ፍሩኝ።» (አል ሙእሚኑን 51-52)*

﴿ شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحًا وَٱلَّذِىٓ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ وَمَا وَصَّيْنَا بِهِۦٓ إِبْرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓ ۖ أَنْ أَقِيمُوا۟ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُوا۟ فِيهِ ﴾ الشورى: ١٣

*«ከሃይማኖት ያን ኑሕን ያዘዘበትን፣ ወዳንተም ያወረድነውንና ኢብራሂምንም፣ ሙሳንም፣ ዒሳንም ያዘዝንበትን ደነገገላችሁ። (ሁሉንም)፡-"በዚህ ሃይማኖት ላይ ፀንታችሁ ተገኙ። በርሱ ላይ አትለያዩ።" (በማለት አዘዝን)።» (አል ሹራ 13)*

የሐይማኖት ዋነኛ አላማ የሰው ልጆችን ለተፈጠሩለት አላማ ማብቃት ነው። እርሱም አምላካቸውን በርሱ ላይ ምንንም አካል ሳያጋሩ እንዲያመልኩት ማድረግ ነው።[39]

ሐይማኖት መፈጸም ያለባቸውን ግዴታዎች እና መብቶቻቸውን ይደነግግላቸዋል። ወደዚህ ዓላማ የሚያደርሱ መንገዶችን ያሳያቸዋል። በመለኮታዊ ጎዳና አማካይነት የአላህን ውዴታና የሁለቱን አለማት ደስታ ያገኙ ዘንድ ይረዳቸዋል። በዚህ ጎዳና መሠረት የሰው ልጅ ማንነት ከሁለት አይሰነጠቅም። በመንፈስና በስጋ፣ በዚህችና በመጭው አለም መካከል ጥልና ግጭት ተፈጥሮ የሰውን ልጅ

[38] ሚፍታሁ ዳረ ሰአዳህ 2/383
[39] መጅሙዓል ፈታዋ 2/6

# የነብይነት መቋጨት

ባለፉት ገጾች የነብይነትን ምንነትና መልክቶች፣ የነብያትን ተአምራትና የነቢዩ ሙሐመድን ነብይነት ማረጋገጫዎች ተመልክተናል። ስለ ነብይነት መቋጨት ማውጋት ከመጀመራችን በፊት አላህ አንድን ነብይ የሚልከው የሚከተሉት ምክንያቶች ሲከሰቱ ብቻ መሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡-

1) አንድ ነቢዩ ለአንድ አካባቢና ሕዝብ ብቻ ሲላክ እና ሌሎች ሕዝቦች መልእክቱን እንዲያደርሱ ሳይታዘዙ ሲቀሩ አላህ ለአጎራባች ሕዝቦችም ሌላ መልእክተኛ ይልካል።

2) ቀድሞ የመጣው መልእክተኛ ትምህርት ሲጠፋ አላህ ትምህርቱን ለማደስ ሌላ ነብይ ይልካል።

3) ቀድሞ የተላከው ነብይ ሕግጋት ለተላከበት ዘመን ብቻ ተስማሚ ሲሆኑና ለቀጣዮቹ ዘመናት ተስማሚ ሳይሆን ሲቀር አላህ ከቦታውና ከጊዜው ጋር የሚጣጣም ሕግና ስርዓት የሚያስተምር ሌላ መልእክተኛ ይልካል።

አላህ ነቢዩ ሙሐመድን ለሰው ልጆች ባጠቃላይ ለመላክ በጥበቡ ወስኗል። ትምህርታቸውንም ለየትኛውም ቦታና ጊዜ ተስማሚ አድርጎታል። እንዳይበረዝና እንዳይከለስም ጠብቆታል። እናም የሰዎችን ሕይወት የሚቀይር ሕያውና ከጉድፍና ከመበረዝ የጸዳ መልእክት አድርጎታል። ይህም በመሆኑ እርሳቸውን በመላክ ነብይነትን ቋጭቷል።[43]

አላህ ለነብዩ ሙሐመድ ከሰጣቸው የተለየ ችሮታ መካከል እርሳቸውን የነብያት መቋጫ ማድረጉ ይጠቀሳል። በርሳቸው መለኮታዊ መልእክትን ሞልቷል። ሕግጋትን ደምድሟል። የነብያትን ግንብ አጠናቋል። በርሳቸው መነሳት ተከታዩ የእየሱስ ትንቢት ፍጻሜ አግኝቷል።

[43] ዓቂደቱ ጣሃውያ ገጽ 156



«ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ፤ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ፤ ለዓይኖቻችንም ድንቅ ነህ፤ የሚለውን ከቶ በመጽሐፍ አላነበባችሁምን?»[44]

ቄስ አብራሃም ካሊል፣ ይህ የእየሱስ ንግግር ከተከታዩ የነቢዩ ሙሐመድ ቃል ጋር ተመሳሳይ መሆኑን አጽድቀዋል፡-

«የኔና ከኔ በፊት የተነሱ ነብያት ምሳሌ አንድ ቤት እንዳነጸ ሰው ምሳሌ ነን። ሰውየው ቤቱን አሳምሮ ሰራ። ግና የአንዲት ጡብ ማኖሪያ ያህል ክፍተት በአንድ ማእዘን ላይ ይቀረው ነበር። ቤቱን የሚጎበኙ ሁሉ በቤቱ አሰራር ይደነቃሉ። ይህች ቀዳዳ በአንዲት ጡብ ብትደፈን የበለጠ ያማረ ይሆናል የሚል አስተያየትም ይሰጣሉ። ይህች ጡብ እኔ ነኝ። እኔ የነብያት መቋጫ ነኝ።»[45] (ቡኻሪ)

ይህ ቄስ በኋላ ላይ ሰልሟል።

ይህም በመሆኑ አላህ ለነብዩ ሙሐመድ የሰጣቸውን መጽሐፍ ከቀደምት መጽሐፍት ሁሉ የበላይና እነርሱን የሚሽር አደረገው። ሕግና ስርዓታቸውንም የጥንት ሕጎችን ሁሉ የሚሽር አደረገው። እንዳይበረዝና እንዳይከለስም የመጠበቁን ሐላፊነት ራሱ ወሰደ። ቁርአን ከትውልድ ትውልድ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ በቃልም በጽሑፍም ተላለፈ። የነብዩ የሕይወት ፈለግ የሆነው ሱናም እንደዚሁ ከትውልድ ትውልድ በአስተማማኝ አኳኋን ተላለፈ።

የዚህ ሕግና መልእክት፣ እንዲሁም የአምልኮ ስርዓት አተገባበርም በአስተማማኝ ሁኔታ ከትውልድ ትውልድ ተላለፈ።

የነብዩ ሙሐመድን ታሪክ የሚያወሱ የታሪክና የሐዲስ መጽሐፍትን ስናነብ ባልደረቦቻቸው ንግግራቸውንና ተግባራቸውን አንድም ሳያጓድሉ በመጠበቅ ለሰው ልጆች እንዳስተላለፉት እንረዳለን። የአምልኮ ስርዓታቸውን፣ ትግልና ጥረታቸውን፣ ውዳሴያቸውን፣ ምህረት አለማመናቸውን፣ ትህትናቸውን፣ ጀግንነታቸውን፣ ከባልደረቦቻቸው ጋር የነበራቸውን መልካም ግንኙነት፣ የእንግዳና

[44] የማቴዎስ ወንጌል ም 21 ቁ 42

[45] ሙሐመድ በኦሪት፣ በወንጌልና በቁርአን ገጽ 73

የልውክ አቀባበላቸውን አስተላልፈውልና። ደስታና ሐዘናቸውን፣ የጉዞና የሐገር ቤት ሕይወታቸውን፣ የአመጋገብ፣ የአጠጣጥና የአለባበስ ስርዓታቸውን፣ ሲተኙና ሲነቁ የሚፈጽሙትን ሁሉ ሳያጓድሉ አውርሰውናል።

ይህን ሁሉ ስናይ ይህ ሐይማኖት በእርግጥም የአላህ ጥበቃ ለቅጽበት ያልተለየው በመሆኑ ላይ እርግጠኞች እንሆናለን። በእርግጥም የመጨረሻ መልእክተኛ እና የነብያት መቋጫ መሆናቸውንም እንገነዘባለን። አላህ ለነብያት መደምደሚያ፣ የመልእክት መጠናቀቂያ፣ መሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ ገልጾልናል።

﴿ مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمًا ﴿٤٠﴾ ﴾ الأحزاب: ٤٠

*«ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ መካከል የአንዱም አባት አይደለም። ግን (እርሱ) የአላህ መልዕክተኛና የነቢያት መቋጫ ነው። አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ ነውና።» (አል አህዛብ 40)*

ነብዩ ሙሐመድም እንዲህ ብለዋል፡-

«ለሰው ልጆች ባጠቃላይ ተላኩ። ነብይነትም በኔ ተቋጨ።» (አህመድና ሐኪም)

እነሆ የእስልምናን ምንነት፣ ምንጮቹንና መሠረቶቹን ቀጥሎ እናብራራለን።



# የኢስላም ትርጉም

መዝገበ ቃላትን ስትፈትሽ ኢስላም የሚለው ቃል ትርጉሙ፡ «የአንድን አካል ትእዛዝና እቀባዎች ያለ ተቃውሞ መፈጸም፣ ለዚያ አካል ፈቃድ ማደርና መገዛት» የሚል ሆኖ ታገኘዋለህ።

አላህ እውነተኛውን ሐይማኖት ኢስላም ብሎ የሰየመው የመልእክቱ ፍሬ ነገር አላህን ያለ ተቃውሞ መታዘዝና ለርሱ ፈቃድ ያለ ማንገራገር ማደር፣ አምልኮን ለርሱ ብቻ ማድረግ፣ መልእክቱን አምኖ መቀበልና በርሱ ማመን በመሆኑ ነው። ከዚህ የተነሳ ኢስላም የሚለው ቃል ነቢዩ ሙሐመድ ላመጡት ሐይማኖትም በመጠሪያነት እንዲያገለግል ተደርጓል።

## እስልምናን ማስተዋወቅ

ኢስላም በዚህ ስያሜ ለምን ተጠራ? በምድር ላይ ያሉ የተለያዩ ሐይማኖቶች ስያሜዎቻቸውን ያገኙት ከመስራች ሰብእናዎቻቸው ወይም ከተለየ ሕዝብ ስያሜ ነው። ለምሳሌ ክርስትና ከክርስቶስ፣ ቡድሂዝም ከመስራቹ ከቡድሃ፣ የዘራድሽ እምነት ከመስራች ከዘራድሽ፣ አይሁዳነት አይሁድ ከተሰኘው ማሕበረሰብ ወዘተ ስያሜያቸውን እንዳገኙ መገንዘብ ይቻላል።

ኢስላም ግን ከዚህ ይለያል። ስያሜው ከአንድ ግለሰብ ወይም ሕዝብ ስያሜ ጋር የተሳሰረ አይደለም። የተለየ መልእክትና ይዘት ያለው ቃል ነው። የእስልምና ስያሜ እንዲህ መሆኑ ሐይማኖቱ የተመሠረተው ለአንድ የተለየ ግለሰብ ወይም ሕዝብ ሳይሆን የምድር ላይ ነዋሪዎችን ባጠቃላይ በመልእክቱ ለማስዋብ መሆኑን ያመለክታል። ለአላህ ያደረ እና ለፈቃዱ የተገዛ ማንኛውም ሰው፣ ዘር፣ ጾታ፣ የቆዳ ቀለም፣ ቦታ ሳይለይ፣ ሙስሊም ይሰኛል። በየትኛውም ዘመንና ቦታ የሚገኝ የትኛውም ሰው ይህን ባህሪ መጎናጸፍ ይችላል።

## የእስልምና ምንነት

በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር ለአንድ በተለየ ሕግ ያደረ፣ አንድን የተለየ ስርዓትና ምህዋር የሚከተል መሆኑ ግልጽ

ነው። ጸሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ምድርና ሰማይ ተፈጥሯዊውን ሕግና የጉዞ ስርዓት ተከትለው ይጓዛሉ። ቅንጣት ታክል ከሕጉ ዝንፍ አይሉም። የሰው ልጅ ራሱ በአካላዊ ማንነቱ ለተፈጥሯዊ ሕጎች ያደረ ሆኖ ታገኘዋለህ።

የሚተነፍሰው አየር፣ ውሃ ወይም ምግብ፣ ብርሃንና ሙቀት የሚከጅለው አላህ ለሕይወቱ ባስቀመጠለት ሕግና ስርዓት መሰረት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። መላ አካሉ ለዚህ ሕግ ያደረ ነው። የአካል ክፍሎቹ ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በአላህ በተወሰነላቸው መሠረት ብቻ ነው።

ከታላቁ ፕላኔት እስከ ትንሹ አቶም ድረስ ያሉ ሁሉም የዚህ ዩኒቨርስ አካሎች ያደሩለት ይህ መለኮታዊ ሕግና ተፈጥሯዊ ስርዓት የተላቀው እና ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ የዘረጋው ስርዓት ነው። እናም በሰማያትና በምድር ውስጥ ያሉ ፍጡራን ሁሉ ለመለኮታዊ ሕግና ስርዓት ተገዥዎች በመሆናቸው ኢስላም የመላው ዩኒቨርስ ሐይማኖት ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ኢስላም ማለት ለአላህ ትእዛዝና እቀባ ያለ ተቃውሞ ተገዥ መሆን ማለት ነው። ከአሁን ቀደም እንደገለጽነው በዚህ ትርጉም መሠረት ጸሐይ፣ ጨረቃና ምድር ለአላህ ፈቃድ አድረዋል። አየሩ፣ ውሃው፣ ብርሃኑ፣ ጨለማው፣ ሙቀቱ ለአላህ ሕግ ተገዥ ሆነዋል። ዛፍና ድንጋዩ፣ እንዲሁም እንስሳቱ ፈቃዱን ያለ ተቃውሞ ፈጽመዋል። እናም ሙስሊሞች ናቸው። አምላክን የካደ፣ ሕልውናውን ያልተቀበለ፣ ተአምራቱን ያስተባበለ ወይም ከርሱ ጋር ሌላን አምላክ የሚያመልከው ሰው እንኳ በተፈጥሯዊ ማንነቱ፣ በአካላዊ እሱነቱ ለዚህ ተፈጥሯዊ ሕግ ተገዥ በመሆኑ ሙስሊም ሊሰኝ ይችላል።

ይህን ከተረዳህ ወደ ሰው ልጅ ሁኔታ እንመለስ። ሁለት ሐይሎች ሲጎትቱት እናስተውላለን፡

አንደኛ፡ አላህ የሰውን ልጅ የፈጠረበት ተፈጥሯዊ ባህሪው። እርሱም ለአላህ እጅ መስጠት፣ ለፈቃዱ ማደር፣ እርሱን ማፍቀርና ማምለክ፣ ወደርሱ መቃረብ፣ እርሱንና እርሱ የሚወደውን ሁሉ ማለትም እውነትን እና በጎ ነገርን መውደድ፣ እርሱ የሚጠላውን እኩይ እና ሐሰት፣ በደል እና ወሰን አላፊነት ሁሉ መጥላት፣ እንደዚሁም



ተፈጥሯዊ የሆነው ገንዘብን፣ ቤተሰብን፣ ልጅን መውደድ፣ የምግብ፣ የመጠጥና የጾታዊ ፍላጎት፣ አካላት ተግባራቸውን ለማከናወን የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ከዚህ ውስጥ ይፈረጃል።

ሁለተኛ፡ የሰው ልጅ መርጦ መስራት የሚችልበት መስክ ሲሆን፣ አላህ መልእክተኛ ልኮለታል። መጽሐፍትን አውርዶለታል። እውነትን ከሐሰት፣ መቀናትን ከጥመት፣ ደግነትን ከክፋት መለየት ይችል ዘንድ። ምርጫው ከተሟላ መረጃና እውቀት ጋር ይሆን ዘንድም አእምሮ ለገሰው። እናም ከፈለገ የበጎነትን መንገድ ይመርጣል። እርሱም ወደ እውነትና ወደ መቀናት ያደርሰዋል። ከፈለገም የክፋትን መንገድ ይመርጥና ወደ ውድቀትና ጥፋት ይመራዋል።

የሰው ልጅ ከመጀመሪያው አንጻር የተፈጥሮ ሕግንና ስርዓትን የሚከተል፣ ከዚያ ቅንጣት የማያፈነግጥ ሆኖ ታገኘዋለህ። በዚህ ረገድ ከሌሎች ፍጡራን የተለየ አይደለም። ከሁለተኛው አኳያ የሻውን የመምረጥ መብትና ክሕሎት ያለው ሆኖ ይታያል። ከፈለገ ሙስሊም ካልፈለገም ካሃዲ መሆን ይችላል፡

﴿إِنَّا هَدَيْنَٰهُ ٱلسَّبِيلَ إِمَّا شَاكِرًا وَإِمَّا كَفُورًا ۝٣﴾ الإنسان: ٣

«መንገዱንም አመለከትነው፤ አመስጋኝ (አማኝ) ወይም ከሓዲ (ይሆናል)» (አል ኢንሳን 3)

ይህም በመሆኑ የሰው ልጆችን ሁለት አይነት ሆነው ታገኛቸዋለህ፡

አንደኛው አምላካን የሚያውቅ፣ በርሱ የሚያምን፣ እርሱን ብቻ የሚያመልክ፣ የዘረጋውን ሕግና ስርዓት በሕይዋቱ ውስጥ የሚከተልና የሚተገብር ሲሆን፣ ይህ ተፈጥሯዊውን ለአላህ የማደርና ከርሱፈቃድ ያለማፈንገጥ መስመር በመከተሉ ሙስሊም ይሰኛል። የተሟላ እስልምናንም ተከትሏል። እውቀቱም ትክክለኛ ነው። ምክንያቱም መልእክተኛ የላከለትን እና የማወቅና የመማር ክህሎት የለገሰውን ፈጣሪውን አውቋል። አእምሮውም ትክክለኛ፣ አስተሳሰቡም ቀጥተኛ ነው። ምክንያቱም አእምሮውን አሰርቶ፣ አስቦና አስተንትኖ ነገሮችን የመረዳትና የማገናዘብ ክሕሎት የለገሰውን አላህን ብቻ ለማምለክ ወስኗልና። አንደበቱም እውነተኛ ነው' እውነትንም መስክሯል።

ምክንያቱም ከአንድ አምላክ ውጭ ሌላ አምላክ እንዳለ አልመሰከረምና። ይህም አምላክ የመናገር ክሕሎት የሰጠው አላህ ነው። ሕይወቱ እውነትን ብቻ የመረጠች ሆናለች። ምክንያቱም መርጦ የመወሰን ነጻነት በተሰጠው መስኩም ለአላህ ሕግና ስርዓት ለማደር ወስኗል። በርሱና በሌሎች ፍጡራን መካከልም የመተዋወቅና የመግባባት ግንኙነት ፈጥሯል። ምክንያቱም ጥበበኛና አዋቂ ከሆነው አላህ ውጭ ሌላን አካል አያመልክም። ይህም አምላክ ፍጡራን ሁሉ የሚገዙትና ለፈቃዱ ያደሩለት፣ ለሰው ልጅም ፍጡራኑ ያገለግሉት ዘንድ የገራለት አምላክ ነው።

## የክህደት ምንነት

በአንጻሩ ሌላ የሰው አይነት እናገኛለን። ይህም ሰው ባያውቀውም ለተፈጥሯዊው የእስልምና እምነት ያደረ ሆኖ ተወልዷል። እንደዚሁ ሆኖም ሕይወቱን ሙሉ ይኖራል። ግና አምላኩን አያውቅም። በሕግጋቱ አያምንም። መልእክተኞችን አልተከተለም።

አላህ የለገሰውን አእምሮና የማገናዘብ ችሎታ ፈጣሪውን፣ አይንና ጆሮ የሰጠውን አካል ለማወቅ አልተጠቀመበትም። የአምላክን ሕልውና ካደ። እርሱን ከማምለክም ኮራ። መርጦ የመስራት ነጻነት በተሰጠው የሕይወቱ መስክ ለአላህ ሕግና ስርዓት ለማደር አልፈቀደም። ወይም ከርሱ ጋር ሌላንአካል አጋርቷል። አንድነቱን በሚያመላክቱ ተአምራት ማመንን አልወደደም። ከሐዲ (ካፊር) የሚሰኘው ይህ ሰው ነው። «ኩፍር» የሚለው ቃል ትርጉሙ «መሸፈን» ማለት ነው።

ይህ ሰው «ካፊር» የተሰኘበት ምክንያት ተፈጥሯዊ ባህሪው በመሐይምነት እና በቂልነት ሸፋን በመሸፈኑ ነው። የተወለደው የእስልምናን ተፈጥሯዊ ሐይማኖት ይዞ መሆኑን አውቀሃል። አካላዊ እሱነቱ የሚንቀሳቀሰውና የሚመራውም በእስልምና ብቻ ነው። በዙሪያው ያለው ዓለምም በዚሁ የእስልምና ፈለግ ብቻ ይመራል። እርሱ ግን በመሐይምነትና በቂልነት ግርዶ ተሸፍኗል። ዓይኑ የፍጡራኑን እና የራሱን ተፈጥሯዊ ባህሪ ከማየት ተጋርዷል። አእምሯዊ ክሕሎቱን ከተፈጥሮው ጋር በሚጋጭ ሁኔታ እንጅ



አይጠቀምበትም። አይታው ከተፈጥሮው የሚቃረን ነገር ነው። የሚሰራውም እርሱን በሚበክልና በሚያበላሽ አኳኋን ነው።

ካሐዲ (ካፊር) የተዘፈቀበት ጥመትና መንገድ መሳት ምን ያህል የከፋ እንደሆን ማስተዋል ትችላለህ።[46]

ይህ እንድትመራበት የሚፈለገው እስልምና ከባድና አስቸጋሪ ነገር አይደለም። አላህ ላገራለት ሰው ገር ነው። ኢስላም ማለት ይህ ዩኒቨርስ የሚመራበት ያማረ ሕግና ስርዓት ማለት ነውና፡

﴿ وَلَهُۥٓ أَسْلَمَ مَن فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ طَوْعًا وَكَرْهًا وَإِلَيْهِ يُرْجَعُونَ ﴿٨٣﴾ ال عمران: ٨٣ ﴾

*«በሰማያትም በምድርም ያሉ ሁሉ በውድም ሆነ በግድ ለርሱ የታዘዙና ወደርሱ የሚመለሱ ከሆነው አላህ ዲን ውጭ ሌላ ዲን ይሻሉን?» (አሊ ዒምራን 83)*

ኢስላም የአላህ ሐይማኖት ነው፡

﴿ إِنَّ ٱلدِّينَ عِندَ ٱللَّهِ ٱلْإِسْلَٰمُ ﴾ ال عمران: ١٩

*«በአላህ ዘንድ (ተቀባይነትና ተወዳጅነት ያለው) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው።» (አሊ ዒምራን 19)*

ኢስላም መላ ማንነትን ለአላህ ማስረከብ ነው፡

﴿ فَإِنْ حَآجُّوكَ فَقُلْ أَسْلَمْتُ وَجْهِىَ لِلَّهِ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِ ﴾ ال عمران: ٢٠

*«(ሙሐመድ ሆይ! በሃይማኖት ጉዳይ) ቢከራከሩህ፡- "ራሴን (ለአላህ አስረከብኩ፤ እርሱን ብቻ አመልከዋለሁ)፤ እኔን የተከተሉትም (ይህንኑ ይፈጽማሉ)።" በላቸው።» (አሊ ዒምራን 20)*

የአላህ መልእክተኛ የእስልምናን ትርጉም እንዲህ ሲሉ አብራርተዋል፡

[46] መባዲኡል ኢስላም ገጽ 3-4

መነጽር ከመረመረ በኋላ ዘመናዊ ሳይንስ ስለ ስማያትና ምድር፣ እንዲሁም ስለ ሰው ልጅ የደረሰባቸው ግኝቶች ከቁርአን ገለጻዎች ጋር ሙሉ በሙሉ እንደሚስማሙ የመሰከረ ሲሆን፣ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ግን የስማያትንና የምድርን እንደዚሁም የሰው ልጆችን እና የእንስሳትን አፈጣጠር አስመልክቶ በርካታ ስህተቶች መኖራቸውን መስክሯል።[50]

## ለ) ሱንናህ

አላህ ለነቢዩ ሙሐመድ የተቀደሰውን ቁርአን አወረደላቸው። በተመሳሳይ መልኩም በሐዲስ (በሱንና)በርካታ እውነታዎችን ገለጸላቸው። ሱንና የቁርአን ማብራሪያ ነው። የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-

«እኔ ቁርአንን እና እርሱን የሚመስልን ነገር ተሰጥቻለሁ።» (አህመድ)

ቁርአን ውስጥ ያሉትን ጥቅልና አሻሚ ሐሳቦች እንዲያብራሩም አላህ ፈቃድ ሰጥቷቸዋል፡-

﴿وَأَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ٱلذِّكْرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيْهِمْ وَلَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٤٤﴾﴾

النحل: ٤٤

*«ለሰው ልጆች የወረደላቸውን (መልዕክት) ታብራራላቸውና እነርሱም ያስተነትኑ ዘንድ ቁርአንን ወደ አንተ አወረድን።» (አል ነሀል 44)*

ሱንና የእስልምና ሁለተኛ ምንጭ ነው። እርሱም ከነቢዩ ሙሐመድ በትክክለኛ የመልእክት ሰንሰለት (ሰነድ) አማካይነት የተገኘ ንግግራቸው፣ ተግባራቸው፣ ሌሎች ሲሰሩት አይተው ያጸደቁትንና ባህሪያቸውን የሚያጠቃልል ነው።

ሱንና ከአላህ ለነብዩ የተላከ መልእክት ነው። ምክንያቱም ነቢዩ ሙሐመድ ከልብ ወለድ አይናገሩም። ንግግራቸው ሁሉ መለኮታዊ ራእይ ነው፡-

[50] ምርምሩን ያካሄደው ክርስትያን በነበረ ጊዜ ሲሆን፣ ከዚህ ጥልቅ ፍተሻ በኋላ ግን እስልምናን ተቀብሏል።



﴿إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَىٰ ﴿٤﴾ عَلَّمَهُۥ شَدِيدُ ٱلْقُوَىٰ ﴿٥﴾﴾ النجم: ٤ - ٥

*«እርሱ (ቁርአን)፣ (ከአላህ) የተወረደለት መልዕክት እንጅ ሌላ አይደለም። ኃይለ ብርቱ የሆነው (መልአክ) (ቁርአንን) አስተማረው፣» (አል ነጅም 4-5)*

አላህ እንዲያደርሱ ያዘዛቸውን መልእክት ብቻ ለሰዎች ያደርሳሉ፡-

﴿إِنْ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّ وَمَآ أَنَا۠ إِلَّا نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٩﴾﴾ الأحقاف: ٩

*«የምከተለው የሚገለጽልኝን ራዕይ ብቻ ነው። እኔ ግልጽ አስፈራሪ እንጅ ሌላ አይደለሁም።» (አል አህቃፍ 9)*

ተአማኒ ሱንና የእስልምና እምነት፣ አምልኮ፣ዓለማዊ ሕይወትና ስነ ምግባሮች የተግባር ማብራሪያ ነው።

ነቢዩ ሙሐመድ የአላህን ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ ተግብረዋል። ለሰዎችም አብራርተዋል። ተከታዮቻቸውም የርሳቸውን አርአያነት እንዲከተሉ አዘዋል። በአንድ ሐዲሳቸው እንዲህ ብለዋል፡-

«እኔ ስሰግድ እንዳያችሁት አድርጋችሁ ስገዱ።» (ቡኻሪ)

አማኞች የርሳቸውን ቃል እና ተግባር ሳያዛንፉ እንዲከተሉም አላህ አዟል። ይህ ሲሆን እምነታቸው ይበልጥ እንደሚሟላም ገልጿል።

﴿لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِى رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُوا۟ ٱللَّهَ وَٱلْيَوْمَ ٱلْءَاخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرًا ﴿٢١﴾﴾ الأحزاب: ٢١

*«የአላህ መልዕክተኛ፣ (ከመካከላችሁ) አላህንና መጭውን ዓለም ተስፋ ለሚያደርግ፣ አላህንም በብዛት ለሚያወሳ መልካም አርአያ ነው።» (አል አህዛብ 21)*

የነቢዩ ባልደረቦች የርሳቸውን ቃልና ተግባር ለቀጣዩ ትውልድ አስተላለፉ። ያ ትውልድም ቀጥሎ ለመጣው ትውልድ አስተላለፈ። ከዚያ በኋላ በሱንና መጽሐፍት አማካይነት በተደራጀ መልክ ተጻፈ። የሐዲስ ዘጋቢዎች አንድን ሐዲስ ከትክክለኛነት ለመመዝገብ መስፈርታቸው የከበደ ነበር። ሐዲሱን የሚያስተላልፈው ሰው ሐዲሱን ሰማሁት ካለው መምህር ጋር በሕይወት የተገናኙ መሆን አለባቸው። በዚህ መልኩ በሐዲሱ ዘጋቢና በነቢዩ ሙሐመድ መካከል

ሳይቋረጥ የተቀጣጠለ የመልእክት ሰንሰለት ይኖራል።[51] በየእርከኑ የሚገኙ ሐዲስ አስተላላፊዎችም ታማኞች፣ መልካም ስብእና ያላቸውና የማስተላለፍ ብቃታቸው የተመሰከረለት መሆን ይኖርበታል።

ሱንና የእስልምና ተግባራዊ ትርጓሜ ከመሆኑም በተጨማሪ ቁርአንን ለማብራራት ይረዳል። በጥቅሉ የተቀመጡ ሕግጋቱን ይተነትናል። የአላህ መልእክተኛ የሚወርድላቸውን የቁርአን መልእክት ያብራሩና ይተነትኑ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በቃል፣ አንዳንድ ጊዜ በተግባር፣ ሌላ ጊዜ በሁለቱም። በአንዳንድ ሕጋዊ ድንጋጌዎችና ማብራሪያዎች ሱንና ራሱን ችሎ የሚገለጽበት ሁኔታም አለ።

ቁርአንና ሱንና የእስልምና ሐይማኖት መሠረታዊ ምንጮች መሆናቸውን ማመን ግዴታ ነው። እነርሱን መከተል፣ አለመግባባቶችን በነርሱ መፍታት፣ ትእዛዛቸውን መተግበር፣ ከከለከሉት መታቀብ፣ መልእክታቸውን አምኖ መቀበል፣ ከውስጣቸው በተካተቱ የአላህ ስሞች፣ በባህሪያቱና በተግባራቱ፣ አላህ ለአማኝ ባሮቹ ባዘጋጀላቸው ነገርና ለጠላቶቹ በዛተው ቅጣት ማመን ግዴታ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ ثُمَّ لَا يَجِدُوا فِي أَنفُسِهِمْ حَرَجًا مِّمَّا قَضَيْتَ وَيُسَلِّمُوا تَسْلِيمًا ﴿٦٥﴾﴾ النساء: ٦٥

*«በጌታህ እምላለሁ፣ በመካከላቸው ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች ሁሉ አንተን ዳኛ እስካላደረጉህ፣ ከዚያም በፀጋና በደስታ (ያለተቃውሞ) እስካልተቀበሉና (ለብይንህ) እጅ እስካልሰጡ ድረስ አማኞች አይሆኑም።»*
*(አል ኒሳእ 65)*

﴿وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا﴾ الحشر: ٧

*«መልዕክተኛው የሰጣችሁን ያዙ። የከለከላችሁንም ተው።» (አል ሐሽር 7)*

[51] የሐዲስ ምሁራን ለሐዲስ ዘገባ ሲሉ ሁለት አዳዲስ ሳይንሶችን ፈጠሩ። «ጀርሀ ወተእዲል» እና «ሙስጠለሐል ሐዲስ» የሚባሉ። እነዚህ እጅግ ድንቅ የእውቀት መስኮች የትኛውም ሕዝብ ዘንድ የማይገኙ የሙስሊሙ ኡምማ ብቻ ሐብት ናቸው።



# የእምነትና የተግባር ደረጃዎች

ባለፈው ትምህርት የአላህን ሐይማኖት መሠረታዊ ምንጮች ተመልክተናል። ቀጥሎ በእስልምና ሐይማኖት ውስጥ የሚገኙ የእምነትና የተግባር ደረጃዎቹን እንመለከታለን። እነርሱም ኢስላም፣ ኢማንና ኢህሳን ይባላሉ። ባጭሩ እንቃኛቸዋለን።

## የመጀመሪያው ደረጃ

የመጀመሪያው ደረጃ ኢስላም ሲሆን መሠረቶቹም አምስት ናቸው። እነርሱም ሸሃዳዎች፣ ሶላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ፣ ዘካ መስጠት፣ ረመዷን መጾምና ሐጅ ማድረግ ናቸው።

1) **ሸሃዳዎች** የሚባሉት የአላህን አንድነትና የነቢዩ ሙሐመድን መልእክተኛነት መመስከር ናቸው።

ከአላህ ሌላ አምላክ የለም ብሎ መመስከር ማለት ከርሱ ውጭ በሰማያትም ሆነ በምድር በእውነት የሚያመልኩት አምላክ እንደሌለና ከርሱ ሌላ ያሉ አማልክት ሁሉ የሐሰት አማልክት መሆናቸውን መመስከር ነው። ይህ ምስክርነት አላህን ብቻ በፍጹም ቅንነትና ታማኝነት ማምለክንና ከርሱ ሌላ ያሉ አካላትን ሁሉ ፈጽሞ አለማምለክን ያካትታል። ሁለት ነገሮች እስካልተረጋገጡ ድረስም ጠቀሜታ አይኖረውም፡-

አንደኛ፡- የአላህን አሐዳዊነት ከልብ አምኖ፣ አውቆ፣ እውነት ብሎና ወዶ መቀበል።
ሁለተኛ፡- ከአላህ ሌላ በሚመለኩ ነገሮች ሁሉ መካድ። የአላህን አንድነት በቃሉ መስክሮ ከአላህ ውጭ የሚመለኩ አካላትን ያልካደና ያላስተባበለ ምስክርነቱ አይፈይደውም።[52]

የነቢዩ ሙሐመድን መልእክተኛነት መመስከር ማለት የታዘዙትን መፈጸም፣ ያስተላለፉትን መልእክት እውነት ብሎ መቀበል፣ ከከለከሉት መታቀብ፣ አላህን እርሳቸው ባስተማሩት መንገድ ብቻ ማምለክ፣ እርሳቸው ለሰው ልጆች ባጠቃላይ መላካቸውን ማወቅና

[52] ቁረቱ ዓይኑል ሙወሂዲን ገጽ 60.

ማመን፣ የአላህ አገልጋይ እንደሆኑ፣ እንደማይመለኩ፣ የሚስተባበሉና ሊታዘዟቸው የሚገቡ መልእክተኛ መሆናቸውን፣ የታዘዛቸው ጀነት፣ ያመጸባቸው እሳት እንደተዘጋጀለት ማወቅና ማመን ነው። እንዲሁም በእምነትና አመለካከት፣ በአምልኮ ስርዓት፣ በሕግና አስተዳደር፣ በስነ ምግባር፣ በቤተሰባዊ ጉዳዮች፣ በሐላልና በሐራም አጀንዳዎች ወዘተ የአላህን ሕግ ከርሳቸው እንደምንቀበል ማወቅና ማመን ግድ ነው። ምክንያቱም የአላህን መልእክት ለሰው ልጆች አድራሽ ናቸውና።[53]

**2) ሶላት**፣ የእስልምና ሁለተኛው መሠረት ነው። የእስልምና ምሰሶ እንደሆነም ተገልጿል። በሰውየውና በአምላኩ መካከል ያለ የግንኙነት ምመስመር ነውና።በቀን አምስት ጊዜ ተደጋግሞ ይፈጸማል። እምነት በርሱ ይታደሳል። ነፍስ ከሐጢአት ቆሻሻዎች ትጸዳለች። ሶላት በወንጀልና በሰውየው መካከል ግርዶ ይሆናል።

ሙስሊም ገና ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነሳ በዓለማዊ ጉዳዮች ከመጠመዱ በፊት በተሟላ ንጽህና ከአምላኩ ፊት ይቆማል። «አሏሁ አክበር» (አላህ ከሁሉም ይልቃል) በማለትም የአምላኩን ታላቅነት ይናዘዛል። እርሱን በብቸኝነት ይታዘዛል። እገዛውን ይጠይቃል። ቀጥተኛውን ጎዳና እንዲመራው ይማጸናል። አምላኩን ለማምለክና ለመታዘዝ የገባውን ቃል በሱጁድ፣ በሩኩእና በመቆም ያድሳል። ይህንኑ በቀን አምስት ጊዜ ደጋግሞ ይፈጽማል።

ሶላት ለመስገድ የአካል፣ የልቦና፣ የልብስና የመስገጃ ቦታ ንጽህና የግድ ነው። ከሌሎች ሙስሊም ወንድሞቹ ጋርም በጋራ ሊፈጽም ግድ ነው። ሲሰግድ ፊቱን ወደ አላህ ቤት ወደ ቂብላ ያዞራል።

ሶላት አላህን ፍጹም ባማረና በተሟላ መልኩ ለማምለክ የተደራጀ የአምልኮ ስርዓት ነው። መላ ሰውነቱን ያሳትፋል። አካልን፣ አንደበትን፣ የእግር የእጅ፣ የራስና የስሜት ሕዋሳት፣ እንዲሁም የሌሎች የአካል ክፍሎችን እንቅስቃሴና ተሳትፎ ያካትታል። በሶላት ውስጥ ሁሉም የሰውነታችን ክፍሎች ከአምልኮ ስርዓቱ የየድርሻቸውን ያኛሉ።

[53] ዲኑል ሐቅ ገጽ 51-52



የስሜት ሕዋሳትና አካላት ከሶላት የአምልኮ ድርሻ አላቸው። ቀልብም ድርሻ አለው። ሶላት አላህን ማወደስን፣ ማመስገንን፣ ማላቅን፣ ክብሩንና ልእልናውን መግለጽን፣ የእውነትን ምስክርነት (ሸሃዳ)፣ የቁርአን ንባብን፣ ከአምላክ ፊት በውርደትና በመተናነስ መቆምን፣ በፍርሃትና በተመስጦ ተውጦ ለልእልናው በመዋረድና ለክብሩ በመተናነስ ሩኩእ እና ሱጁድ ማድረግን፣ እንዲሁም መቀመጥን ሁሉ ያካተተ አምልኮ ነው።

ሰጋጁ በሶላት ውስጥ ቀልቡን ለአላህ ይሰጣል። አካሉ ይተናነሳል። በፍርሃት ስሜትም ይቆማል። አላህን በማወደስና በነቢዩ ሙሐመድ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይሰፍን ዘንድ በመመኘት፣ እንዲሁም የዚህችንም ሆነ የመጭውን ዓለም በጎ ነገሮች ከአምላኩ በመማጸን ሶላቱን ያጠናቅቃል።[54]

**3) ዘካ፦** ከእስልምና መሠረቶች መካከል ሦስተኛው ነው። ባለ ሐብት ሙስሊም ከገንዘቡ ዘካ መስጠት ግድ ይሆንበታል። መጠኑ አነስተኛ ነው። ለድሆችና ዘካ እንዲቀበሉ ለተፈቀደላቸው ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ይሰጠዋል።

ሙስሊም ዘካውን ለተገቢዎቹ ሰዎች በደስታ መስጠት፣ በተቀባዮች ላይ አለመመጻደቅና በዘካው ሰበብ እነርሱን አለማወክ ግድ ይሆንበታል። ሲሰጥም የአላህን ውዴታ በመሻት እንጅ ከፍጡራን ውለታ ወይም ምስጋና ከጅሎ ወይም ደግሞ ክብርና ዝናው እንዲገን አልሞ መሆን የለበትም።

ዘካ ለገንዘብ በረከት ነው። ድሆችንም ያስደስታል። ከልመናም ያድናቸዋል። ከረሃብና ከእርዛትም ይታደጋቸዋል።

ዘካ መስጠት ቸርነትን፣ ከራስ ሌሎችን ማስቀደምን፣ ለሌሎች መትጋትንና የእዝነትን ድንቅ ባህሪያት መላበስ ነው። ከንፉግነት እኩይ ባህሪ መጽዳት ነው። በዘካ ሙስሊሞች እርስ በርሳቸው ይረዳዳሉ። ሐብታሙ ለድሃው ያዝናል። ዘካ በትክክል ቢሰበሰብና ቢሰራጭ በሕብረተሰቡ ውስጥ ችግረኛ ድሃ፣ እዳ ያጎበጠው ባለእዳ ወይም ስንቅ አልባ ተጓዥ አይገኝም ነበር።

[54] ሚፍታሁ ዳረ ስአዳህ 2/384

**4) ጾም፡-** በረመዷን ወር መጾም አራተኛው የእምነት መሠረት ነው። ጾም ማለት አላህን በማምለክ አላማ ጠዋት ጎህ ከመቅደዱ በፊት ጀምሮ ጸሐይ እስከትጠልቅ ድረስ ከምግብ፣ ከመጠጥና ከጾታዊ ግንኙነት ታቅቦ መዋል፣ ራስን ከስጋዊ ፍላጎቶች ማቀብ ነው። አላህ ለበሽተኛ፣ ለተጓዥ፣ ለእርጉዝ፣ ለመጫት፣ የወር አበባ በማየት ላይ ላለችና ለአራስ ሴት አፈጻጸሙን አቅልሎላቸዋል። እያንዳንዳቸውን የሚመለከቱ፡ የማቃለያ ድንጋጌዎችን ደንግጓል።

በዚህ የጾም ወር ውስጥ ሙስሊም ራሱን ከስጋዊ ፍላጎቶች አቅቦ ይቆያል። እናም ነፍስ ከእንስሳዊነት ወጥታ ወደ መላእክነት ትመጥቃለች። ጾመኛ በዚህች ዓለም ውስጥ አላህን ከማስደሰት ውጭ ሌላ ዓላማና ጉዳይ የሌለው ሰው ዓይነት ገጽታ ይላበሳል።

ጾም ቀልብን ሕያው ያደርጋል። ለዚህች ዓለም ጸጋዎች ለከት የለሽ ጉጉትን ያከስማል። ከአላህ ዘንድ ያለውን ጸጋ የመጓጓትን ስሜት ይፈጥራል። ሐብታሞች የድሆችን ችግር እንዲያስታውሱ ያደርጋል። እናም ቀልቦቻቸው ያዝናሉ። አላህ የሰጣቸው ጸጋ ይታወሳቸውና ምስጋና ያክላሉ።

ጾም ነፍስን ያጸዳል። አላህን በመፍራት ስሜት ይገራለታል። ግለሰብም ሆነ ማሕበረሰብ፣ በሚስጥርም በይፋም፣ በድሎትም በሐዘንም የአላህ ቁጥጥር እና ጥበቃ እንዳለበት እንዲሰማው ያደርጋል። ሕብረተሰቡ ይህን የአምልኮ ስርዓት ለአንድ ወር ያህል አላህ ያየኛል፣ ይቆጣጠረኛል በሚል ስሜት ተሞልቶ ያለ ማዛነፍ ሲፈጽም ይስተዋላል። ይህን እንዲያደርግ ያስገደደው አላህን መፍራቱ፣ በአላህና በመጭው ዓለም ማመኑ፣ አላህ ሚስጥራትን ሁሉ አዋቂ መሆኑን በእርግጠኝነት መረዳቱ፣ የሰው ልጅ ከአምላክ ፊት ቆሞ በዚህች ዓለም ስላሳለፈው ሕይወት የሚጠየቅበት ቀን እንደሚመጣ ከልብ መቀበሉ ነው።[55]

**5) ሐጅ፡-** በተቀደሰችው የመካ ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው የአላህ ቤት ሐጅ ማድረግ አምስተኛው የእስልምና መሠረት ነው። ለአካለ መጠን የደረሰና አቅም ያለው ማንኛውም ሙስሊም ወደ ተቀደሰው

[55] ሚፍታሁ ዳረ ሰአዳህ 2/384



መስጊድ መሄድ የሚችልበት መጓጓዣ እና መሄጃና መምጫ የሚሆነው ገንዘብ፣ ቀለብ፣ ለቤተሰቦቹም ደርሶ እስኪመለስ ድረስ ቀለብ ካለው፣ መንገዱም ሰላም ከሆነና ቤተሰቦቹንም ጥሎ መሄዱ በነርሱ ላይ አደጋ የማያስከትል ከሆነ ሐጅ ማድረግ ግዴታ ይሆንበታል።

ሐጅ በእድሜ ልክ አንድ ጊዜ አቅሙ ላለው ሙስሊም ላይ ግዴታ ይሆናል። ሐጅ ማድረግ የፈለገ ሰው ወደ አላህ ንስሐ መግባት አለበት። ይህ ሲሆን ነፍስ ከወንጀል ቆሻሻ ትጸዳለች። ከተቀደሰችው የመካ ከተማ ሲደርስ አላህን በማምለክና በመታዘዝ፣ እንዲሁም በማላቅ ስሜት ተውጠ የሐጅን ስርዓት ያከናውናል። ካእባ እና ሌሎችም መካ ውስጥ ያሉ ስፍራዎች እንደማይመለኩ ያውቃል። መጥቀምም ሆነ መጉዳት እንደማይችሉም ያውቃል። አላህ ወደዚህች የተቀደሰች ቦታ ሐጅ እንዲደረግ ባያዝ ኖሮ የሐጅ ስርዓት መፈጸም ባልተፈቀደ ነበር።

በሐጅ ወቅት ሙስሊም ነጭ ሽርጥና ኩታ ይለብሳል። ከተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የመጡ ሙስሊሞች በአንድ ቦታ ላይ ይሰበሰባሉ። በገዥና ተገዥ፣ በሐብታምና በድሃ፣ በነጭና በጥቁር መካከል ልዩነት የለም። ሁሉም የአላህ ፍጡራንና ባሪያዎች ናቸው። አንዱ ከሌላው የሚበልጠው አላህን በመፍራትና በበጎ ስራ ብቻ ነው።

ሙስሊሞች በሐጅ አማካይነት ይተዋወቃሉ። ይተጋገዛሉ። ከሞት ተቀስቅሰው ለምርመራ በአንድ መስክ የሚቆሙበትን ጊዜም ያስታውሳሉ። እናም ከሞት በኋላ ላለው ሕይወታቸው ስኬት በዚህች ዓለም አላህን ለመታዘዝ የበለጠ ዝግጁዎች ይሆናሉ።[56]

## አምልኮ በኢስላም

አምልኮ ማለት ለአላህ ተገዥነት ማለት ነው። ምክንያቱም አላህ ፈጣሪ ሲሆን አንተ ፍጡር ነህ። አንተ ባሪያ አላህ ደግሞ ጌታህ ናችሁ። ይህ ይሆን ዘንድ በዚህች ዓለም ውስጥ የአላህን ሕግና ስርዓት፣ እንዲሁም የመልእክተኞችን ፈለግ ተከትለህ በቀጥተኛው ጎዳና ላይ የመጓዝ ግዴታ አለብህ። አላህ ለባሮቹ ታላላቅ ሕግጋትን

[56] ያለፈው ምንጭ 2/385፣ ዲኑል ሐቅ ገጽ 67

﴿ لِكُلٍّ جَعَلْنَا مِنكُمْ شِرْعَةً وَمِنْهَاجًا ﴾ المائدة: ٤٨

*«ከመካከላችሁ ለሁሉም ሕግጋትን (ቀርፀናል)፤ (ግልጽ የሆነን) ጐዳናም ዘርግተናል።» (አል ማኢዳህ 48)*

የነዚህ ሕግጋት መቋጫ የነቢዩ ሙሐመድ ሕግ (ሸሪዓ) ነው። የጥንቶችንም ይሽራል። መልእክታቸው የመልእክቶች ሁሉ መቋጫ፣ እርሳቸውም የነብያት መደምደሚያ ናቸውና።

በሁሉም ነብያት ማመን ግዴታ ነው። አንዳቸውን ያልተቀበለ ሁሉንም እንዳስተባበለ ይቆጠራል። ምክንያቱም ሁሉም ነብያት የሰበኩት በአላህ፣ በመላእክት፣ በመጻሕፍት፣ በመልእክተኞችና በመጭው ዓለም ማመንን ነውና። እምነታቸውም አንድ ነው። በነርሱ መካከል ልዩነት በማድረግ በከፊሉ አምኖ በከፊሉ የካደ በሁሉም እንደ ካደ ይቆጠራል። ሁሉም በሁሉም ነብያት ማመንን አስተምረዋልና። አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿ ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلْمُؤْمِنُونَ ۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّن ﴾ البقرة: ٢٨٥

*«መልዕክተኛው (ሙሐመድ) ከአላህ ወደርሱ በተወረደለት መልዕክት አመነ። አማኞችም (እንዲሁ አመኑ)። "ሁሉም በአላህ፣ በመላእክት፣ በመጻሕፍትና በመልዕክተኞች፥ በመካከላቸው ምንም ልዩነት አናደርግም (ከፊሉቹን አምነን በከፊሉቹ አናስተባብልም)" ያሉ ሲሆን፥ አመኑ።» (አል በቀራህ 285)*

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَكْفُرُونَ بِٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦ وَيُرِيدُونَ أَن يُفَرِّقُوا۟ بَيْنَ ٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦ وَيَقُولُونَ نُؤْمِنُ بِبَعْضٍ وَنَكْفُرُ بِبَعْضٍ وَيُرِيدُونَ أَن يَتَّخِذُوا۟ بَيْنَ ذَٰلِكَ سَبِيلًا ﴿١٥٠﴾ ﴾ النساء: ١٥٠

*«እነዚያ በአላህና በመልዕክተኞቹ የሚክዱ፥ በአላህና በመልዕክተኞቹ መካከልም ልዩነትን ሊያደርጉ የሚሹ፥ "በከፊሉች (መልዕክተኞች) እናምናለን፥ ከፊሉቹን ግን እናስተባብላለን።" የሚሉ፥ በዚህ (በእምነትና በክህደት) መካከልም (አዲስ) መንገድን ሊያበጁ የሚሹ፥» (አል ኒሳእ 150)*



**5) በመጭው አለም ማመን፦** በዚህች ምድር ውስጥ ያሉ ፍጡራን ሁሉ ፍጻሜ ሞት ነው። የሰው ልጅ ከሞት በኋላ መሄጃው የት ይሆን? በዚህች ዓለም ውስጥ ከቅጣት ያመለጡ በዳዮች እንዳመለጡ ይቀሩ ይሆን? በዚህች ዓለም ውስጥ ለበጎ ስራቸው ምንም ዓይነት ምላሽ ያላገኙት በዚሁ ሁኔታ እንደሞቱ ይቀሩ ይሆን? የሰው ልጅ ወደ ሞት ይጎርፋል። ትውልድ አልፎ ትውልድ ይተካል። አላህ የዚህችን ዓለም ፍጻሜ እስከያውጅ ድረስ ይህው ሁኔታ ይቀጥላል። ከዚያም በመጭው ዓለም ከመጀመሪያ ሰው እስከ መጨረሻው ሰው ያሉትን ሁሉ በአንድ መስክ ይሰበሰባሉ። ምርመራም ይደረግላቸዋል። ሙእሚኖች ወደ ጀነት ይሄዳሉ። ካሀድያን ወደ እሳት ይነዳሉ።

ጀነት አላህ ለአማኝ ወዳጆቹ ያዘጋጃት የድሎት አገር ናት። ጸጋዎች በየአይነቱ ሞልተውባታል። እነዚህን ጸጋዎች በቃላት መግለጽ አይቻልም።

ጀነት መቶ ደረጃዎች አሏት። እያንዳንዱ ደረጃ በእምነታቸው እና አላህን በታዘዙት ልክ የሚስተናገዱ ነዋሪዎች አሉት። ጀነት ውስጥ አነስተኛውን ጸጋ የሚያገኘው ሰው ግዛቱ የዚህች ዓለም ንጉስ ካለው ግዛት አስር እጥፍ ይጨምራል።

እሳት አላህ በርሱ ለካዱ ሰዎች ያዘጋጃት የቅጣት አገር ናት። ሊሰሟቸው የሚከብዱ ልዩ ልዩ የቅጣት ዓይነቶች አሉባት። አላህ በመጭው ዓለም ሞት እንዲኖር ቢፈቅድ ኖሮ የእሳት ሰዎች ገና እሳቱን ሲያዩ በሞቱ ነበር።

አላህ የሰውን ልጅ እንቅስቃሴ ያውቃል። በቅርበትም ይቆጣጠራቸዋል። በተጨማሪም ለእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት መላእክት መድቦላቸዋል። አንደኛው በጎ ስራውን፣ ሌላኛው ክፉ ስራውን ይከትባሉ። አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿ مَّا يَلْفِظُ مِن قَوْلٍ إِلَّا لَدَيْهِ رَقِيبٌ عَتِيدٌ ﴿١٨﴾ ﴾ ق: ١٨

*«ከቃል አንድንም አይናገርም፥ ከርሱ ዘንድ (ቃሉን ለመመዝገብ) ዝግጁ የሆኑ መላእክት ያሉ ቢሆን እንጅ።» (ቃፍ 18)*

ተግባሮቹ በመጽሐፍ መልክ ይዘጋጃሉ። በእለተ ቂያማም ለሰውየው ይሰጣሉ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَوُضِعَ ٱلْكِتَٰبُ فَتَرَى ٱلْمُجْرِمِينَ مُشْفِقِينَ مِمَّا فِيهِ وَيَقُولُونَ يَٰوَيْلَتَنَا مَالِ هَٰذَا ٱلْكِتَٰبِ لَا يُغَادِرُ صَغِيرَةً وَلَا كَبِيرَةً إِلَّآ أَحْصَىٰهَا ۚ وَوَجَدُوا۟ مَا عَمِلُوا۟ حَاضِرًا ۗ وَلَا يَظْلِمُ رَبُّكَ أَحَدًا ﴿٤٩﴾ ﴾ الكهف: ٤٩

«(የሥራ) መዝገብ ይቀርባል። ኃጢአተኞችንም በውስጡ የያዘውን (መረጃ) እጅግ ሲፈሩት ታያለህ። "ወይ ጥፋታችን ምን ዓይነት (መዝገብ) ነው! ትንሽ ትልቅ ሳይል (ሁሉንም ሥራዎች ልቅም አድርጎ) በውስጡ ያሰፈረ!" ይላሉ። የሠሩትን ሥራ ከፊታቸው ቀርቦ ያገኙታል። ጌታህ ማንንም አይበድልም።» (አል ከህፍ 49)

ሰውየው የስራ መዝገቡን ያነሳል። ተግባራቱን አይክድም። የሚክዳቸው ካሉም አላህ አይኑን፣ ጆሮውን፣ እጆቹን፣ እግሮቹንና ቆዳውን ያናግራቸውና የሰራውን ሁሉ ይመሰክራሉ። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَيَوْمَ يُحْشَرُ أَعْدَآءُ ٱللَّهِ إِلَى ٱلنَّارِ فَهُمْ يُوزَعُونَ ﴿١٩﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا مَا جَآءُوهَا شَهِدَ عَلَيْهِمْ سَمْعُهُمْ وَأَبْصَٰرُهُمْ وَجُلُودُهُم بِمَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿٢٠﴾ وَقَالُوا۟ لِجُلُودِهِمْ لِمَ شَهِدتُّمْ عَلَيْنَا ۖ قَالُوٓا۟ أَنطَقَنَا ٱللَّهُ ٱلَّذِىٓ أَنطَقَ كُلَّ شَىْءٍ وَهُوَ خَلَقَكُمْ أَوَّلَ مَرَّةٍ وَإِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴿٢١﴾ وَمَا كُنتُمْ تَسْتَتِرُونَ أَن يَشْهَدَ عَلَيْكُمْ سَمْعُكُمْ وَلَآ أَبْصَٰرُكُمْ وَلَا جُلُودُكُمْ وَلَٰكِن ظَنَنتُمْ أَنَّ ٱللَّهَ لَا يَعْلَمُ كَثِيرًا مِّمَّا تَعْمَلُونَ ﴿٢٢﴾ ﴾ فصلت: ١٩ - ٢٢

«የአላህ ጠላቶች ወደ እሳት የሚሰበሰቡበትን ቀን (አስታውስ)። እነርሱ (ያንጊዜ) በአንድ ላይ ተከማችተው (ወደ እሳት) ይነዳሉ። ወደርሷ በቀረቡ ጊዜም ጆሮዎቻቸው፣ ዓይኖቻቸውና ቆዳዎቻቸው ይሠሩት በነበረው ነገር በነርሱ ላይ ይመሰክሩባቸዋል። ቆዳዎቻቸውንም፦ "በኛ ላይ የመሰከራችሁት ለምንድን ነው?" በማለት ይጠይቃሉ። "ያ ሁሉንም ነገር ያናገረ አላህ አናገረን። እርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጠራችሁ። ወደርሱም ትመለሳላችሁ።" ይሏቸዋል። "(እኩይ በምትፈጽሙበት ወቅት) ከጆሮዎቻችሁ፣ ዓይኖቻችሁና ቆዳዎቻችሁ ምስክርነት አትደበቁም ነበር። ግና አላህ ከምትፈጽሙት (እኩይ ተግባር) ብዙውን አያውቅም የሚል ግምት ነበራችሁ።"(ፉሲለት 19-22)



በመጭው ዓለም ማመንን ሁሉም ነብያትና መልእክተኞች ሰብከዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنَّكَ تَرَى ٱلْأَرْضَ خَٰشِعَةً فَإِذَآ أَنزَلْنَا عَلَيْهَا ٱلْمَآءَ ٱهْتَزَّتْ وَرَبَتْ ۚ إِنَّ ٱلَّذِىٓ أَحْيَاهَا لَمُحْىِ ٱلْمَوْتَىٰٓ ۚ إِنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٣٩﴾ ﴾ فصلت: ٣٩

«ምድርን ደረቅ ሆና ማየትህም ከተአምራቱ ነው። በርሷ ላይ ውሃ ባወረድን ጊዜ (በቡቃያዎችዋ) ነፍስ ትዘራለች። ትለመልማለችም። ያ እርሷን ሕያው ያደረጋት አምላክ በእርግጥም ሙታንን ሕያው ያደርጋል። እርሱ ሁሉንም ነገር መፈፀም ይችላል።» (ፉሲለት 39)

﴿ أَوَلَمْ يَرَوْا۟ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَلَمْ يَعْىَ بِخَلْقِهِنَّ بِقَٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يُحْـِۧىَ ٱلْمَوْتَىٰ ۚ بَلَىٰٓ إِنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٣٣﴾ ﴾ الأحقاف: ٣٣

«ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው፣ እነርሱን በመፍጠሩም ድካም ያልተሰማው አላህ ሙታንን ሕያው ማድረግ እንደሚችል ለላዩምን? በእርግጥም ይህን ማድረግ የሚሳነው አይደለም። እርሱ ሁሉንም ነገር ቻይ ነውና።» (አል አሕቃፍ 33)

የአላህ ጥበብ የሚወስነውም ይህንኑ ነው። ምክንያቱም አላህ ፍጡራንን ለቀልድ አልፈጠረም። እንዲሁም አይተዋቸዋውም። አላህ ይቅርና የሰው ልጅ እንኳ አንድን ዋጋ ያለው ነገር ያለ ምንም አላማና ሳያስበው በድንገት አይፈጥርም። ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው ይህን እያደደርግም ብሎ የሚያምን፣አምላክ ለጫዋታ እንደፈጠረውና እንዲሁም እንደሚተወው እንዴት ሊያስብ ይችላል? ይህ ፍጹም ለአላህ ተገቢ አይደለም። እርሱ ከዚህ በጣም የጸዳና የላቀ ነው። እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَفَحَسِبْتُمْ أَنَّمَا خَلَقْنَٰكُمْ عَبَثًا وَأَنَّكُمْ إِلَيْنَا لَا تُرْجَعُونَ ﴿١١٥﴾ ﴾ المؤمنون: ١١٥

"የፈጠርናችሁ ለቀልድ እንደሆነና እናንተም ወደኛ እንደማትመለሱ ገመታችሁን?" (አል ሙእሚኑን 115)

﴿ وَمَا خَلَقْنَا ٱلسَّمَآءَ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا بَٰطِلًا ۚ ذَٰلِكَ ظَنُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ۚ فَوَيْلٌ لِّلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِنَ ٱلنَّارِ ﴿٢٧﴾ ﴾ ص: ٢٧

*«ሰማይንና ምድርን፣ በመካከላቸውም ያሉትን ፍጡራን በከንቱ አልፈጠርንም። ይህ የነዚያ የካዱት ሰዎች እሳቤ ነው። ከሓዲያን ከእሳት ወዮላቸው።» (ሷድ 27)*

በመጭው ዓለም ማመን እስተዋይ ሁሉ የሚቀበሉት፣ አእምሮም የሚያጸድቀው፣ ንጹህና ቀጥተኛ ተፈጥሮም የሚቀበለው እምነት ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው በመጭው ዓለም ካመነ አንድን ተግባር ለምን እንደሚሰራ እና እንደሚተው ያውቃል። ይህን የሚያደርገው ከአላህ ዘንድ ያለውን ጸጋ ተስፋ አድርጎ መሆኑን ይገነዘባል።

ሰውን የበደለ በመጭው ዓለም እዳ እንደሚከፍል ያምናል። መልካም የሰራ ምንዳ፣ ክፉ የሰራ ቅጣት እንደሚያገኘውም ያምናል። ሁሉም ነፍሶች የስራቸውን ዋጋ በትክክል ያገኛሉ። መለኮታዊ ፍትህ ይሰፍናል። አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ فَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ خَيْرًا يَرَهُ ۝٧ وَمَن يَعْمَلْ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ شَرًّا يَرَهُ ۝٨ ﴾ الزلزلة: ٧ - ٨

*«ቅንጣት ያክል መልካም የሠራ ሰው ያገኘዋል። ቅንጣት ያክል ክፉን የሠራም ሰው ያገኘዋል።»*
*(አል ዘልዘላህ 7-8)*

እለተ ቂያማ (ትንሳኤ) መቼ እንደሚከሰት የሚያውቅ ሰው የለም። ነብያትና መልእክተኞች፣ ወይም መላእክት እንኳ ቀኑን በትክክል አያውቁም። አላህ ብቻ የሚያውቀው ሚስጥር ነው። እንዲህ ብሏል፡

﴿ يَسْأَلُونَكَ عَنِ السَّاعَةِ أَيَّانَ مُرْسَاهَا قُلْ إِنَّمَا عِلْمُهَا عِندَ رَبِّي لَا يُجَلِّيهَا لِوَقْتِهَا إِلَّا هُوَ ﴾ الأعراف: ١٨٧

*«(ሙሐመድ ሆይ!) "ዕለተ ትንሳኤ መቼ ነው?" በማለት ይጠይቁሃል። እርሷን የሚመለከት እውቀት ያለው ከጌታዬ ዘንድ ነው። የምትከሰትበትን ዕለት ግልጽ የሚያደርግልንም እርሱ ብቻ ነው በላቸው።» (አል አእራፍ 187)*

﴿ إِنَّ اللَّهَ عِندَهُ عِلْمُ السَّاعَةِ ﴾ لقمان: ٣٤

*«የሰዓቷ (ትንሳኤ) እውቀት ያለው አላህ ብቻ ነው።" (ሉቅማን 34)*



5) **በቀዷቀደር ማመን**፡ አላህ ያለፈውንም፣ የአሁኑንም፣ የሚመጣውንም ሁሉ ያውቃል። የባሮቹን ሁኔታና ተግባር፣ የመሞቻ ጊዜና የሲሳይ መጠንም ያውቃል ብሎ ማመን በቀዷቀደር ማመን ይባላል። አላህ እንዲህ ብሏል፡

﴿ إِنَّ اللَّهَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٌ ۝٦٢ ﴾ العنكبوت: ٦٢

*«አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ ነው።» (አል አንከቡት 62)*

﴿ وَعِندَهُ مَفَاتِحُ الْغَيْبِ لَا يَعْلَمُهَا إِلَّا هُوَ وَيَعْلَمُ مَا فِي الْبَرِّ وَالْبَحْرِ وَمَا تَسْقُطُ مِن وَرَقَةٍ إِلَّا يَعْلَمُهَا وَلَا حَبَّةٍ فِي ظُلُمَاتِ الْأَرْضِ وَلَا رَطْبٍ وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُّبِينٍ ۝٥٩ ﴾ الأنعام: ٥٩

*«የሩቅ ሚስጥራት ቁልፎች በእጁ ናቸው። ከርሱ ውጭ ማንም አያውቃቸውም። (ሁሉንም) በየብስም በባሕርም ውስጥ ያሉ (ፍጡራንን ሁሉ) ያውቃል። ከቅጠልም ምንም አትረግፍም፣ እርሱ የሚያውቃት ቢሆን እንጅ። በምድር ጨለማዎች ውስጥ የምትገኝ እያንዳንዷ ቅንጣት፣ ርጥብ ወይም ደረቅ ነገር ግልጽ ከሆነው መጽሐፉ ውስጥ ሰፍራለች።» (አል አንዓም 59)*[58]

ይህን ሁሉ ከርሱ ዘንድ ካለ መጽሐፍ ውስጥ አስፍሮታል።

﴿ وَكُلَّ شَيْءٍ أَحْصَيْنَاهُ فِي إِمَامٍ مُّبِينٍ ۝١٢ ﴾ يس: ١٢

*«ሁሉንም ነገር ግልጽ ከሆነ መዝገብ ውስጥ አስፍረናል።» (ያሲን 12)*

አላህ እንዲህም ብሏል፡

---

[58] በቁርአን ውስጥ ከዚህች አንቀጽ ውጭ ሌላ አንቀጽ ባይኖር እንኳ ከአላህ የመጣ ለመሆኑ ይህችው ብቻ በቂ ማስረጃ ትሆን ነበር። ምክንያቱም የሰው ልጅ በየትኛውም ዘመን ሳይንስና ቴክኖሎጂ አድጓል በሚባልበት እና በእውቀቱ በተኩራራበት በዚህ ዘመን እንኳ እንዲህ ዓይነት ሁለንተናዊ የሆነ እውቀት ባለቤት መሆን ቀርቶ ማሰብ እንኳ አይችለም። ማድረግ የሚችለው በእርሱ አካባቢ ያለን እጽዋት ወይም እንስሳ የተወሰነ ሚስጥር መግለጽ ብቻ ነው። ለዚያውም ካወቀው የማያውቀው በጣም ይበዛል።

﴿أَلَمْ تَعْلَمْ أَنَّ اللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِي السَّمَاءِ وَالْأَرْضِ ۗ إِنَّ ذَٰلِكَ فِي كِتَابٍ ۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ ﴿٧٠﴾﴾ الحج: ٧٠

*«አላህ በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያለውን ሁሉ እንደሚያውቅ አታውቅምን? ይህ ሁሉ በመዝገብ ውስጥ ሰፍሯል። ይህን ማድረግ ለአላህ እጅግ ቀላል ነው።» (አል ሐጅ 70)*

አላህ አንድን ነገር ማድረግ ሲሻ «ሁን» ይለዋል ወዲያውኑም ይሆናል።

﴿إِنَّمَا أَمْرُهُ إِذَا أَرَادَ شَيْئًا أَنْ يَقُولَ لَهُ كُنْ فَيَكُونُ ﴿٨٢﴾﴾ يس: ٨٢

*«እንድ ነገር በሻለ ጊዜ ትእዛዙ "ሁን" የሚል ሲሆን፣ (ያ ነገር) ወዲያውኑ ይሆናል።» (ያሲን 82)*

አላህ ሁሉንም ነገር እንደፈጠረ ሁሉ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው።

﴿إِنَّا كُلَّ شَيْءٍ خَلَقْنَاهُ بِقَدَرٍ ﴿٤٩﴾﴾ القمر: ٤٩

*«እኛ ሁሉንም ነገር በልክ ፈጠርን። » (አል ቀመር 49)*

﴿اللَّهُ خَالِقُ كُلِّ شَيْءٍ﴾ الزمر: ٦٢

*«አላህ የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው።» (አል ዙመር 62)*

የሰው ልጆችን እንዲታዘዙት ፈጠረ። የአምልኮ ስርዓቱን ገለጻላቸው። እንዲፈጽሙትም አዘዛቸው። እርሱን ከመወንጀል አስጠነቀቃቸው። የሐጢአትን ምንነት አብራራላቸው። የአላህን ትእዛዝ በመፈጸም ምንዳ እንዲያገኙ ወይም ሐጢአት በመስራት እንዲቀጡ፣ ይህን የማድረግ አቅም ሰጣቸው።

አንድ ሰው «በቀዷቀደር» ማመኑ የሚከተሉትን ጥቅሞች ያስገኝለታል፡

1) አንድን ነገር ሲሰራ ማድረግ ያለበትን ሁሉ ያደርጋል። ሰበቡን ያደርሳል። ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን በአላህ ይመካል። ምክንያትና ውጤት የአላህ ቀደር (ውሳኔ) አካል መሆናቸውን ይረዳልና።



2) ይህ እምነት የቀልብ ረፍትንና መረጋጋትን ይሰጣል። ስክነትን ያጎናጽፋል። ሁሉም ነገር የሆነው በአላህ ውሳኔ መሆኑን፣ ያገኘው ክፉ ነገር ሊያጣው እንደማይችል ያመነ ነፍሱ ረፍት ታገኛለች። የአላህን ውሳኔ በደስታ ያስተናግዳል። ከርሱ የተሻለ የደስታና የእርጋታ ሕይወት የሚኖር የለም።

3) የሚፈልጉትን ሲያገኙ፣ ሐሳብ ሲሳካ፣ በራስ መደነቅንና መኩፈስን ያስወግዳል። ምክንያቱም ሐሳብ መሳካቱ የአላህ ጸጋና በርሱ ውሳኔ የተፈጸመ መሆኑን ያምናል። ስለዚህም አላህን ያመሰግናል።

4) ያሰቡት ሳይሳካ ሲቀር ወይም እንዳች መጥፎ ነገር ሲደርስ መረበሽን፣ መታወክን፣ ቁጭትንና ሐዘንን ያስወግዳል። ምክንያቱም በአላህ ውሳኔ የሆነ ነው። የርሱን ውሳኔ የሚያስቀር የለም። ይህን የተረዳ መታወኩ ይወገዳል። ትእግስት ያደርጋል። ምንዳም ከአላህ ይከጅላል፡

﴿مَا أَصَابَ مِنْ مُصِيبَةٍ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي أَنْفُسِكُمْ إِلَّا فِي كِتَابٍ مِنْ قَبْلِ أَنْ نَبْرَأَهَا ۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ ﴿٢٢﴾ لِكَيْلَا تَأْسَوْا عَلَىٰ مَا فَاتَكُمْ وَلَا تَفْرَحُوا بِمَا آتَاكُمْ ۗ وَاللَّهُ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٍ فَخُورٍ ﴿٢٣﴾﴾ الحديد: ٢٢ - ٢٣

*«በምድርም፣ በራሳችሁም ላይ የሚደርስ አንድም መከራ የለም፣ እንዲከሠት ከማድረጋችን በፊት መዝገብ ውስጥ የሰፈረ ቢሆን እንጅ። ይህ ለአላህ እጅግ በጣም ቀላል ነው። (ከመልካም ነገር) ባለፋችሁ እንዳታዝኑ፣ በተሰጣችሁም (ስለቅጥ) እንዳትደሰቱ (ይህን አደረግን)። አላህም ኩራተኛንና ጉረኛን ሁሉ አይወድምና» (አል ሐዲድ 22-23)*

5) ሙሉ በሙሉ በአላህ የመመካትን ስሜት ያስርጻል። ምክንያቱም ጥቅምም ሆነ ጉዳት በአላህ እጅ መሆኑን ሙስሊም ስለሚያውቅ ትእቢተኛን ለጉልበቱ አይፈራም። ከሰዎች መካከል አንዱን ፈርቶ በጎ ነገር ከመስራት አይታቀብም። ነቢዩ (ሰዐወ) ለኢብን አባስ እንዲህ ብለዋቸዋል፡

«ሰዎች ሁሉ አንተን ለማጥቃት ቢሰባሰቡና ቢተባበሩ አላህ ከጻፈልህ ውጭ ሌላ ነገር አይጠቅሙህም። በአንዳች ነገር ሊጎዱህ ቢሰባሰቡና ቢተባበሩም አላህ ከጻፈልህ ውጭ ሌላ ጉዳት አያደርሱብህም።» (አህመድና ቲርሚዚ)

# ተውባ

የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፦

«እያንዳንዱ የሰው ልጅ ስህተት ፈጻሚ ነው። ከስህተት ፈጻሚዎች ውስጥ በላጮቹ ተውባ አድራጊዎች ናቸው።» (አህመድና ቲርሚዚ)

የሰው ልጅ ደካማ ፍጡር በመሆኑ የሐጢአትን መከራ መሸከም ስለማይችል አላህ ለርሱ በማዘን ማቃለያ አበጀለት። ይህም ማቃለያ ተውባ ይባላል። ተውባ ትርጉሙ ወንጀልን አስቀያሚ ነገር መሆኑን በመረዳት፣ አላህን በመፍራትና ወደፊት ያዘጋጀለትን ጸጋም ተስፋ በማድረግ መተው፣ ለፈጸመው ወንጀል መቆጨት፣ በርሱ ላይ አለመዘውተር፣ በቀሪ እድሜ በበጎ ስራ ላይ መበርታት ነው።[62] ተውባ በሰውየውና በአምላኩ መካከል ብቻ የሚፈጸም የልቦና ተግባር ነው። ብዙ ውጣ ውረድ፣ ድካምና ስቃይ የለውም። የቀልብ ብቻ ተግባር ነው። ወደፊት ወንጀል ከመፈጸም መታቀብ ነው። ወንጀልን መተው ደግሞ ረፍት እንጅ ስቃይ አይደለም።[63]

ሚስጥርህን ከሚያጋልጥና ድክመትህን ያለ አግባብ ከሚጠቀምበት የሰው ልጅ ፊት ንስሐ መግባትና ሐጢአትን መናዘዝ አያስፈልግህም። ተውባ ባንተና በአምላክህ መካከል የሚደረግ ሚስጥራዊ ግንኙነት ነው። እርሱን በቀጥታ ምህረት ትለምነዋለህ። እንዲያቀናህም ትማጸነዋለህ። ንስሐህን ይቀበላል።

በእስልምና የውርስ ሐጢአት የሚባል ነገር የለም። ከሐጢአት የሚያጸዳ የተለየ ሰውም የለም። በኋላ ላይ እስልምናን የተቀበለው ነምሳዊው አይሁድ ሙሐመድ አሳድ እንዲህ ሲል ጽፏል፦

«በቁርአን ውስጥ በአንድም ቦታ ላይ የሰው ልጅ ከውርስ ሐጢአት መጽዳት እንደሚያስፈልገው የሚገልጽ አንድም መልእክት አላገኘሁም። በእስልምና በሰውየውና በእጣ ፈንታው መካከል የሚቆም የውርስ ሐጢአት የሚባል ነገር የለም። ለሰው ልጅ የሰራው

[62] አልሙፍረዳት ፊ ገሪበል ቁርአን ገጽ 76

[63] አልፈዋኢድ- ኢብንል ቀይም ገጽ 16



እንጅ ሌላ የለውም።[64]የሰው ልጅ የንስሐና የመዳን በር ተከፍቶለት ከሐጢአት ይጸዳ ዘንድ ቁርባን ማትረብ ወይም ራሱን መግደል አያስፈልገውም።»[65] አላህ እንዲህ ብሏል፦

﴿ وَأَن لَّيْسَ لِلْإِنسَٰنِ إِلَّا مَا سَعَىٰ ﴾ النجم: ٣٩

*«የሰው ልጅ ከለፋበት ውጭ ሌላ የለውም።» (አል ነጅም 39)*

ተውባ በርካታና ታላላቅ በጎ ውጤቶች አሉት። ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተወስተዋል፦

1) የአላህን ታጋሽነት ስፋት ሰውየው እንዲረዳ ያደርገዋል። አላህ ነውሩን ማጋለጥ ሲችል ሸፍኖለታል። ቅጣቱን ማፋጠን ሲችል አዘግይቶለታል። ቢያጋልጠው ኖሮ ከሰው መሐል ተከብሮ መኖር ባልቻለ ነበር። የሐጢአት ቆሻሻው አስቀያሚ ስብእና አላብሶት ሰዎች በናቁት እና በሸሹት ነበር። ግና አላህ ነውሩን ሸፍኖ፣ በክብር እንዲኖር አደረገው። በትእግስቱ ሸፈነው። አቅም ለገሰው። ሲሳይም ቸረው።

1) የነፍሱን ምንነት እንዲያውቅ ያደርገዋል። ነፍስ በክፉ ታዛለች። ከርሷ የመነጩ ሐጢአቶች፣ የፈጸመቻቸው ጥፋቶች ክልክል የሆኑ ስጋዊ ስሜቶችን ለመታገስ ደካማ መሆኗን ያሳያሉ። ስለዚህም ምንጊዜም የአላህ ጥበቃ ያሻታል። ከርሱ እንክብካቤ የምትብቃቃበት ቅጽበት የለም።

2) አላህ ለሰው ልጅ ተውባን በመደንገግ ትልቅ የደስታ ምክንያት አዘጋጀለት። ሰፊ የሐሴት በር ከፈተለት። እርሱም ወደ አላህ መመለስና በርሱ መታገዝ ነው። በተውባ አማካይነት ዱዓ፣ ለአላህ መዋደቅ፣ ጉዳይን ለርሱ ማዋየት፣ እርሱን መከጀል፣ ማፍቀር፣ መፍራት፣ ተስፋ ማድረግ እና መሰል ጸጋዎችን እንዲያጣጥም አደረገው። ነፍስ ወደፈጣሪዋ ይበልጥ እንድትጠጋ ረዳት። ተውባ ባይኖር ወደ አላህ መመለስና መቅረብ አይገኝም ነበር።

[64] አል ነጅም 39

[65] The Road to Meka p 140

3) በተውባ አማካይነት አላህ ያለፈን ወንጀል ይምራል። እንዲህ ብሏል፡-

﴿ قُلْ لِلَّذِينَ كَفَرُوا إِنْ يَنْتَهُوا يُغْفَرْ لَهُمْ مَا قَدْ سَلَفَ ﴾ الأنفال: ٣٨

«ለነዚያ ለካዱት ሰዎች (ከክህደት) ከታቀቡ ያለፈ ወንጀላቸው እንደሚምርላቸው፣...ንገራቸው» (አል አንፋል 38)

4) ወንጀልን ወደ በጎ ስራ ይቀይራል።

﴿ إِلَّا مَنْ تَابَ وَآمَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَالِحًا فَأُولَٰئِكَ يُبَدِّلُ اللَّهُ سَيِّئَاتِهِمْ حَسَنَاتٍ وَكَانَ اللَّهُ غَفُورًا رَحِيمًا ﴿٧٠﴾ ﴾ الفرقان: ٧٠

*«ንስሐ የገቡ፣ ያመኑና መልካም ተግባራትን የፈፀሙት ሲቀሩ። ለእነርሱ፣ አላህ ኃጢአታቸውን በመልካም ሥራዎች ይቀይርላቸዋል። አላህ መሓሪ፣ አዛኝ ነውና።» (አል-ፉርቃን 70)*

5) ሰውየው መስሎቹ የሰው ልጆች ሲያጠፉና ሲሳሳቱ አላህ ለርሱ ጥፋት ያሳየውን ትእግስትና ይቅር ባይነት እርሱም እንዲያሳይ ተውባ ያስታውሰዋል። ምንዳ የተግባር አካል ነውና። ሰዎችን በእንዲህ አይነት መልካም አኳኋን ያስተናገደ ከአላህም ዘንድ ተመሳሳይ መስተንግዶ ይደረግለታል። አላህ ከፉ ስራውን ወደ በጎ አድራጎት ይመልስለታል። እርሱ የመሰሎቹን ሰዎች ከፉ ስራ በበጎ እንደመለሰው።

6) ነፍስ ስህተቷና ግድፈቷ የበዛ መሆኗን በማስታወስ የሌሎችን ነውር ከመከታተል ጥፋት እንዲቆጠብ፣ የሌሎችን ጉድለት ከመከታተል ይልቅ ራሱን በማስተካከል እንዲጠመድ ይረዳዋል።

ይህን ክፍል በአንድ ሐዲሳዊ ዘገባ እቋጨዋለሁ። አንድ ሰው ከነቢዩ ዘንድ መጣና፡- «የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ ያልፈጸምኩት ሐጢአት የለም» አላቸው። «የአላህን አንድነትና የነብዩ መሐመድን መልእክተኛነት ትመሰክር የለምን?» በማለት ሦስት ጊዜ ደጋግመው ጠየቁት። «አዎ» አላቸው። «ይህ ምስክርነትህ ሐጢአትህን ያብስልሐል» አሉት። (አቡ የእላና ጠበራኒ)



በሌላ ዘገባ እንደተወሳው ከነቢዩ ዘንድ መጣና «አንድ ሰው ከአላህ ጋር አንዳችን ነገር ከማጋራት ውጭ ሌሎች ሐጢአቶችን ሁሉ ቢሰራ የተውባ እድል ይኖረዋልን?» ሲል ጠየቃቸው። «ሰልመሐልን?» አሉት። «ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና አንተም የአላህ መልእክተኛ መሆንህን እመሰክራለሁ።» አለ። «እንግዲያውስ የተውባ እድል አለህ። ከእንግዲህ በኋላ በጎ ስራ ፈጽም። ሐጢአትንም ተው። አላህም (በችሮታው) ሐጢአትህን ሁሉ ወደ በጎ ይቀይርልሐል» አሉት። «አኩይ ድርጊቴንና ክፋቴን ሁሉ?» ሲልም ጠየቃቸው። «አዎ» አሉት። «አኳሁ አክበር» በማለት ጮኸ። ከአይን እስኪሰወር ድረስም ይህንኑ ቃል ደጋገመ። (ጠበራኒ)

ነቢዩ በሐዲሳቸው እንደገለጹልን ኢስላም ከርሱ በፊት ያለውን ሐጢአት ያብሳል። እውነተኛ ተውባም ከርሱ በፊት የተፈጸሙ ወንጀሎችን ሁሉ ያስወግዳል።

# በእስልምና ያልተመራ ሰው ፍጻሜ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዳየነው ኢስላም የአላህ ሐይማኖት ነው። እውነተኛው ሐይማኖትም እርሱው ብቻ ነው። ሁሉም ነብያትና የአላህ መልእክተኞች የሰበኩት እምነትም እርሱ ነው። በርሱ ላመነ አላህ በዚህችም ሆነ በቀጣዩ አለም ታላቅ ምንዳ አዘጋጅቶለታል። በርሱ የካደን ደግሞ በብርቱ ቅጣት ዝቶበታል።

አላህ የዚህ ዩኒቨርስ ፈጣሪና ባለቤት፤ አንተ ደግሞ ፍጡር እንደመሆንህ ተፈጥሮን ላንተ ገርቶልሐል። ሕግጋትን አበጅቶልሐል። እንድትከተለውም አዟል። በርሱ ካመንክና ያዘዘውን ከፈጸምክ፤ ከከለከለህም ከታቀብክ በመጭው ዓለም አላህ ቃል የገባልህን ዘልዓለማዊ ድሎትና ስኬት ታገኛለህ። በዚህች አለም ጸጋዎችም ትደሰታለህ። ከማንም በላይ ብልህ አእምሮና የጸዳች ነፍስ ካላቸው ወገኖች፤ ማለትም ከነብያት፤ ከደጋግ ሰዎችና ከአላህ የቅርብ መላኢኮች ጋርም ትመሳሰላለህ።

በአንጻሩ በአምላክ ከካድክ ይህችንም መጭውንም አለም ትከስራለህ። በሁለቱም አለማት ለቁጣውና ለቅጣቱ ትዳረጋለህ። ከማንም በላይ ጎደሎ አእምሮና የቆሸሸች ነፍስ ካላቸው ፍጡራን፤ ማለትም ከሰይጣናት፤ ከበዳዮች፤ ከበካዮችና ከአምባገነኖች ጋርም ትመሳሰላለህ።

አላህን መካድና በእስልምና አለመመራት በጥቅሉ ይህን አደጋ ያስከትላል። ክህደት የሚያስከትለውን ጣጣ ቀጥሎ በዝርዝር አቀርባለሁ፡

## 1) በፍርሃት መሞላትና ሰላም ማጣት

አላህ በርሱ ላመኑትና መልእክተኞቹን ለተከተሉት ሁሉ በዚህችም ሆነ በመጭው ዓለም የተሟላ ሰላም ቃል ገብቶላቸዋል።

﴿ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَلَمْ يَلْبِسُوٓا۟ إِيمَـٰنَهُم بِظُلْمٍ أُو۟لَـٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلْأَمْنُ وَهُم مُّهْتَدُونَ ﴿٨٢﴾ ﴾
الأنعام: ٨٢



*«እነዚያ ያመኑትና እምነታቸውን በበደል ያልበከሉት ሰላም የነርሱ ብቻ ነው። ቅኑን ጉዳና የተመሩትም እነርሱ ብቻ ናቸው።»* (*አል አንዓም 82*)

አላህ ሰላም ለጋሽና የበላይ ነው። በዚህች ዩኒቨርስ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሁሉም ባለቤት ነው። አንድን ሰው በእምነቱ ምክንያት ሲወደው ውስጣዊ ሰላምና መረጋጋት ይለግሰዋል። ሰውየው በርሱ ሲከድ ሰላምንና መረጋጋትን ይነጥቀዋል። እናም በመጭው ዓለም ፍጻሜውን የሚፈራ፤ በዚህች አለም በሽታንና ችግርን፤ የመጭው ጊዜ እጣ ፈንታውን የሚሰጋ ሆኖ ታገኘዋለህ። ለራሱና ለንብረቱ ደህንነት ስጋት ስለሚንጠውና በአላህ ስለማይመካ የመድን ዋስትና ቢሮዎችን ሲያጣብብ ታገኘዋለህ።

## 2) የጭንቅ ሕይወት

አላህ የሰውን ልጅ ፈጠረ። በዩኒቨርሱ ውስጥ ያሉ ነገሮችንም ለጥቅሙ ገራለት። የሁሉንም ፍጡራን ሲሳይና እድሜም ወሰነ። በራሪ አእዋፍ ከጎጆው ወጥቶ ከዛፍ ዛፍ እየተንጠላጠለና እያዜመ የእለት ጉርሱን ሲፈልግ ታገኘዋለህ። የሰው ልጅም አላህ ሲሳያቸውንና እድሜያቸውን ከወሰነላቸው ፍጡራን መካከል አንዱ ነው። በጌታው ካመነና በርሱ ሕግና ስርዓት ከተመራ ደስታና መረጋጋት ይለግሰዋል። ሁለንገሩን ገር ያደርግለታል። በኑሮው ከዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም እንኳ ደስታ አይለየውም።

በጌታው ከካደና እርሱን ከማምለክ ከተኩራራ ግን ሕይወቱን የጭንቅ ሕይወት ያደርግበታል። ጭንቀትና ሐሳብ ያሸክመዋል። የደስታና የድሎት ሰበቦች ሁሉ በእጁ ቢሆኑ እንኳ ከጭንቅ አይታደጉትም። ለዜጎቻቸው የቁሳዊ ሐይወት ድሎትን ባመቻቹ ሐገራት ውስጥ ራስን የማጥፋት ወንጀል መበራከቱን አታይምን? ሕይወትን ደስታማ ለማድረግ የሚመረተውን የቁስ መዓትና የመዝናኛ ጉዞዎችን ብዛት አታስተውልምን? ልቦና ከእምነት ሲነጥፍና የመጪነት ስሜት ሲነግስ ይህን ጭንቀት በአዳዲስ ነገሮች ለማስወገድ የሚደረግ ከንቱ ሙከራ ይበረክታል። አላህ እንዲህ ሲል እውነትን ተናግሯል፡

﴿ وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِى فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ أَعْمَىٰ ﴿١٢٤﴾ ﴾ طه: ١٢٤

*"ግና ከመልዕክቴ ያፈገፈገ ሕይወቱ ጭንቅ የበዛበት ይሆናል። በትንሳኤ ቀንም እውር አድርገን እንቀሰቅሰዋለን።» (ጧሃ 124)*

## 3) ከራሱና በዙሪያው ካለው አለም ጋር በግጭት ይኖራል

ነፍስ የተፈጠረችው በአሐዳዊ ተፈጥሯዊ እምነት ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ فِطْرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِى فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيْهَا ﴾ الروم: ٣٠

*«(ይህ) አላህ የሰው ልጆችን የፈጠረበት ተፈጥሯዊ መንገድ (ዲን) ነው።» (አል ሩም 30)*

የሰው ልጅ አካል ለአምላኩ እጅ ሰጥቷል። እርሱ በዘረጋው ሕግና ስርዓት ይመራል። አላህን ከካደ ግን ከዚህ ተፈጥሮው ጋር ይጋጫል። የመምረጥ መብት የተሰጠው የሕይወቱ መስክ የአምላኩን ትእዛዝ ይቃረናል። እናም አካሉ ለአላህ ሕግ ያደረ ሆኖ እያለ ሕሊናው በእርሱ ላይ በማመጽ ከርሱ ጋር ይጋጫል።

በዙሪያው ካሉ ፍጡራን ጋርም ይጋጫል። ምክንያቱም ከግዙፉ ኘላኔት እስከ ትንሿ አተም ድረስ ያሉ ፍጡራን ሁሉ ለአምላካቸው ያደሩ፣ እርሱ በዘረጋው ስርዓት የሚመሩ ናቸው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰٓ إِلَى ٱلسَّمَآءِ وَهِىَ دُخَانٌ فَقَالَ لَهَا وَلِلْأَرْضِ ٱئْتِيَا طَوْعًا أَوْ كَرْهًا قَالَتَآ أَتَيْنَا طَآئِعِينَ ﴿١١﴾ ﴾ فصلت: ١١

*«ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ። ጭስ ነበረች፣ እርሷንና መሬትንም፡- "ወዳችሁም ሆነ ሳትወዱ ኑ።" አላቸው። "ወደን (እና ታዛዦች ሆነን) መጣን" አሉ።» (ፉሲለት 11)*

ይህ ዩኒቨርስ ልክ እንደርሱ ለአላህ እጅ የሰጠውን ይወዳል። በአላህ ላይ ያመጸውን ይጠላል። ከሐዲ ከአጠቃላዩ የተፈጥሮ ሂደት ያፈነገጠ ነው። ራሱን በአምላክ ተቀናቃኝነት ሰይሟል። በርሱ ላይ አምጿል።



ይህም በመሆኑ ክህደቱንና አመጹን ሰማያትና ምድር እንዲሁም በውስጣቸው ያሉ ፍጡራን ሁሉ እጅግ ይጠሉታል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَقَالُوا۟ ٱتَّخَذَ ٱلرَّحْمَٰنُ وَلَدًا ﴿٨٨﴾ لَّقَدْ جِئْتُمْ شَيْـًٔا إِدًّا ﴿٨٩﴾ تَكَادُ ٱلسَّمَٰوَٰتُ يَتَفَطَّرْنَ مِنْهُ وَتَنشَقُّ ٱلْأَرْضُ وَتَخِرُّ ٱلْجِبَالُ هَدًّا ﴿٩٠﴾ أَن دَعَوْا۟ لِلرَّحْمَٰنِ وَلَدًا ﴿٩١﴾ وَمَا يَنۢبَغِى لِلرَّحْمَٰنِ أَن يَتَّخِذَ وَلَدًا ﴿٩٢﴾ إِن كُلُّ مَن فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ إِلَّآ ءَاتِى ٱلرَّحْمَٰنِ عَبْدًا ﴿٩٣﴾ ﴾ مريم: ٨٨ - ٩٣

*"አዛኙ አምላክ ልጅ ያዘ።" አሉ። (አጋሪዎች ሆይ!) እጅግ ከፉ የሆነን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ። ለአዛኙ አምላክ ልጅ አለው ስላሉ ሰማያት ሊቀደዱ፣ ምድርም ልትሰነጠቅ፣ ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቀርባሉ። ልጅ መያዝ ለአዛኙ አምላክ ተገቢው አይደለም። በሰማያትም በምድርም ውስጥ አንድም የለም፣ ለአር-ረሕማን ባሪያ ሆኖ የሚመጣ ቢሆን እንጅ።» (መርየም 88-93)*

አላህ ፈርአውንንና ሰራዊቱን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

﴿ فَمَا بَكَتْ عَلَيْهِمُ ٱلسَّمَآءُ وَٱلْأَرْضُ وَمَا كَانُوا۟ مُنظَرِينَ ﴿٢٩﴾ ﴾ الدخان: ٢٩

*«ሰማይም ምድርም አላለቀሱላቸውም። (ጥቂት) የመቆየት ዕድልም አልተሰጣቸውም።» (አል ዱኻን 29)*

## 4) መሐይም ሆኖ ይኖራል

ክህደት ማለት መሐይምነት ነው። ከተራው መሐይምነት ይከፋል። ምክንያቱም ከሐዲ አምላኩን አያውቅም። አላህ ድንቅ በሆነ ጥበብ የዘረጋውን አለምና በርሱ ውስጥም የረጨውን ተአምር እያየ ዩኒቨርሱን ያነጸውንና እርሱን የፈጠረውን አምላክ ይክዳል። ይህ ታላቅ መሐይምነት አይደለምን?

## 5) ራሱንም በዙሪያው ያሉ ሰዎችንም በዳይ ሆኖ ይኖራል

ላልተፈጠረለት አላማ በመዋሉ፣ አምላኩን ትቶ ሌላን አካል በማምለኩ ራሱን በድሏል። በደል ማለት አንድን ነገር ያለ ቦታው

﴿ أَوَلَمْ يَرَ الْإِنسَانُ أَنَّا خَلَقْنَاهُ مِن نُّطْفَةٍ فَإِذَا هُوَ خَصِيمٌ مُّبِينٌ ﴿٧٧﴾ وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِيَ خَلْقَهُ ۖ قَالَ مَن يُحْيِي الْعِظَامَ وَهِيَ رَمِيمٌ ﴿٧٨﴾ قُلْ يُحْيِيهَا الَّذِي أَنشَأَهَا أَوَّلَ مَرَّةٍ ۖ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيمٌ ﴿٧٩﴾ ﴾ يس: ٧٧ - ٧٩

*«የሰው ልጅ ከፍትወት ጠብታ እንደ ፈጠርነው አላወቀምን? ይሁንና (የተለያዩ የሕይወት እርከኖችን ካለፈ በኋላ) ግልጽ ተሟጋች ለመሆን በቃ። ለኛ ምሳሌ አደረገልን። አፈጣጠሩንም ዘነጋ። "የበሰበሱ አጥንቶችን ሕያው የሚያደርግ ማን ነው?" አለ። በል፦ "ያ መጀመሪያ ከምንም ያስገ ኛቸው (አምላክ) ሕያው ያደርጋቸ ዋል። እርሱ ፍጡራንን ሁሉ ጠንቅቆ ዐዋቂ ነው።"(ያሲን 77-79)*

﴿ يَا أَيُّهَا الْإِنسَانُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ الْكَرِيمِ ﴿٦﴾ الَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّاكَ فَعَدَلَكَ ﴿٧﴾ فِي أَيِّ صُورَةٍ مَّا شَاءَ رَكَّبَكَ ﴿٨﴾ ﴾ الانفطار: ٦ - ٨

*«የሰው ልጅ ሆይ! ፍፁም ቸር በሆነው ጌታህ (ላይ እንድታምፅ) ያነሳሳህ ምንድን ነው? በፈጠረህ፣ አካለ ሙሉ ባደረገህና ባስተካከለህም፣ በመረጠው ቅርፅና ውበት በፈጠረህም (ጌታህ ላይ እንድታምፅ ያነሳሳህ ምንድን ነው)?» (አል ኢንፊጣር 6-8)*

ከድህነት እንዲገላግልህ፣ ከበሽታ እንዲፈውስህ፣ ችግርን እንዲያስወግድልህ፣ ሐጢአትህን እንዲምርልህ፣ ስትበደል እንዲረዳህ፣ መንገድ ስትስት እንዲመራህ፣ ያላወቅከውን እንዲያሳውቅህ፣ ስትፈራ ሰላም እንዲቸርህ፣ ስትደክም እንዲያበረታህ፣ ጠላትህን እንዲመልስልህ፣ ሲሳይም እንዲለግስህ አምላክህን ከፊቱ ቆመህ የመማጸንን ለዛ ራስህን እንዴት ትነፍጋለህ?[67]

አላህ ለሰው ልጆች ከሰጣቸው ጸጋዎች ሁሉ ከሐይማኖት ጸጋ ቀጥሎ ትልቁ የአእምሮ ጸጋ ነው። በርሱ የሚጠቅመውን ከሚጎዳው እንዲለይ፣ የአላህን ትእዛዝና እቀባ እንዲገነዘብ ማስቻሉ ነው። እንደዚሁም የፈጠረለትን ትልቁን ዓላማ እንዲያውቅ ማስቻሉ ነው። ይህም አላማ አላህን በርሱ ላይ ምንንም አካል ሳያጋሩ ማምለክ ነው። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

---

[67] ሚፍታህ ዳረ ስአዳ 1251



﴿ وَمَا بِكُم مِّن نِّعْمَةٍ فَمِنَ اللَّهِ ۖ ثُمَّ إِذَا مَسَّكُمُ الضُّرُّ فَإِلَيْهِ تَجْأَرُونَ ﴿٥٣﴾ ثُمَّ إِذَا كَشَفَ الضُّرَّ عَنكُمْ إِذَا فَرِيقٌ مِّنكُم بِرَبِّهِمْ يُشْرِكُونَ ﴿٥٤﴾ ﴾ النحل: ٥٣ - ٥٤

*«የጌታችሁ ፀጋዎች ሁሉ ከአላህ (የተገኙ) ናቸው። አንዳች ጉዳት ባገኛችሁም ጊዜ ወደርሱ ትራጮኻላችሁ። ጉዳቱንም ከናንተ ላይ ባስወገደ ጊዜ ከውስጣችሁ ከፊሎቹበጌታቸው ያጋራሉ።» (አል ነህል 53-54)*

የሰው ልጅ ሆይ፣ ብልህና አስተዋይ ሰው ታላላቅ ጉዳዮችን ይወዳል። ተራና ርካሾችን ደግሞ ይጠላል። የነብያቶችንና የሌሎችንም ደጋግ ሰዎችን ፈለግ መከተልን ይወዳል። ሁሌም እነርሱን በአርአያነት ለመከተል፣ በጎ ስራቸውን ለመፈጸም ይጥራል። ወደፊት ከነርሱ ጋር ለመኖራበት ይመኛል። ይህን ምኞቱን ለማረጋገጥ መንገዱን አላህ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡-

﴿ قُلْ إِن كُنتُمْ تُحِبُّونَ اللَّهَ فَاتَّبِعُونِي يُحْبِبْكُمُ اللَّهُ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ذُنُوبَكُمْ ۗ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٣١﴾ ﴾ آل عمران: ٣١

*«በላቸው፦ "አላህን የምትወዱ ከሆናችሁ ተከተሉኝ፣ አላህ ይወዳችኋል፣ ኃጢአቶቻችሁንም ይምራል፣ አላህ መሓሪ አዛኝ ነው።"(አሊ ዒምራን 31)*

ይህን ሲፈጽም አላህ ከነብያት፣ከመእከተኞች ከሸሂዶችና ከደጋግ ሰዎች ያኖራብተዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَمَن يُطِعِ اللَّهَ وَالرَّسُولَ فَأُولَٰئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِم مِّنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ وَالصَّالِحِينَ ۚ وَحَسُنَ أُولَٰئِكَ رَفِيقًا ﴿٦٩﴾ ﴾ النساء: ٦٩

*«አላህንና መልዕክተኛውንም የሚታዘዝ (በመጪው ዓለም) አላህ ፀጋውን ከለገሳቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትና ከደጋጐች ጋር ይሆናል። የነዚህ ባልንጀራነት ምን ያምር!» (አል ኒሳእ 69)*

አንተ ሰው ሆይ፣ ለራስህ ጊዜ ስጥተህ፣ ከሰዎች ገለል ብለህ የመጣልህን እውነት እንድትፈትሽ ጋብዤሐለሁ። መረጃውን አስተንትን። እውነት ሆኖ ካገኘህው ተከተለው። የልምድ እና የባህል እስረኛ አትሁን። ከባልንጀሮችህ፣ ከአገርህና ከአያት ቅድመ አያቶችህ ውርስ ይህ እንደሚበልጥብህ እወቅ። አላህ ካህድያንን ወደዚህ ስልት እንዲህ በማለት መርቷቸዋል፡-

﴿قُلْ إِنَّمَا أَعِظُكُم بِوَاحِدَةٍ ۖ أَن تَقُومُوا لِلَّهِ مَثْنَىٰ وَفُرَادَىٰ ثُمَّ تَتَفَكَّرُوا ۚ مَا بِصَاحِبِكُم مِّن جِنَّةٍ ۚ إِنْ هُوَ إِلَّا نَذِيرٌ لَّكُم بَيْنَ يَدَيْ عَذَابٍ شَدِيدٍ (٤٦)﴾ سبأ: ٤٦

*"እንዲት ነገር ብቻ እመክራችኋለሁ። ይህውም ሁለት ሁለት፣ አንድ አንድ እየሆናችሁ ለአላህ ስትሉ (በቅንነትና በታማኝነት) እንድትቆሙና ባልደረባችሁ (ሙሐመድ) እብደት የሌለበት መሆኑን፣ እርሱ ብርቱ የሆነን ቅጣት የሚያስጠነቅቃችሁ እንጅ ሌላ እንዳልሆነ አስባችሁ እንድትደርሱበት ብቻ ነው።" በላቸው።(ሰበእ 46)*

አንተ ሰው ሆይ! እስልምናን ብትቀበል የምትጎዳው ወይም የሚቀርብህ ነገር የለም። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿وَمَاذَا عَلَيْهِمْ لَوْ آمَنُوا بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَأَنفَقُوا مِمَّا رَزَقَهُمُ اللَّهُ ۚ وَكَانَ اللَّهُ بِهِمْ عَلِيمًا (٣٩)﴾ النساء: ٣٩

*«በአላህና በመጭው ዓለም ቢያምኑና አላህ ከለገሳቸውም (ሲሳይ) ቢመፀውቱ ምን ጉዳት ያገኛቸዋል? አላህ እነርሱን ጠንቅቆ ዐዋቂ ነው» (አል ኒሳእ 39)*

ኢብን ከሲር ይህን አንቀጽ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፡-

«በአላህ ቢያምኑና ምስጉን የሆነውን ጎዳና ቢከተሉ፣ መልካም ለሰሩ ሰዎች በመጭው ዓለም የገባውን ቃል ቢያምኑና ተስፋ ቢያደርጉ፣ ከሰጣቸው ሲሳይ እርሱ በሚወደው መልኩ ቢመጸውቱ ምን የሚጎዳቸው ነገር አለ? ንጹህና የተበላሸ ሐሳባቸውን ለይቶ ያውቃል። ከመካከላቸው ለበጎ ነገር ሊመራም የሚገባው ማን እንደሆነም ለይቶ ያውቃል። እናም ለበጎ ይገጥመዋል። መቀናትን ይመራዋል። ለሚወደው በጎ ስራ ያበቃዋል። ውርደት እና ከእዝነቱ በር መባረር ያለበትንም ለይቶ ያውቃል። ከርሱ በር የተባረረ አፈረ። በዚህችም በመጭውም ዓለም ከሰረ።»[68]

እስልምናን መቀበልህ መስራት ከምትፈልገው በአላህ የተፈቀደ ስራ አያቅብህም። ከዚህም አልፎ አላህ የርሱን ውዴታ በመሻት ለምትሰራው ስራ ሁሉ ይመነዳሐል። ያ ስራ ዓለማዊ ሕይወትህን የሚያሻሽል፣ ገንዘብህን፣ ስልጣንህን፣ ወይም ክብርህን የሚጨምር ቢሆንም እንኳ። ስጋዊ ፍላጎትህን ለማሟላት የምትፈጽማቸው

[68] ተፍሲር ቢን ከሲር 1/497



የተፈቀዱ (ሐላል) ተግባሮች እንኳ ከሐራም ለመብቃቃት እስበህ ከፈጸምካቸው ምንዳ ያስገኛሉ። የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ)፡- «ለናንተ አንዳችሁ በሚፈጽመው ጾታዊ ግንኙነት ውስጥ ምጽዋት አለ።» በማለት ተናገሩ። «የአላህ መልእክተኛ ሆይ፣ አንዳችን ስጋዊ ፍላጎቱን ስላረካ ምንዳ ያገኛልን?» በማለት ጠየቋቸው። «በሐራም ላይ ቢያውለው ኖሮ ወንጀል ይሆንበት አልነበረምን?» በማለት ጠየቁ። «አዎ» አሏቸው። «እንደዚሁም በሐላል ላይ ሲያውለው ምንዳ ያገኛል።» አሉ።

መልእክተኞች እውነትን ይዘው መጥተዋል። የአላህንም ፈቃድና ፍላጎት ሰብከዋል። የሰው ልጅም በዚህች ዓለም ሕይወት ውስጥ ከተሟላ እውቀትና መረጃ ጋር እንዲጓዝና በመጭው ዓለምም ከተሳካላቸው ሰዎች እንዲሆን የአላህን ሕግና ስርዓት (ሸሪዓ) ማወቅ በእጅጉ ያስፈልገዋል። አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿يَا أَيُّهَا النَّاسُ قَدْ جَاءَكُمُ الرَّسُولُ بِالْحَقِّ مِن رَّبِّكُمْ فَآمِنُوا خَيْرًا لَّكُمْ ۚ وَإِن تَكْفُرُوا فَإِنَّ لِلَّهِ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضِ ۚ وَكَانَ اللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا (١٧٠)﴾ النساء: ١٧٠

*«የሰው ልጆች ሆይ! መልዕክተኛው ከጌታችሁ ዘንድ እውነትን አምጥቶላችኋል። እመኑበት። ለናንተ የተሻለ ይሆናልና። ብትክዱም፣ (የምትጎዱት ራሳችሁን ብቻ ነው)። (ምክንያቱም) በሰማያትም በምድርም ውስጥ ያሉት ሁሉ የአላህ ናቸው። አላህም ዐዋቂ፣ ጥበበኛ ነው።» (አል ኒሳእ 170)*

﴿قُلْ يَا أَيُّهَا النَّاسُ قَدْ جَاءَكُمُ الْحَقُّ مِن رَّبِّكُمْ ۖ فَمَنِ اهْتَدَىٰ فَإِنَّمَا يَهْتَدِي لِنَفْسِهِ ۖ وَمَن ضَلَّ فَإِنَّمَا يَضِلُّ عَلَيْهَا ۖ وَمَا أَنَا عَلَيْكُم بِوَكِيلٍ (١٠٨)﴾ يونس: ١٠٨

*"የሰው ልጆች ሆይ! ከጌታችሁ ዘንድ እውነቱ መጣላችሁ። የተቀና በመቀናቱ ተጠቃሚው ራሱ ነው። መንገድ የሳተም በእድራጎቱ ተጐጂው እርሱ ብቻ ነው። እኔ የናንተን (ተግባር) ተቆጣጣሪ አይደለሁም።" በላቸው።(ዩኑስ 108)*

አንተ ሰው ሆይ፣ ብትሰልም የምትጠቅመው ራስህን ነው። ብትክድም የምትጎዳው ራስህን ነው። አላህ ከፍጡራኑ የተብቃቃ ነው። የወንጀለኞች ወንጀል አይጎዳውም። የታዛዦች መታዘዝም አይጠቅመውም። እያወቀ እንጅ አይወነጀልም። በፈቃዱ እንጅ ትእዛዙ አይፈጸምም። በነቢዩ አማካይነት እንዲህ የሚል መልእክት አስተላልፏል፡-

«ባሮቼ ሆይ፣ በራሴ ላይ በደልን እርም አደረግኩ። በናንተ መካከልም እንደዚሁ እርም አድርጌዋለሁ። ስለዚህም አትበዳደሉ። ባሮቼ ሆይ፣ እኔ ያቀናሁት ሲቀር ሁላችሁም መንገድ የሳታችሁ ናችሁ። ስለዚህም እንዳቀናችሁ ለምኑኝ፣ አቀናችኋለሁ። ባሮቼ ሆይ፣ እኔ የመገብኩት ሲቀር ሁላችሁም የተራባችሁ ናችሁ። ስለዚህም እመግባችሁ ዘንድ ለምኑኝ፣ እመግባችኋለሁ። እኔ ያለበስኩት ሲቀር ሁላችሁም የታረዛችሁ ናችሁ። ስለዚህም አለብሳችሁ ዘንድ ለምኑኝ፣ አለብሳችኋለሁ። ባሮቼ ሆይ፣ ቀንም ሌትም ሐጢአት ትፈጽማላችሁ። እኔ ደግሞ ወንጀሎችን ሁሉ እምራለሁ። ስለዚህ ምህረት ለምኑኝ እምራችኋለሁ። ባሮቼ ሆይ፣ እኔን ለመጉዳትም ሆነ ለመጥቀም አቅም የላችሁም። ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያችሁም የመጨረሻችሁም፣ ሰዋችሁም አጋንንቶቻችሁም ከመካከላችሁ ይበልጥ እኔን ፈሪ የሆነውን ሰው ልቦና ቢይዙ ይህ ድርጊታቸው ከንግስናዬ ቅንጣት ታህል አያክልም።

ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያችሁም የመጨረሻችሁም፣ ሰዋችሁም አጋንንቶቻችሁም ከመካከላችሁ ይበልጥ አመጸኛ የሆነውን ሰው ልቦና ቢይዙ፣ ይህ አመጻቸው ከንግስናዬ ቅንጣት ታህል አያጎድልም። ባሮቼ ሆይ፣ የመጀመሪያችሁም የመጨረሻችሁም፣ ሰዎችሁም አጋንንታችሁም ከአንድ መስክ ላይ ቆመው ቢለምኑኝና የጠየቁኝን ሁሉ ብሰጣቸው ከኔ ዘንድ ካለው ሐብት መርፌ ከውቅያኖስ ውስጥ ብትጠልቅ ልታጎድል የምትችለውን ውሃ ያህል እንኳ አያጎድልም።

ባሮቼ ሆይ፣ ስራዎቻችሁን በጥንቃቄ እመዘግባለሁ፡ በርሱም እመነዳችኋለሁ። መልካም ነገር ያገኘ አላህን ያመስግን። ከዚህ ውጭ ያገኘ ደግሞ ራሱን እንጅ አይውቀስ።» (ሙስሊም)

የዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ምስጋና ይድረሰው። የነብያትና የመልእክተኞች ሁሉ ፈርጥ በሆኑት በነቢዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልንጀሮቻቸው ሁሉ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈን።

=ተፈጸመ=

ـدع مجاناً ولا يجوز بيـ

# الإسلام أصــوله ومبادئه
# باللغة الأمهرية (إثيوبيا)

تأليف

الدكتور/ محمد بن عبد الله السحيم

الطبعة الأولى محرم لعام ١٤٣١هـ

APE4523/2002

ترجمة / حسن ناجو